

«እርስ በእርስ ባለመግባባት ከድህነት የምንወጣበትን ጊዜ ልናራዝመው አይገባም»

- ኢንተርናሽናል ሼፍ አንተነህ ድፋባቸው

ገጽ 6

የወባ በሽታ ስርጭትና የኢትዮጵያ ጥረት

ገጽ 8


# አዲስ ዘመን

81ኛ ዓመት ቁጥር 281 ሰኔ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


## በቱሪዝም ዘርፍ እመርታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የፖሊሲ ማሻሻያ እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ

- ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ 23 ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ ታቅዷል



ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

ወርቁ ማሩ

ሀዋሳ፡- በኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፉ ያለውን እምቅ የቱሪዝም ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል ዘርፉን ለመለወጥ የሚያስችሉ የፖሊሲ ማሻሻያ ሥራዎች እየተካሄዱ መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ ገለጹ። በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ 23 ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ መታቀዱንም ጠቁመዋል።

"ኢትዮጵያ እያሸነፈች ትሻገራለች" በሚል መሪ ሃሳብ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሃዋሳ ባዘጋጀው የፓናል ውይይት ላይ ጥናት ያቀረቡት የቱሪዝም ሚኒስትሯ አምባሳር ናሲሴ ጫሊ እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፉ ያላት እምቅ አቅም ከፍተኛ ነው። ይህንን ዘርፍ ለማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል።

አምባሳደር ናሲሴ በጽሁፋቸው እንደጠቆሙት ቱሪዝም በኢትዮጵያ ተቋማዊ ቅርጽ ይዞ የመጣው

በቱሪዝም ዘርፍ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








## ባለፉት 11 ወራት ከስጋና የስጋ ተረፈ ምርት 110 ሚሊዮን ዶላር ተገኘ

ዳንኤል ዘነበ

አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት ዓመት በባለፉት 11 ወራት ለውጭ ገበያ ከቀረበው 21 ሺህ ቶን ስጋና የስጋ ተረፈ ምርት 110 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን አስታወቀ።

በባለሥልጣኑ የኤክስፖርት ቄራዎች ኢንስፔክሽን እና ሰርተፊኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶክተር አያሌው ሹመት ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደተናገሩት ፤ በ2014 ዓ.ም በባለፉት 11 ወራት ለውጭ ገበያ ከቀረበው 21 ሺህ ቶን ስጋና የስጋ ተረፈ ምርት 110 ሚሊዮን ዶላር

ባለፉት 11 ወራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ጠንካራና የበለጸገች አገር ለመገንባት ብዝሃነትን ተቀብሉ ጽንፈኝነትን መከላከል እንደሚገባ ተጠቆመ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ጠንካራና የበለጸገች አገር ለመገንባት እያንዳንዱ ዜጋ ብዝሃነትን ተቀብሎ ጽንፈኝነትን መከላከል እንደሚጠበቅበት ተገለጸ።

ትላንት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት "ከጽንፎች መሐል ወርቃማውን አማካይ ፍለጋ" በሚል መሪ ሀሳብ በተዘጋጀው የአዲስ ወግ መርሐግብር ላይ ጽንፈኝነትን መከላከል የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት በመሆኑ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባ ተጠቁሟል።

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጅጌ በዝግጅቱ ላይ ባቀረቡት የውይይት መነሻ ሀሳብ እንደገለጹት፤ አሁን ላይ የኢትዮጵያን የለውጥ መሰረት እውን ለማድረግ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስክ ለውጥ ማምጣት ይገባል።

መንግሥት ባለፉት አራት ዓመታት በጀመራቸው

ጠንካራና የበለጸገች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

## ኢትዮጵያና የዓለም ባንክ 21 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ የዕርዳታ ስምምነት ተፈራረሙ

ገጽ 4


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ

ADAMA STEEL FACTORY

ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር

የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ኮልሞ

0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


ገጽ 9

የፓርላማችን ውሉ ያስታወሰን ቁምነገሮች




## ኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- ኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርታማነታቸውን በእጥፍ በማሳደግ የዜጎችን የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንደሚኖርባቸው የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ገለጸ።

14ኛው አገር አቀፍ የዓለም የኅብረት ሥራ ቀን "ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለተሻለች ኢትዮጵያ" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንትና ተከብሯል።

የኅብረት ሥራ ቀንን አስመልክቶ በተዘጋጀው መድረክ የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ አብዲ ሙመድ እንደገለጹት፤ ኅብረት ሥራ ማህበራት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የግብርና ምርታማነትን በእጥፍ ለማሳደግ ትኩረት አድርገው መስራት አለባቸው።

በኢትዮጵያ በመሰረታዊ ፍጆታ ዕቃዎችንና ዋና ዋና የግብርና ምርቶች ላይ ከፍተኛ የፍላጎት ዕድገት መኖሩን አቶ አብዲ ጠቁመው፤ የፍላጎቱ ማደግ የምርት እጥረት ማስከተሉን ገልጸዋል።

በመሆኑም ፍላጎቱን ለማሟላትና የኑሮ ውድነቱን ለመቋቋም አምራች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከተለምዷዊ የምርታማነት አቅማቸው ፈጥነው በመውጣት ከፍተኛ የግብርና ምርታማነት ለማምጣት ብርቱ ሥራ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

የኅብረት ሥራ ዘርፉ ለሀገራችን ምጣኔ ሃብትና ማኅበራዊ ዕድገት ያበረከተው አስተዋጽኦ ለማሳደግ ጥረት ማድረግ እንደሚገባም ምክትል ኮሚሽነሩ ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ ድሪባ በቀለ በበኩላቸው፤ ኅብረት ሥራ ማህበራት የኢኮኖሚ ቀውስ በሚገጥምበት ወቅት ማህበረሰቡ ችግሩን እንዲቋቋም በግብርናው፣ በኢንዱስትሪውና በአገልግሎት ዘርፉ ላይ ትኩረት አድርገው መስራት እንደሚገባቸው ተናግረዋል።

በሩሲያና ዩክሬን ጦርነት የተነሳ ባጋጠመው የኢኮኖሚ ቀውስ በሰላም ቀጠና ውስጥ ያሉ የግብርና አምራች ሀገራት ሳይቀሩ ስጋት ውስጥ መግባታቸውን ጠቁመው፤ በዚህ ስጋት ምርታቸውን ለውጭ ገበያ ከማቅረብ የተቆጠቡ አገራት መኖራቸውን ገልጸዋል።

በመሆኑ አብዛኛውን የግብርና ምርት በአገር ውስጥ ምርት መሸፈን ስለሚገባ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራ ሥራ እንደሚጠበቅባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

እንደ አቶ ድሪባ ገለፃ፤ እንደ አለምም ሆነ እንደ ሀገር አቀፍ አሁን ለገባንበት ኢኮኖሚያዊ ፈተናዎች ኅብረት ሥራ ማህበራትን የመውጫ ቀዳዳ በማድረግ መፍትሄ የማምጣት እድሎችን መጠቀም ይገባል።

በግብርናው ዘርፍ ያለንን ዕምቅ አቅም አሟጠን በመጠቀም በስንዴ የጀመርነውን ምርታማነት ወደ ሌሎች የምግብ ሰብሎች ማስፋትና ምርትን ከራሳችን አልፈን ኤክስፖርት በማድረግ የወቅቱን ፈተና ወደ ዕድል መቀየር ይገባናል ብለዋል።

ኅብረት ሥራ ማህበራት በቀውስ ውስጥ ተፈጥረው ቀውስን የሚታደጉ ተቋማት መሆናቸው ታሪካዊ ዳራቸው የሚያሳይ መሆኑን የገለጹት አቶ ድሪባ፤ የሃገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራት ቀውስን በዘላቂነት እንዲቋቋሙ ከተፈለገ በቀዳሚነት የአመራርና የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ማዘመን እንደሚያስፈልግ ተገልጿል።

# በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ አደናቃፊ ህጐች እንዲሻሻሉ በመደረጉ በፍትህ ዘርፉ ለውጥ መምጣቱ ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ አደናቃፊ ህጐች እንዲሻሻሉና አዳዲስ ህጐች እንዲወጡ በመደረጉ በፍትህ ዘርፉ ለውጥ መምጣቱን የፍትህና ህግ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የፍትህና ህግ ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር አምባሳደር ደግፌ ቡላ ከትናንት ጀምሮ ለተከታታይ ሁለት ቀን የሚቆይ ለፍትህ አካላት ከፍተኛ አመራሮች ሀገር አቀፍ የስልጠና መድረክ ትናንት መሰጠት ሲጀምር እንደገለጹት፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ በፍትህ ተቋማት ውስጥ ከፍተኛ ችግሮች ነበሩ።እነዚህን ችግሮች ለመፍታትም የፍትህ ተቋማትና ባለሙያዎችን አቅም ከመገንባት አንጻር በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። በተለይ በሀገር አቀፍ ደረጃ አደናቃፊ ህጎች እንዲሻሻሉና አዳዲስ ህጎች እንዲወጡ ተደርጓል።

ለውጡ ከመጣ ወዲህ በመንግሥት በኩል ለህግና ፍትህ አካላት አስፈላጊውን ትኩረት በመስጠት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል ያሉት አምባሳደር ደግፌ፤ የተጠርጣሪዎች አያያዝን በተመለከተ ሰፊ ችግር ነበር፣ የችግሩ መነሻም የህግ ማእቀፉ በመሆኑ ተሻሽሏል። እንዲሁም የሲቪል ማህበራትን ከሥራ ለማገድ ሲያገለግሉ የነበሩ ጨቋኝ ህጎች መሻሻላቸውን ተናግረዋል።

ተቋማት በቻሉት ልክ አሰራራቸውን እንዲያስተካክሉ የተሰሩ ሥራዎች አሉ ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ነገር ግን መንግሥትና ህብረተሰቡ ከሚፈልገው ፍትህ አንጻር የሚፈለገው ውጤት መጥቷል ማለት አይቻልም። በወረቀት የሪፎርም ሥራው ተሰርቷል፣ ነገር ግን ተግባራዊ ለማድረግ ችግሮች በመኖራቸው ተገልጋዩ በሚፈልገው ልክ እርካታ አልመጣም። ተገልጋዩን የሚያረካ ሥራ እንዲኖር እስካሁን የተሰሩ ሥራዎች እንዳሉ ሆኖ በቀጣይ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የፍትህ ሥራ በአንድ ተቋማት ብቻ ተግባራዊ የሚደረግ አይደለም ያሉት አምባሳደሩ፣ የፍትህ ተቋማት በሙሉና የህብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ ነው ብለዋል። ከሰብዓዊ መብት አያያዝ ጋር ተያይዞ ከለውጡ በፊት በማረሚያ ቤቶች ከፍተኛ ችግር ነበር፣ አሁን ከፍተኛ ለውጥ መጥቷል። የህዝቡ የፍትህ ፍላጐት ከፍተኛ በመሆኑ እየመጣ ያለው ለውጥ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አሳስበዋል።

የህግ ባለሙያዎችን አስተሳሰብ ከመቀየር አንጻር ብዙ ሥራ አልተሰራም ያሉት አምባሳደር ደግፌ፣ ለባለሙያዎች



አምባሳደር ደግፌ ቡላ

ስልጠና በመስጠት የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጡ ለማድረግ ይሰራል። እየተሰጠ ያለው ስልጠናም ጥሩ ስነምግባር ያላቸው ባለሙያዎችን በማፍራት በህግ አግባብ እንዲሰሩ ለማድረግ ነው ብለዋል።





# ፋብሪካው 80 ከመቶውን ግብአት ከአገር ውስጥ በመጠቀም የውጭ ምንዛሪ ወጪ እያስቀረ መሆኑን ገለጸ

አዲስ አበባ፡- የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ማስፋፊያ አካል የሆነው ታጠቅ ሲሚንቶ ፋብሪካ ከሚያስፈልገው የድንጋይ ከሰል ግብዓት ውስጥ 80 በመቶውን ከአገር ውስጥ በመጠቀም የውጭ ምንዛሪ ወጪን እያስቀረ መሆኑን ገለጸ።

ፋብሪካው አሁን ላይ በቀን እስከ 20 ሺህ ኩንታል ሲሚንቶ ለገበያ እያቀረበ መሆኑንም አስታውቋል።

በኬሚካልና ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ የታጠቅ ምርትና ኢንጅነሪንግ መምሪያ ተጠባባቂ ኃላፊ አቶ ዳንኤል አጥላው ፋብሪካው በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ላሉ ከተሞች ምርት እንዲያቀርብ ታልሞ መቋቋሙን ገልጸዋል።

በፋብሪካው የሚመረተው ሲሚንቶ ዓለም አቀፍ ደረጃውን ያሟላና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ መሆኑንም አመላክተዋል።

ሲሚንቶን በማምረት ሂደት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ወጪ ለድንጋይ ከሰል ግዥ የሚወጣ በመሆኑ ለምርት አለማደግ ተግዳሮት መሆኑን ጠቁመዋል።

በመሆኑም ፋብሪካው ከሚያስፈልገው የድንጋይ ከሰል ግብዓት ውስጥ 80 በመቶውን ከአገር ውስጥ በመጠቀም ገበያን ለማረጋጋት እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

በቀጣይ የድንጋይ ከሰል ፍላጎቱን በአገር ውስጥ ምርት ለማሟላት እንደሚሰራም ነው የጠቆሙት።

ይህም ለድንጋይ ከሰል የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ከማስቀረት ባሻገር የሲሚንቶ ምርትን ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል።

በሌላ በኩል በአሁኑ ወቅትም ፋብሪካው በቀን 20 ሺህ ኩንታል ሲሚንቶ በማምረት ለገበያ እያቀረበ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ሆኖም የጥሬ እቃ ግብዓት፣ የመለዋወጫ እቃዎችና የኃይል አቅርቦት ችግር በፋብሪካው ሥራ ላይ ተግዳሮት እየፈጠረ መሆኑን ነው የጠቆሙት።

እነዚህና መሰል ችግሮች ከተፈቱለት ፋብሪካው በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርቱን በእጥፍ በማሳደግ የአገሪቱን የሲሚንቶ ፍላጎት ለማሟላት የበኩሉን ሚና እንደሚወጣም አረጋግጠዋል።

የኢትዮጵያ ዓመታዊ የሲሚንቶ ፍላጎት ከ11 ሚሊዮን ቶን በላይ ቢሆንም አሁን ላይ ሁሉም ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ከስምንት ሚሊዮን ቶን ያልበለጠ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ማስፋፊያ አካል የሆነው የታጠቅ ሲሚንቶ ፋብሪካ በ50 ሚሊዮን ዶላር የተቋቋመ ሲሆን የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ከሚያመርተው ምርት 40 በመቶውን ይሸፍናል።

ዜና

# የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎችን ከሽብር ጥቃት ለመከላከል በቅንጅት እየተሠራ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎችን ከሽብር ጥቃት ለመከላከል በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን የኢፌዴሪ ስደተኞችና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት ገለጸ።

የኢፌዴሪ ስደተኞችና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ተስፋሁን ጎበዛይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሽብርተኞችና ተላላኪዎቻቸው የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች ላይ ጥቃት በማድረስ ዓለም አቀፍ ትኩረት ለማግኘት ይሻሉ። ይህን ለመከላከል ከፀጥታና ደህንነት አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው።



አቶ ተስፋሁን ጎበዛይ

ሽብርተኞች በዓለም አቀፍ ደረጃ እና በጎረቤት ሀገራት ጭምር ተመሳሳይ እኩይ ባሕሪ እንደሚያንፀባርቁ የገለፁት ዳይሬክተሩ፤ በኢትዮጵያም በአለፈው አንድ ዓመት በሕወሓት፣ በሸኔ እና በቤኒሻንጉል ታጣቂዎች በሦስት የስደተኛ ጣቢያዎች ላይ ጥቃት ተፈጽሟል ብለዋል።

በበርሃሌ፣ ጉሬሽምቦላና ቶንጎ የሚባሉ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች ላይ ጥቃት ተፈጽሞ ዓለም አቀፍ መነጋገሪያ ሆኖ እንደነበር በማስታወስ ተመሳሳይ ጥቃቶች እንዳይፈጸሙ ከፀጥታና ደህንነት አካላት እንዲሁም ከራሳቸው ከስደተኞች ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑንም አቶ ተስፋሁን ተናግረዋል።

በጣም ስጋት አለባቸው ተብለው የተለዩ የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች በፌዴራል ፖሊስ እንዲጠበቁ መደረጉንና ወደፊትም ያለው የስጋት ደረጃ እየተገመገመ በሚመጥን የፀጥታ አካል እንዲጠበቅ እንደሚደረግ አብራርተዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከስደተኞች ጋር በተያያዘ አንድም የሽብር ጥቃት ተከስቶ የማያውቅበት አንዱ ምክንያት የተቀናጀ ሥራ እየሠራን በመሆኑ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የደረሱ የሽብር ጥቃቶች የሚፈፀሙት ከመረጃ እጥረት ሳይሆን ተቀናጅቶ ካለመሥራት መሆኑን ገልፀው ካለፈው ትምህርት በመውሰድ ከክልል እስከ ፌዴራል ያሉ ተቋማት ሽብርን በመከላከል ዙሪያ ተቀናጅተውና ተናበው እየሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

አብዛኞቹ ስደተኞች ስጋትን ሸሽተው የሚመጡና ዒላማቸውም ሰብዓዊና ማሕበራዊ ድጋፍ ማግኘት ቢሆንም እነዚህን ከለላ በማድረግ ገብተው የሽብር ጥቃት ለመፈፀም የሚያስቡ ስለሚኖሩ ሁሌም ጠንቃቃ የሆነ አሠራር ተዘርግቷልም ብለዋል።

እንደ አቶ ተስፋሁን ገለፃ፤ ኢትዮጵያ የሽብርተኝነት ስጋት ያለባት ሀገርና አሸባሪዎች ዒላማ የሚያደርጓት ሀገር በመሆኗ አሸባሪ ኃይሎች ስደተኞችን ተገን አድርገው ወይም ተመሳስለው በመግባት በስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች ላይ ሕዋሳት እንዳያደራጁ የማድረግ እና የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን ጥቃት በማክሸፍ ላይ ከስደተኞች ጋር ጭምር በመተባበር እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ሽብርተኞች ከስደተኞች ጋር ሰርገው እንዳይገቡ በማድረግ ከድንበር ቁጥጥር ጀምሮ በርካታ ተቋማትን ያሳተፈ የተቀናጀ ሥራ እንደሚሠራ በመጠቆም የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች ላይም በስደተኞች ውስጥ በተፈጠሩ መዋቅሮች የሽብር ጥቃትን በጋራ እየተከላከልን ነው ብለዋል።

በስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች የስደተኛ ማዕከላዊ ኮሚቴ መቋቋሙን፤ ከብሎክ ጀምሮ እስከ መጠለያ ጣቢያ ደረጃ ባሉ መዋቅሮች ይህ አደረጃጀት መፈጠሩንም አቶ ተስፋሁን አብራርተዋል።

በተጨማሪም የስደተኞችን ንቃተ ህሊና በማሳደግ፤ ስደተኞችን ከለላ አድርጎ የሚመጣ የሽብር ጥቃት የመጀመሪያው ገፈት ቀማሽ እነሱ መሆናቸውን በማስገንዘብ በንቃት እንዲሠሩና መረጃዎች ሲኖሩም እንዲጠቁሙ በማድረግ አብረን እየሠራን ነው ያለነው ሲሉም አቶ ተስፋሁን ገልጸዋል።

# የሳንሱሲ -ታጠቅ- ኬላ አስፓልት ኮንክሪት መንገድ ለተጠቃሚዎች ክፍት መሆኑ ተገለጸ

- **የመንገዱ መከፈት ችግራቸውን እንዳቃለለላቸውም ተጠቃሚዎች ተናግረዋል**

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- ከ13 ኪሎ ሜትር በላይ ርዝመት ያለው የሳንሱሲ -ታጠቅ- ኬላ አስፓልት ኮንክሪት መንገድ ለአገልግሎት ክፍት መሆኑን የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አስታወቀ። የመንገዱ መከፈት ችግራቸውን እንዳቃለለላቸውም የመንገዱ ተጠቃሚዎች ተናግረዋል።



ለአገልግሎት ክፍት የተደረገው ሳንሱሲ - ታጠቅ- ኬላ አስፓልት ኮንክሪት መንገድ

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የማዕከላዊ ግንባታ ፕሮጀክት አስተዳደር ፕሮግራም ዳይሬክተር አቶ ኡመር ሁሴን የመንገዱን መከፈት አስመልክቶ በተዘጋጀው የመስክ ጉብኝት ወቅት እንደገለጹት፣ መንገዱ ከመሰራቱ በፊት ከሳንሱሲ ታጠቅ ኬላ ድረስ ለመድረስ ሰዓታት ይፈጅ ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ይህ ችግር ተቀርፎ በደቂቃዎች ውስጥ የሚፈለግበት ቦታ መድረስ ተችሏል።

መንገዱ ጠባብ በመሆኑ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ነበረበት ያሉት አቶ ኡመር፤ በዚህ የተነሳ ህብረተሰቡ ለከፍተኛ የትራንስፖርት እንግልት ተዳርጎ ቆይቷል ብለዋል።

መንገዱ በመገንባት ላይ እያለ ከወሰን ማስከበር ጋር በተያያዙ ችግሮች እንደነበሩ የጠቆሙት አቶ ኡመር፣ ሆኖም አስተዳደሩ ችግሩን በመፍታት መንገዱ እንዲጠናቀቅና ለአገልግሎት እንዲበቃ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

እንደ አቶ ሁሴን ገለጻ ግንባታው ከ825 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት ሲሆን በአጠቃላይ ግንባታው 13.54 ኪሎ ሜትር ርዝመት እና ከ20.5 እስከ 32.5 ሜትር የጎን ስፋት አለው።

መንገዱ የመንገድ አካፋይ ፣እግረኛ መሄጃ መንገድና አቃፊ ትከሻ በግራና በቀኝ እንደተሰራለት ገልጸው የመንገዱ መጠናቀቅ በምዕራብ ኢትዮጵያ የወጪና ገቢ ኮሪደር የነበረውን መጨናነቅ አማራጭ በመፍጠር አመቺ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ያደርጋል ብለዋል።

በአሸዋ ሜዳና ቡራዩ መካከል ለረጅም ጊዜ በሹፍርና ሥራ ላይ የተሰማሩት አቶ ደመቀ ለገሠ እንደገለፁት፤ መንገዱ ከመሰራቱ በፊት ጠባብና ለማሽከርከር አስቸጋሪ እንደነበር ጠቁመው፣ መስመሩ መውጫና መግቢያ በር ከመሆኑ የተነሳ አውቶብስና ተሳቢ መኪና ተጋጭቶ ከአስር ሰው በላይ ሕይወት ያለፈበት አጋጣሚ እንደነበርም ጠቁመዋል።

ሆኖም መንገዱ ተሰርቶ ክፍት መሆኑን ተከትሎ እንደልባቸው መንቀሳቀስ መቻላቸውንና ነዳጅ እንዲቆጥቡ እንዳደረጋቸውም ገልጸዋል።

ቡራዩ ገፈርሳ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ በላይነሽ ድሪብሣ በበኩላቸው መንገዱ ከመሰራቱ በፊት የነበረው ሁኔታ በጣም አስቸጋሪ እንደነበር ይናገራሉ።

ወይዘሮ በላይነሽ እንደሚሉት፤ ገፈርሳ ወንዝ ድልድይ ስለሌለው መንገዱን በማቋረጥ ለትራንስፖርት አስቸጋሪ ነበር። መንገዱ ጠባብ ከመሆኑ የተነሳ አደጋ ይበዛበታል፣ ተማሪዎች በጊዜ ትምህርት ቤት ለመድረስ ይቸገሩ ነበር።

ሆኖም መንገዱ ተሰርቶ ለትራፊክ ክፍት ከሆነበት ቀን ጀምሮ የትራፊክ መጨናነቅ የለም ፣ገፈርሳ ወንዝን ከመንገዱ የሚከላከል ደረጃውን የጠበቀ ድልድይ በመሰራቱ የነበሩ ችግሮች ተቀርፈዋል፤ ወደፈለጉበትም በፍጥነት ለመጓዝ እያስቻለን ነው ብለዋል።

በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩትና ኬላ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ሼክ ሙሐባ ወዓለም መንገዱ ከመሰራቱ በፊት ኮሮኮንች የበዛበትና ለተሽከርካሪ አስቸጋሪ እንደነበር ጠቁመው፤ የመኪናዎች ባሌስትራ በየጊዜው ይሰበር ነበር ብለዋል።

ከዚህም ባሻገር ፤ ከመንገዱ መጥበብና መኪናዎች መብዛት የተነሳ በሰውና በንብረት ላይ በየጊዜው አደጋዎች ይከሰቱ እንደነበር ጠቁመው፤ መንገዱ ከተሰራ በኋላ ችግሮች እየተቀረፉ መሆኑን ጠቁመዋል።

## ሰሞኑን የተከሰተው የዶሮ በሽታ እንዳይዛመት ህብረተሰቡ አስፈላጊውን የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወስድ ተጠየቀ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ እና ቢሾፍቱ ከተሞች ጥቂት የዶሮ እርባታ ሥፍራዎች ላይ ሰሞኑን የተከሰተው የዶሮ በሽታ እንዳይዛመት ህብረተሰቡ አስፈላጊውን የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወስድ የግብርና ሚኒስቴር አሳሰበ።

የበሽታውን መንስኤና ምንነት ለማጥናት የጥናት ቡድን ተቋቁሞ ናሙና እየተሰባሰበ በመሆኑ ውጤቱ ሲታወቅ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል ተብሏል።

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳ ለኢዜአ እንደገለጹት፤ ባሳለፍነው ሳምንት በቢሾፍቱ እና በአዲስ አበባ ከተሞች ውስን የዶሮ እርባታ ቦታዎች የዶሮ በሽታ ተከስቷል።

በሽታው በንክኪ የሚዛመት በመሆኑ በእርባታ ቦታዎች በተወሰኑ ዶሮዎች ላይ ከተከሰተ ሌሎች ዶሮዎችን ሙሉ በሙሉ ስለሚያጠፋ ጥንቃቄ ያሻል ብለዋል።

በሽታው ከተከሰተ ጀምሮ ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንዳይስፋፋ በሽታውን መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችሉ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ገልጸዋል።

የበሽታውን መንስኤና ምንነት ለማጥናትም የጥናት ቡድን ተቋቁሞ ናሙና እየተሰባሰበ መሆኑን ገልጸው፤ ውጤቱ ሲታወቅ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል ብለዋል።

በሚኒስቴሩ የተቋቋመው ግብረ-ኃይል በሽታው በተከሰተባቸው አካባቢዎች ብቻ ተወስኖ እንዲቀር እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

በሽታው እንዳይዛመት እየተወሰዱ ካሉ እርምጃዎች መካከልም ዶሮ አርቢዎች ለተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች እርባታ ከውጭ የሚገባውን የበሽታው መንስኤ እስኪጣራ የለማ እንቁላል ዝውውር መታገዱን ገልጸዋል።

የለማ እንቁላል ሲባል ለዶሮ እርባታ ከውጭ የሚገባ እንጂ ለሰው ምግብ ፍጆታ የሚውል እንዳልሆነ ገልጸዋል።

የተከሰተው በሽታ በቅጡ መቆጣጠርና መከላከል ካልተቻለ በአገር የዶሮ ሀብት ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ ዶሮ አርቢዎችና ሕብረተሰቡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ አሳስበዋል።

በዚህም በሽታውን የመከላከልና የመቆጣጠር እንዲሁም የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ግብረ-ኃይል ተቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱን ገልጸው፤ አሁን ላይ ሥርጭቱና የሞት መጠኑ መቀነሱን ተናግረዋል።

የታመሙ ዶሮዎችን ወደ ገበያ የማውጣት አዝማሚያዎችን በግብረ-ኃይሉ በተሰራ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መሻሻሎች እንዳሉ ገልጸው፤ አሁንም የበሽታው ምንነት እስኪታወቅ ጥንቃቄ እንዲደረግ መክረዋል።

በሽታው ባልተከሰተባቸው ቦታዎች ሌሎች ዶሮዎችን ባለማስገባት እና የራሳቸውንም ወደ ሌሎች ሥፍራዎች ባለማዘዋወር ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

በዚህም በሽታው የተከሰተባቸው አርቢዎች ወደ ገበያ ባለማውጣትና የሞቱ ዶሮዎችንም በመቅበር እንዲሁም በሽታው የተከሰተባቸውን የእርባታ ጣቢያዎች ኬሚካል መርጨት እንደሚገባ ገልጸዋል።

ሕብረተሰቡን ከስጋት እና ሌሎች አርቢዎችን ከጉዳት እንዲሁም አካባቢን ከብክለት ለመታደግ የጋራ ትብብር ይፈልጋል ብለዋል።

በሽታው በሰው ጤና ላይ ያደረሰው ጉዳት እስካሁን ባይኖርም ሕብረተሰቡም በዶሮ እና በዶሮ ውጤቶች አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸዋል።

ሚኒስቴሩ በጉዳዩ ላይ ከኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ እየሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

በሽታው እስካሁን በሰዎች ላይ ያደረሰው ጉዳት ባይኖርም ሚኒስቴሩ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የተንቀሳቀሱ ዶሮዎች ስለሚኖሩም ለጊዜው የዶሮ እንቅስቃሴ መገደብ የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ገልጸዋል።

በየእለቱ ያለውን ሁኔታ እና የጊዜ ገደቡ የሚነሳበትን ወቅት ለመወሰን የሚያጣራ ኮሚቴ መዋቀሩን ገልጸዋል።

በዶሮዎች ላይ የህመም ምልክት ካጋጠመ ዶሮ እና የዶሮ ውጤቶችን ለገበያ ባለማቅረብ ሊደርስ የሚችል ጉዳትን ለመቀነስ ማኅበረሰቡ ቀና ትብብር እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

ዜና

## ጠንካራና የበለጸገች...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

የሪፎርም ሥራዎች በአገሪቱ ፖለቲካዊ ቅኝት ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት መፍትሔ ማምጣት ላይ እየሰራ መሆኑንም የጠቆሙት አቶ ተስፋዬ ለዚህ ስኬታማነት ደግሞ ሁሉም ዜጋ ሊረባረብ ይገባል ብለዋል።

አቶ ተስፋዬ እንደገለጹት፤ የአገሪቱ ዋናው ችግር ከ1960 ዎቹ ጀምሮ እያደጉ የመጡ ፖለቲካዊ ስብራቶች ሲሆኑ በዚህም ጽንፈኝነትና አክራሪነት ገኖ የወጣበት እንደሆነ ጠቁመዋል።

በዚህም መነሻነት የፖለቲካ ባህላችን መለወጥ እንዳለበት የሚያምነው የብልጽግና ፓርቲ፣ የፖለቲካ እይታን ከተቃዋሚ ወደ ተፎካካሪ በመለወጥ ጽንፈኝነትን ለማስወገድ ሰርቷል ብለዋል።

ቀደም ባሉ ጊዜያት የሀሳብ ልዩነት የሚፈታው በግጭት፣ በጦርነትና አውዳሚ በሆነ መንገድ መሆኑ ብዙ ጉዳቶች አስከትሏል ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ አሁን ላይ የመንግሥት ቁርጠኛ አቋም የሀሳብ ልዩነቶችን በድርድር፣ በውይይትና በሀሳብ የበላይነት መፍታት ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ተስፋዬ ገለፃ፤ በብሔርም ሆነ በሃይማኖት የሚከሰቱ የጽንፈኝነት አስተሳሰቦች የሚመነጩት ተገልግያለሁ አልያም ተበድያለሁ ከሚል እሳቤ ነው።

ነገር ግን ያለፉ ቁርሾዎችን ነቅሶ በማውጣት ከመነታረክ ይልቅ የትናንትን የታሪክ ቁርሾ በእርቅና በሰላም በመፍታት ወንድማማችነትን መሰረት ያደረገ አገራዊ አንድነት መገንባት ላይ ሁሉም ትኩረት ሊያደርግ እንደሚገባ የገለፁት አቶ ተስፋዬ፤ ኢትዮጵያ የሁላችንም፣ ለሁላችንም የምትበቃ አገር በመሆኗ እና ጽንፈኝነት አገርንና ሕዝብን የሚጎዳ በመሆኑ ሊወገድ እንደሚገባም ገልጸዋል።

ሌላው የውይይት መነሻ ሃሳብ ያቀረቡት የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዷለም እንደገለጹት፤ በአገሪቱ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ የምርጫ ጉዳይ አይደለም። ጽንፈኝነትን ለመከላከል መንግሥት ህግ ከማስከበር ጀምሮ ልዩነቶችን በምክክርና በውይይት እንዲፈቱ በትኩረት እየሰራ ነው። ጽንፈኝነትን ለመከላከልና ወርቃማውን አማካኝ ለመፈለግ ከምልክቶች ይልቅ ዋናው የችግሩን መነሻ ለመፍታት መስራት ላይ አጽንኦት ተሰጥቶበታል። ለዚህም ብዝሃነትን ተቀብሎ በአግባቡ በማስተናገድ ጽንፈኝነትን ቦታ ማሳጣት ይገባል።

ጽንፈኝነትን በማዳከም ወደ ወርቃማው አማካይ ለመምጣት ተቋማት በገለልተኝነት ሕዝብን እንዲያገለግሉ እየተሰራ ነው ያሉት አቶ ብናልፍ፤ ጠንካራ የሆኑ የደህንነት፣ የፍትህ፣ የጸጥታ ተቋማት በላቀ ደረጃ መገንባት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል። የችግሮች መፍቻ ድርድር፣ ውይይትና በሀሳብ የበላይነት ማመን በመሆኑ ‹‹እኔ ብቻ›› የሚለውን በመተው ሁሉም አሸናፊ ሆኖ በሰላም በጋራ ወደሚኖርበት መንገድ መምጣት ይገባል ብለዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በበኩላቸው ባቀረቡት የመነሻ ሃሳብ፣ ተቃርኖ የሰው ልጅ አንዱ አካል ነው ብለዋል።

“በአንድ አገር ‘የእኔ ብቻ’ ማለት አይቻልም፤’የእኛ’ የሚባል እንዳለ በመገንዘብ ‹‹የእኛ በሚለው እሳቤ ውስጥ የእኔም ድርሻ አለበት ብሎ መውሰድ አስፈላጊ ነው ያሉት አምባሳደር ሬድዋን፤ አሁን በአገሪቱ ላይ የደህንነት ችግር ሆኖ የሚመጣው በተቃርኖዎች መሃል የሚመጣው ችግር ነው ብለዋል።

በመሆኑም ችግሮችን ለመፍታት መንግሥት ዋናውን ድርሻ ቢወስድም ሁሉም ዜጋ ኃላፊነት እንዳለበት በመነሻ ሃሳባቸው አጽንኦት ሰጥተዋል።

ከትናንት ጠቃሚውን ታሪክ ወስዶ የማይጠቅመውን መተው ላይ ማተኮር አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ ሬድዋን፤ ሁላችንም የምንጋራው ታሪክ ስላለን በትናንትና እና በዛሬ ላይ ቆሞ ነገን አሻግሮ በማየት እጃችን ላይ ያለውን ዕድል መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል።

በአዲስ ወግ ውይይት ላይ የተሳተፉ ምሁራን ችግሮችን ለመፍታት በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ያሉ ችግሮችን መፍታት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ አንቂዎች፣ ፖለቲከኞችና ሌሎች ዜጎች ደግሞ ልዩነትን በአግባቡ በመረዳት እና አንዱ ለአንዱ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ሁሉም በትብብር ሊሰራ ይገባል ብለዋል።

# ኢትዮጵያና የዓለም ባንክ 21 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ የዕርዳታ ስምምነት ተፈራረሙ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና የዓለም ባንክ ለከርሰ ምድር ውሃ ልማትና የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ጫና ለመቋቋም የሚረዳ 21 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ የዕርዳታ ስምምነት ተፈራረሙ።



ኦስማን ዲዮን እና አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው፤ በኢትዮጵያና በዓለም ባንክ መካከል የተፈረመው የዕርዳታ ስምምነት በአጠቃላይ 405 ሚሊዮን ዶላር ወይም ከ20 ቢሊዮን 987 ሚሊዮን 99 ሺህ ብር በላይ ነው።

ከዚህ ውስጥ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ያሳደረውን ጫና ለመቋቋም የሚውለውን ከ10 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ የዕርዳታ ስምምነት በገንዘብ ሚኒስትር አቶ አህመድ ሺዴና በዓለም ባንክ የኢትዮጵያ፣ የኤርትራ፣ የሱዳንና የደቡብ ሱዳን ዳይሬክተር ኦስማን ዲዮን መካከል ትናንትና ተፈራርመዋል።

የከርሰ ምድር የውሃ ሀብትን ለማልማት የሚውለውን ከ10 ቢሊዮን 882 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነው የዕርዳታ ስምምነት ደግሞ በበይነ መረብ በተከናወነ ሥነ ሥርዓት (Electronic Signature and agreement) ነው የተፈረመው።

ስምምነቱንም የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴና በዓለም ባንክ ከሰሀራ በታች የመካከለኛው ምስራቅና የሰሜን አፍሪካ ክፍለ አህጉራዊ ትብብር ዳይሬክተር ሚስ ቡዜና ጉርማዚ ፈርመዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሺዴ በዓለም ባንክ አማካኝነት ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመቋቋም የሚደረገውን ድጋፍ የዕርዳታ ስምምነትን በፈረሙበት ወቅት እንደገለጹ፤ ወረርሽኙ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚው ላይ ያሳደረውን ጫና ለመከላከል የሚውለው ዕርዳታ በጤናው ዘርፍ የሚከናወኑ ሥራዎችን ለማገዝ ይረዳል።

የፋይናንስ ድጋፉ በተለይም በኮቪድ-19 ስትራቴጂክ ዝግጁነትና ምላሽ ዕቅድ የኢትዮጵያ ኮቪድ-19 የድንገተኛ ጊዜ ምላሽ ፕሮጀክት ለሚያከናውናቸው ተግባራት የሚውል ሲሆን፤ የድጋፉ ዋነኛ ዓላማ ለኮቪድ 19 ክትባት ግዥ የሚውል ከመሆኑም በላይ ክትባቶች በተመጣጣኝና ፍትሃዊ ሁኔታ ተደራሽ እንዲሆን ይረዳል ብለዋል።

የገንዘብ ዕርዳታው ብሔራዊ የክትባት አሰጣጥ ስርዓትን በተከተለ መንገድ የጤና ተቋማት ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ ወገኖች ከክፍያ ነፃ የሆነ አገልግሎት እንዲሰጡ ያስችላቸዋል ሲሉ አስረድተዋል።

በተመሳሳይ በኢትዮጵያና በዓለም ባንክ መካከል የተፈረመውና ለከርሰ ምድር የውሀ ሀብትን ልማት የሚውለው የዕርዳታ ስምምነት ከኢትዮጵያ በተጨማሪ የአፍሪካ ቀንድ አገራት በሆኑት ሶማሊያና ኬንያ ተግባራዊ ለሚደረገው የከርሰ ምድር ውሀ ልማትና አስተዳደር የሚውል መሆኑ ተገልጿል።

የፕሮጀክቱ የመጀመሪያው ምዕራፍ ሶስቱን የአፍሪካ ቀንድ ሀገራን ጨምሮ የምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግሥታትን (IGAD) የሚያሳትፍ መሆኑን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታውቋል።

የዕርዳታ ስምምነቱ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በ67 ወረዳዎች ለሚያካሂደው የከርሰ ምድር ውሀ ልማት ፕሮጀክት ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን ተጠቁሟል።

ከዚህ ባለፈ የፋይናንስ ድጋፉ በኢትዮጵያ ቅድሚያ በተሰጣቸው 55 ወረዳዎች ላይ የከርሰ ምድር ውሃ ልማት ለማከናወን ከመርዳቱ ባለፈ በቦረና ዞን አራት ወረዳዎች ላይ በሚካሄደው የከርሰ ምድር ውሃ ልማትና የአነስተኛ የመስኖ ልማትም እንደሚውል ሚኒስቴሩ አስታውቋል።

## በቱሪዝም ዘርፍ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ከ1960ዎቹ ጀምሮ ቢሆንም ለዘርፉ በቂ ትኩረት ባለመሰጠቱ አንዴ ከባህል ሌላ ጊዜ ከስፖርት ጋር በጥምር ሲመራ የቆየበት ሁኔታ ነበር።

በአሁኑ ጊዜ መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ተቋሙ ራሱን ችሎ በሚኒስቴር ደረጃ ከመዋቀሩም ባሻገር በኢኮኖሚው ዘርፍ ትኩረት ከተሰጣቸው አምስት ዘርፎች አንዱ እንደሆነም አምባሳደር ናሲሴ ጠቁመዋል።

የቱሪዝም ዘርፍ በዓለም ደረጃም ቢሆን በተለይ በኢኮኖሚው መስክ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ነው ያሉት አምባሳደር ናሲሴ፣ በተለይ ከኮሮና ወረርሽኝ መከሰት በፊት ዘርፉ ትልቅ እመርታ እያሳየ እንደነበር ጠቁመዋል። ለአብነትም እአአ በ2015 ዓ.ም አንድ ቢሊዮን ቱሪስት አንድ ቢሊዮን እድሎች በሚል የተካሄደው የንቅናቄ ዘመቻ ማሳያ ነው ብለዋል።

የቱሪዝም ዘርፍ በዓለም ላይ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ያለው አስተዋፅኦ አስር በመቶ መድረሱን የጠቆሙት አምባሳደሯ፤ በዓመት አንድ ነጥብ ሶስት ትሪሊዮን ዶላር ገቢ እያስገኘና ለ334 ሚሊዮን ሰዎች የሥራ እድል እየፈጠረ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በዓለማችን በየዓመቱ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ሰዎች ከቦታ ቦታ እንደሚዘዋወሩ የተናገሩት አምባሳደር ናሲሴ፣ ከዚህ ውስጥ ግን የአፍሪካ ድርሻ በተለይ የኢትዮጵያ በጣም ዝቅተኛ ነው ብለዋል።

በዚህ የተነሳ ከዚህ ዘርፍ የሚገባንን ጥቅም ለማግኘት መንግሥት ትልቅ ትኩረት በመስጠት እየሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ ከዚህ አንጻር በዘርፉ መሰረተ ልማትን ማስፋት አንዱ የትኩረት አቅጣጫ እንደሆነ ገልጸዋል።

በዚህም መሰረት በዘርፉ በተሰራው የሪፎርም ሥራ በዘርፉ ያለውን አቅም የመፈተሽ እና ይህን እንዴት አድርጎ የብልጽግና መሰረት ማድረግ እንደሚቻል መፈተሹን ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል በሀገራችን የቱሪዝም ዘርፉ በመጀመሪያ በኮቪድ አማካኝነት ጉዳት የደረሰበት ሲሆን በመቀጠል ደግሞ በተከሰቱት የፀጥታ ችግሮችና የሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ለበለጠ ጉዳት ተዳርጎ መቆየቱን ሚኒስትሯ ጠቅሰዋል።

እንደ አምባሳደር ናሲሴ ገለፃ፤ በኢትዮጵያ ትልቅ የቱሪዝም ሀብት አለ፤ የፖሊሲ ማሻሻያዎችም እየተካሄዱ ነው፤ የመንግሥት ኢንቨስትመንት እና የግሉም ዘርፍ ኢንቨስትመንት እያደገ ይገኛል፤ ገበታ ለሀገር እና ገበታ ለሸገርን የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎችም ለዘርፉ መነቃቃት ትልቅ አቅም እየሆኑ ነው፤ እነ ጎርጎራ፤ ወንጪ፣ እንጦጦ እና ኮይሻን የመሳሰሉ የቱሪስት መዳረሻዎች እየተጠናከሩ ነው፤ እነዚህ ሁሉ ለዘርፉ እድገት ትልቅ አቅም ናቸው።

ከዚህ በመነሳትም ኢትዮጵያ በአሥር ዓመቱ የልማት እቅዷ የቱሪስት ፍሰቱን ወደ ሰባት ሚሊዮን ለማድረስ እና በአጠቃላይ 23 ቢሊዮን ብር ገቢ ከዘርፉ ለመሰብሰብ እየተሰራ እንደሆነ ሚኒስትሯ ጠቁመዋል።

በዚህ የተነሳ በቀጣይ የቱሪዝም ሀብቶቻችንን በአግባቡ የማልማት፤ የቱሪዝም መሰረተ ልማትን የማስፋፋት፣ መስህቦችና ምርቶችን በአግባቡ የማስተዋወቅ፣ የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን የማስፋፋት እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን የማሳደግ ሥራ በትኩረት እንደሚሰራ አምባሳደር ናሲሴ ጠቁመዋል። ለዚህም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ጠይቀዋል።

## ባለፉት 11 ወራት...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ገቢ ተገኝቷል። በበጀት ዓመቱ ከስጋና የስጋ ተረፈ ምርት የተገኘው ገቢ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ብልጫ አሳይቷል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ ፤ በ2013 ዓ.ም ወደ ውጭ ገበያ የተላከው ስጋና የስጋ ተረፈ ምርት በአጠቃላይ 15 ሺህ 800 ቶን ተልኮ 79 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል። በዘንድሮ በጀት ዓመት የተገኘው ገቢ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከ31 ሚሊዮን በላይ ልዩነት አለው። ይህ ገቢ የውጭ ምንዛሪ በሀገራችን ኤክስፖርት ቁራ ከተጀመረ ጀምሮ በታሪክ ተመዝግቦ የማያውቅ ነው።

በ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት በ11 ወራት ለተመዘገበው ውጤት መሠረቱ ለጥራትና ደህንነት የተለየ ትኩረት መስጠቱ መሆኑን የገለጹት ዶክተር አያሌው ፤ “ ከጥራትና ደህንነት ጋር ተያይዞ የነበሩ ችግሮችን መፈታት የሀገራችን ምርት በውጭ ሀገራት ዘንድ ተፈላጊነቱ በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር አድርጓል ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛ ቢሆንም፤ ሀገሪቱ ያላት አቅም ከመጠቀም አኳያ እጅግ በጣም ብዙ የሚቀሩ ሥራዎች መኖራቸውን ገልጸዋል።

በተለይ የእንስሳት ዕርባታ፣ አቅርቦትና የገበያ ሥርዓቱን ማሻሻል ቢቻል ለውጭ ገበያ በዓመት 300 ሺህ ቶን ስጋና የስጋ ተረፈ ምርቶችን መላክ የሚያስችል አቅም መኖሩንም ገልጸዋል። ይህም ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማስገኘት የሚያስችል እንደሆነም ዶክተር አያሌው አብራርተዋል።

ሀገራችን 42 ነጥብ 9 ሚሊዮን በግ 52 ነጥብ 5 ሚሊዮን ፍየል፤ 70ነጥብ2 ሚሊዮን የቀንድ ከብት እና ስምንት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ግመል (CSA, 2020/21) በመያዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ በቀንድ ከብት ብዛት አምስተኛ እንዲሁም ፤ ከአፍሪካ አንደኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። በተጨማሪም በበግና በፍየል ብዛት ደግሞ ዘጠነኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ኢትዮጵያ ከፍተኛ የእንስሳት ቁጥር ቢኖራትም ተጠቃሚነቷ ካላት ሀብት አኳያ እዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነ ይታወቃል።

የቅዳሜ መጽሄት

# አገልግል



## «እርስ በእርስ ባለመግባባት ከድህነት የምንወጣበትን ጊዜ ልናራዝመው አይገባም»

- ኢንተርናሽናል ሼፍ አንተነህ ድፋባቸው

ገጽ 6



‹‹ውሎዬ ከማሳ፣ አዳሬም ከአይሱዙ ላይ ነው››

- ቃልኪዳን ጠብቀው

ገጽ 13



## የእሳት ልጅ አመድ ሳስመባል - ስምን የመቀየር ፍልሚያ

ገጽ 16

### ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## በግብር ከፋዮች የግብር ማሳወቂያ የሂሳብ መዝገቦች ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና መፍትሔዎቻቸው

ለአንድ ሀገር ልማትና እድገት ከዜጎች የሚሰበሰበው ግብር በተለያዩ የሀገሪቱ የልማት ዘርፎች ላይ ስለሚውል ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ ግብር መክፈል የዜግነት ትልቁ ግዴታ ነው፡፡ ከዜጎች የሚሰበሰበው ግብር ነው ተመልሶ ለመንግሥት ተቋማት፣ ለሠራተኛው ደመወዝ፣ ለጤና፣ ለትምህርት፣ ለግብርናው ዘርፍ፣ ለሀገር መከላከያና ለፖሊስ፣ ለሀገሪቱ ጸጥታና ደህንነት ጥበቃ ወ.ዘ.ተ የሚውለው፡፡ ግብር የሀገር ሕይወት፤ አቅምና ጉልበት ነው፡፡ ዜጎች ወቅቱን ጠብቀው ግብር ካልከፈሉ ሀገራዊ ሥራዎችን የመሥራት አቅም እንዲሁም የእድገትና የልማት ሕልሞችና ትልሞችን የማሳካት አቅም አይኖረንም፡፡

ግብር አንድ መንግሥት እንደ መንግሥት ትልቁን ሥራውን ለመከወን የሚያስችለው የፋይናንስ አቅም የሚያገኝበት የሀገር ውስጥ ገቢ ነው፡፡ ታዲያ በርካታ ሀገራዊ የልማት ሥራዎች የሚከናወኑት፣ በጀት የሚወጣላቸው፣ በእቅዱም መሠረት ወደ ሥራ የሚገባው ከሕዝቡ በሚሰበሰበው ግብር ነው፡፡ ከውጭ ለተለያየ የልማት ሥራዎች ከሚገኘው ብድርና እርዳታ ውጪ የየትኛውም ሀገር መንግሥት ዋነኛ የገቢ ምንጩ በሀገር ውስጥ የሚሰበሰበው ግብር ነው፡፡

ስለዚህ ዜጎች በግብር በኩል ያለባቸውን ሀገራዊ ኃላፊነት በውል ተገንዝበው በወቅቱ ሲከፍሉ ለሀገራቸው ልማትና እድገት የበኩላቸውን ከፍተኛ ድርሻ እንደተወጡ በማመን ሊኮሩበት ይገባል፡፡ በመሆኑም ግብር መክፈል የዜግነት ግዴታም፤ ክብርም ነው፡፡ ሆኖም ሀገራዊ የግብር አሰባሰብ ሥርዓቱ ለዘመናት ኋላቀር በሆነ መንገድ ሲከናወንና ሳይዘምን ቆይቷል፡፡ ታዲያ በተለይ በሀገሪቱ ከመጣው ለውጥ በኋላ የአገሪቱን የግብር ሥርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ከማዘመን ባለፈ በመንግሥት በኩል ከመዋቅር ጥናት ጀምሮ የአደረጃጀት ለውጥ በማድረግ ግብር ከፋዩ ሕዝብ በተለይም ነጋዴው በሒሳብ አያያዝና በመሳሰሉት



አቶ ዘገየ በላይነህ፤



አቶ ጌታቸው ግርማ፤



የውይይቱ ተሳታፊዎች፤

ሰፊ ግንዛቤና ስልጠናዎችን እንዲያገኝ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ እየተደረጉም ይገኛሉ፡፡

ከዚህ አኳያ በግብር ማሳወቂያ ወቅት የሂሳብ መዝገብ መያዝ የሚጠበቅባቸው ግብር ከፋዮች በራሳቸው ፈቃድ የሚያዘጋጁቸው የሒሳብ መዝገቦችና ተያያዥ የሒሳብ መግለጫዎች ለገቢ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ለግብር ማሳወቂያነት በሚያቀርቡበት ጊዜ የሚስተዋሉ ክፍተቶች ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ለማስቻል እንዲሁም ግብር ከፋዮች ግብራቸውን ለማሳወቅ ወደ ግብር ሰብሳቢ ተቋማት ሲያመሩ ሊደረግላቸው ስለሚገባ መስተንግዶ ዙሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ከሰሞኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሂዷል፡፡

የውይይት መድረኩን በቢሮው የታክስ ጉዳዮች ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘገየ በላይነህ መርተውታል፡፡ እርሳቸውም፤መድረኩ ግብር ከፋዮች በራሳቸው ፈቃድ የሚያዘጋጁቸው የሒሳብ መዝገቦችና ተያያዥ የሒሳብ መግለጫዎች ለገቢ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ለግብር ማሳወቂያነት በሚያቀርቡበት ጊዜ የሚስተዋሉ ክፍተቶች ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ለማስቻልና ለቀጣይ አፈጻጸም መፍትሔ የሚፈልጉ ጉዳዮችን በመፈተሽ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ለማስቀመጥ ታስቦ የተዘጋጀ መድረክ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

አቶ ዘገየ አክለውም ለከተማችን ብሎም ለሀገራችን እድገትና ብልጽግና ካላቸው ተቆርቋሪነት በመነሳት “ለሀገሬ የሚጠበቅብኝን ግብር በወቅቱ መክፈል አለብኝ” በሚል ወደ ቢሮው ለመስተናገድ የሚመጡ ግብር ከፋዮችን የተሳለጠና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ማርካት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በሌላ በኩል በመድረኩ በግብር ከፋዮች የጥሬ ገንዘብ ግብይትና የሒሳብ መዝገብ አያያዝ ዙሪያ የተዘጋጀውን ሰነድ ያቀረቡት በቢሮው የታክስ ኦዲት ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ግርማ በበኩላቸው እንደመዲናዋ ከሚሰበሰበው ገቢ ውስጥ 85 በመቶ የሚሆነውን የሚሰበስበው ከደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋዮች እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

ግብር ከፋዮቹ ግብር የመክፈል ግዴታቸውን እንዲወጡ የሚፈለገው ራሳቸው አዘጋጅተው በሚያቀርቡት ግብር ወይም ታክስ ማሳወቂያ የሂሳብ መዝገቦችና ተያያዥ የሒሳብ መግለጫዎች መሠረት ያደረገ የራስ ታክስ ስሌት እንደሆነ ዳይሬክተሩ አቶ ጌታቸው ጠቁመው፤ ይህም በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተና ግብር ከፋዮች የራስ ታክስ ስሌት ለማዘጋጀት ግንዛቤ ሊኖራቸውና ለግብር ታማኝ መሆን እንደሚገባቸው ሰነዱን ባቀረቡበት ወቅት ገልጸዋል፡፡

በመድረኩ የቀረበውን ሰነድ መሠረት በማድረግ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን፤ በቀጣይ መደረግ ያለባቸው ተግባራት፣ የሒሳብ መዝገብ የሚይዙ ግብር ከፋዮች ላይ የጥሬ ገንዘብ አመዘጋገብና አስተዳደር ዙሪያ የሚስተዋሉ ክፍተቶች እንዲታረሙና በቀጣይ የተሻለ ጥራት ያለው የሒሳብ መዝገብ አያያዝ እንዲኖር መሰረት መጣል ተገቢ እንደሆነም መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

**አድራሻ፡-**

ስልክ የቢሮ ኃላፊ 0115575790
የጽ/ቤት ኃላፊ 0115575741
የሞ/ኮ/ስ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575748
የታ/ጉ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575608
የህግ ማ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575604
Facebook page: Addis Ababa revenue bureau
Web site: http//aarevenue.gov.et
P.O. Box 27400 code 1000

**የላቀ ገቢ ለአዲስ አበባችን ብልፅግና!**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «እርስ በእርስ ባለመግባባት ከድህነት የምንወጣበትን ጊዜ ልናራዝመው አይገባም»

- ኢንተርናሽናል ሼፍ አንተነህ ድፋባቸው

ማህሌት አብዱል



የዛሬው የዘመን እንግዳችን ከጉልበት ሰራተኝነት ተነስቶ ዓለምአቀፍ ሼፍ መሆን የቻለ ወጣት ነው። ትውልዱም ሆነ እድገቱ አዲስ አበባ በተለምዶ የካ ሚካኤል በግ ተራ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን የተማረው አሁን ላይ በፈረሰው ዘርፈሽዋል ትምህርት ቤት ሲሆን፣ በምስራቅ አጠቃላይ እና በኮከበፅባህ በተባሉ ትምህርት ቤቶች ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ተከታትሏል፡፡

ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ካላቸው ቤተሰቦች የተፈጠረው ይህ ወጣት፣ የልጅነት ጊዜውን ያሳለፈው በተለይ በመንግሥት ተቋማት ውስጥ በጽዳት ባለሙያነት የሚሰሩትን እናቱን በማገዝ ነው፡፡ እንደ ልጅ መጫወት ሳያምረው ከማጀት እስከ ደጅ የእናቱ ምርኩዝ በመሆን ኑራቸውን ለመለወጥ ሲል የተለያዩ ሥራዎችን ሠርቷል፡፡ ገና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ ሳለ ጀምሮ፣ በሸክም እና በሌሎችም የጉልበት ሥራዎች ላይ ከመሣተፍ በተጨማሪ በግለሰቦች ቤት በቤት ሰራተኝነት ሳይቀር ተቀጥሮ በመስራት የእናቱን የኢኮኖሚ ቀዳዳ ለመሸፈን፣ ትምህርቱን ለመማር ብዙ ዋጋ ከፍሏል፡፡

ገና በለጋ እድሜው ሕይወት ክፉ ፊቷን የሰጠችው እንግዳችን ከቅርብ ዘመድ አዝማድ ጀምሮ ብዙ መገፋትንና መናቅንን ጭምር እያስተናገደ አድጓል፡፡ በልጅነት ጫንቃው የተሸከማቸው ተደራራቢ ችግሮች በትምህርቱ ዘልቆ እንዳይሄድ ገድበውታል፡፡ በዚህ ተስፋ ሳይቆርጥ፣ ከአንድ ጓደኛው ጋር በመሆን ከሰው ያገኙትን 300 ብር ይዘው ዶሮ እርባታ ጀመረ፡፡

ዶሮዎቹ ደህና ማደግ ሲጀምሩ በሌሊት አውሬ በልቶ ጨረሰበት፣ ልፋቱ መና ቀረ፡፡ ለችግር እጅ መስጠት የማያውቀው ይህ ሰው ግለሰቦች ቤት በመቀጠር ምግብ ከማብሰል ጀምሮ ልብስ እስከማጠብ ድረስ እየሰራ በሚያገኛት ገንዘብ እናቱንና ራሱን መደጎም ያዘ፡፡ ኬክ ቤት ተቀጥሮ ዳቦ መጋገር ለመደ፡፡ ቀጠለና አንድ የግል ኮሌጅ በመግባት በምግብ ዝግጅት ዲፕሎማውን አገኘ፡፡ በተማረበት ሙያ ተቀጥሮ ከመሥራት ጀምሮ የራሱን ሬስቶራንት እስከመክፈትና ቀጥሮ እስከማሠራት ደረሰ፡፡

ይሁንና የእንግዳችን ውጣ ውረድ አላበቃም፣ የከፈታት ሬስቶራንት ትርፋማ ሆና መቀጠል አልቻለችም። ህልውናዋን ለማቆየት ሲል ብዙ ተንገታገተ፡፡ በመጨረሻ ግን ለስደት እጁን ሰጠ፡፡ በስፔናውያን ወዳጆቹ የቀረበለትን የጉብኝት ጥያቄ ተቀብሎ ስፔን ዘለቀ፣ ቀጠለናም ወደ ጀርመን አቀና፡፡ መንገዶቹ ግን አሁንም አልጋ በአልጋ አልነበሩም፣ በሰው ሀገር ማደሪያ ከማጣትና በካምፕ አስከፊ ኑሮን በመምራት ጭምር ሕይወቱን ገፋ፡፡

የጀርመን ነዋሪነት መታወቂያውን ካገኘ በኋላ ግን እድል በሯን ከፈተችለት፡፡ ቋንቋቸውን ትምህርት ቤት ገብቶ ተማረ፡፡ በሀገሩ ያገኛትን የምግብ ሥራ ሙያ እስከ ዓለምአቀፍ ሼፍ የሚያደርገውን ዲፕሎማ አገኘ፡፡ አሁን ላይ በጀርመን ስመጥር ከሆኑ ባለአምስት ኮከብ ሆቴሎች መካከል በአንደኛው በሼፍነት ተቀጥሮ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የዛሬው የዘመን እንግዳችን ኢንተርናሽናል ሼፍ አንተነህ ድፋባቸው ኮረና የሰጠውን የእረፍት ጊዜ በመጠቀም በሕይወት ዘመኑ ያሳለፈው ውጣ ውረድ ፣ ማጣት ማግኘት ለሌሎች ጥሩ አስተማሪ ትሆናለች ብሎ በማሰብ በመፅሃፍ መልኩ ሰንዶ በማዘጋጀት «ስደተኛው ሼፍ» በሚል ርዕስ ለአንባቢያን አድርሷል፡፡ በኢትዮጵያ ታላላቅ ሃያሲያን እጅ ያረፈባት ይህችው መፅሃፍ በአንባቢያን ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ጊዜ አልወሰደባትም፡፡ ከጠበቀው ጊዜ ፈጥናም የመጀመሪያው ዙር ህትመት ሙልጭ ብሎ ተሸጠለት፡፡ በቅርቡ ደግሞ ይህችኑ መጽሐፍ በጀርመንኛ ቋንቋ በማስተርጎምና በማሳተም ዓለምአቀፉን የገበያ መረጃ መረብ አማዞንን መቀላቀል ችላለች፡፡ በቅርቡ ደግሞ ወደ እንግሊዝኛ በመተርጎም እንዲሁም በሆቴል ኢንዱስትሪው ዙሪያ የሚያትት ሌላ አዲስ መጽሐፍ በማስተርጎም ለአንባቢያን ለማድረስ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡ እንግዳችን በሕይወት ውጣ ውረዱና በሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እስቲ ስለአስተዳደግህ አጫውተንና ውይይታችን እንጀምር?**

**ኢንተርናሽናል ሼፍ አንተነህ፡-** አባቴ የቀድሞ ሠራዊት አባል የነበረ ሲሆን እናቴ ደግሞ በአንድ የመንግሥት መስሪያ ቤት ውስጥ በጽዳት ሰራተኝነት ታገለግል ነበር። እኔም ያደኩት በጣም ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች በመሆኑ ያደኩት በድህነት ነው። በዚህ ምክንያት የልጅነት ሕይወት ለእኔ ቀላል አልነበረም፡፡ ፈተናውና ችግሩ የሚጀምረው ይህችን ዓለም ከተቀላቀልኩበት እለት ጀምሮ ነው፡፡ በተለያዩ መድረኮች ላይ እንደተናገርኩት እንደሰው ለመኖር ስል ብቻ ብዙ ፈተናዎች ገና በጨቅላ እድሜዬ ተጋፍጫለሁ፡፡

የቤተሰቡ የመጨረሻ ልጅ ብሆንም ወድቆብኝ የነበረው ብዙ ሃላፊነት ነበር፡፡ ብዙ ጊዜዬን የማጠፋው እናቴን በመርዳት ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ትምህርቴን በአግባቡ መከታተል አልቻልኩም ነበር። እውነቱን ለመናገር አሁን ላይ ያለሁበት ደረጃ ለመድረስ ከእድሜዬ በላይ ብዙ ዋጋ ከፍያለሁ። ከልጅነቴ ጀምሮ ራሴን ለመቻል ብዙ ዝቅተኛ ሥራዎችን ሞክሪያለሁ፡፡ ይሁንና እነዚህ ሥራዎች እንደኪሣራ ሳይሆን የምቆጥራቸው የሕይወት መንገዴ አድርጌ ነው፡፡ ከቀን ሥራ ጀምሮ ፤ ሰው ቤትም በቤት ሰራተኝነት ተቀጥሬ አውቃለሁ፡፡ በተለይ በቀን ሥራ የሠራሁት ለረጅም ጊዜ ነው፡፡

አያት የመኖሪያ መንደር ሲገነባ በቀን ስድስት ብር እየተከፈለኝ ሰርቻለሁ፡፡ በመቀጠልም ትምህርቴን እማር የነበረው ወተት በመሸከም ነበር፡፡ አስተዳደጌን አሁን ላይ ሳስበው እወደዋለሁ፡፡ ምክንያቱም በዚያ ሁኔታ ባላልፍ አሁን የደረስኩበት ደረጃ አልደርስም ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ የምረዳው ፈጣሪ በፈቀደው መንገድ ማለፌ ግድ እንደሆነ ነው ፡፡

የሚገርመው ቤታችን ለረጅም ጊዜ መብራትም ሆነ ውሃ አልነበረም፡፡ ስለዚህ ለምግብ መስሪያን ጫካ በመሄድ ማገዶ እለቅማለሁ፤ እንዳውም አብዛኛው ውሎዬ ጫካ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ የከብት አዛባ ጠፍጥፌ ለእናቴ ማገዶ አዘጋጅላትም ነበር፡፡ ረጅም ርቀት ተጉዤ የቦኖ ውሃ ካለበት ስፍራ ውሃም አመጣ ነበር፡፡ ይህንን ሁሉ የምሰራው ግን ለአቅመ ሥራ ገና ባልበቃ የልጅነት ጉልበቴ በመሆኑ የዘወትር ስራዬ ስለነበር መላ አካሌ በጣም ተጎድቶ ነበር፡፡ ቀኑን ሙሉ ዋናው ትኩረቴ የእናቴን ድካም መቀነስ ስለነበር፤ አጥር ከመስራት ጀምሮ ቤት ውስጥ በወንድ አይሞከሩም የሚባሉትን ስራዎች ሁሉ አጠናቅቄ እጠብቃት ነበር፡፡ በአጠቃላይ ያደኩት ራሳችንን የቻልን እንድንሆን ላይ ታች እያልኩ ነው፡፡

ማንኛውንም ስራ አልንቅም፤ ከልጅነቴ ጀምሮ ስራ እወዳለሁ፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ እጥር የነበረው ራሴን ለመሆንና ኑሮን ለማሸነፍ ነበር፡፡ ሰባተኛ እና ስምተኛ ክፍል እያለሁ ትምህርቴን ከፍዬ የተማርኩት የቀን ስራ እየሰራሁ ነው፡፡ አንድ ዓመት እንዳዉም ራሴ ከፍዬ የግል ትምህርት ቤት ተምሪያለሁ፡፡ የተረፈውን ገንዘብ ደግሞ የምሰጠው ለእናቴ ነው። ሁለተኛ ደረጃ ከገባሁም በኋላ በጠዋት ተነስቼ 20 ሊትር ወተት በትከሻዬ ተሸክሜ ከሾላ ገበያ እስከ አራት ኪሎ ድረስ በእግሬ እያመላለስኩኝ በወር 20 ብር አገኝ ነበር። ለትምህርት ቤት 16 ብር ከፍዬ አራት ብሯን ጮርናቄ እበላባታለሁ፡፡ የሚገርምሽ ያንን ስራ በምሰራበት ወቅት ትከሻዬ ተልጦ ሁሉ ነበር፡፡

ይሁንና በነበረብኝ የስራ ጫና ምክንያት የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ማለፍ ስላልቻልኩኝ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር በመሆን ኮልፌ በሚገኘው ቤታቸው ውስጥ ሰዎች 300 ብር ሰጥተውን 30 ዶሮዎች ገዝተን ማርባት ጀመርን። በጥሩ ሁኔታ እያደጉና እንቁላል መጣል ሲጀምሩ አውሬ ይበላቸው ጀመር፡፡ በኋላም በሽታ ገባና ጨረሳቸው። ከዚያ ተስፋ ቆረጥኩና ኬክ ቤት ተቀጥሬ መስራት ጀመርኩኝ፡፡ ተቀጥሬ እሰራ የነበረው ለገሃር አካባቢ በ130 ብር ነበር ፡፡

ዘወትር ከሌሊቱ 11 ሰዓት ተነስቼ የካ ከሚገኘው ቤታችን እስከ ለገሃር ድረስ በእግሬ እየሮጥኩኝ በመሄድ ዳቦ እጋግር ነበር፡፡ ዳቦ መጋገሩን እየለመድኩኝ ከመጣሁኝ በኋላ ግን ኬክ ጋጋሪው ሙያውን ሊያስተምረኝ ባለመፈለጉ እቆጭ ጀመር። ስለሆነም ራሴን ማስተማር እንዳለብኝ ወሰንኩኝ። ግን በወቅቱ ክፍያው ቀላል አልነበረምና በሰዎች ድጋፍ ተማርኩኝ፡፡ በመሃል ትምህርት ቤቱ ዋጋ ጨመረብን፤ የምከፍለው ስላልነበረኝ ግለሰብ ቤት ውስጥ የቤት ሰራተኛ ሆኜ ተቀጠርኩኝ፡፡ ምግብ እሰራለሁ፤ የህፃናት ልብስ አጥባለሁ፤ ሌሎች የቤት ስራቸውን እየሰራሁ 260 ብር በወር ይከፍሉኝ ነበር፡፡

ቤታቸው ሲኤምሲ ስለነበር የምማርበት ትምህርት ቤት ፒያሳ እመላለስ የነበረው በአውቶብስ ነበር፡፡ እንደዚያም ሆኖ ገንዘቡ አይበቃኝም ነበር። በዚያ መልኩ ትምህርቴን እንደምንም ብዬ ከጨረስኩኝ በኋላ፤ አክሱም ሆቴል ለስድስት ወራት በነፃ ሠራሁ፡፡ ከዚያ ደግሞ የተወሰነ ገንዘብ እየከፈሉኝ ለአንድ ዓመት ሠራሁ፡፡ በመቀጠልም የተለያዩ ሬስቶራንቶች እየተዘዋወርኩኝ ሠርቻለሁ፡፡ በዚህ መልኩ ከልጅነት ጀምሮ በውጣ ውረድ ውስጥ ካለፍኩኝ በኋላ ዓለምአቀፍ ሼፍ ለመሆን በቅቻለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ያሳለፍከው ችግር አሁን ላለህበት ደረጃ «ጥንካሬ ሰጥቶኛል» ብለህ ታምናለህ?**

**ኢንተርናሽናል ሼፍ፡-** ልክ ነው፡፡ እንደነከርኩሽ እናቴ ሌሊት ከጅብ ጋር እየተጋፋች በመሄድ የምትመለሰውም ከምሽቱ 11 ሰዓት ነው፡፡ የሚገርምሽ እንዲህም ሰርታ የሚከፈላት የነበረው 40 ብር ነበር። በመሆኑም እኔ ነበርኩኝ ወፍጮ ቤት እህል ከማስፈጨት ጀምሮ በማብኳትና በመጋገር እናቴን አግዛታለሁ፡፡ እናቴ ማታ ስትመጣ የምጠብቃት ቤቱን አፅድቼና ቡና አፍልቼ ነበር፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ገበያ እሄዳለሁ፤ እንጨት እለቅማለሁ፤ እድር መክፈልና ቀብር መሄድ ራሱ የእኔ ሃላፊነቶች ነበሩ። በዚህም ሌት-ተቀን እኛን ለማሳደግ የምትተጋውን እናቴን አሳርፌያታለሁ ብዬ አምናለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ እናቴ ትደሰታለች ሌላ ጊዜ ደግሞ ትቆጣኝ ነበር። በነገራችን ላይ እናቴ በባህሪዋ ሃይለኛ ነበረች፤ በዚያ ላይ ከነበረባት የሕይወት ጉስቁልና እና ልጆችን ለብቻ ማሳደግ ምሬት ውስጥ ከቷት ነበር፡፡ እናቴ ምሬቷን ባለማወቅ የምትወጣ የነበረው እኔ ላይ ነበር፡፡ ያም ቢሆን እናቴ ለልጆቿ ብዙ ዋጋ የከፈለች ጀግና እናት ነበረች። በአጠቃላይ ግን እኔ ያንን የእናቴን ትጋት እያየሁ በማደጌ ትልቅ ጽናትና አቅም ፈጥሮልኛል ብዬ አምናሁ፡፡

እንደተባለው አሁን ላይ ያ ጊዜ እንዴት አለፈ እያልኩ አስባለሁ፡፡ አንዳንዶቹ ችግሮች ደግሞ ለማመንም የሚከብዱ ነበሩ፡፡ በተለይ የአዲስ አበባ ልጅ ሆኖ የሰው ቤት ተቀጥሮ መስራት ቀላል አይደለም፡፡ እንዳውም እዚህ ጀርመን ያለ ሰው መጽሃፌን ካነበበ በኋላ «ብዙ ሰዎች በአንተ መንገድ ቢያልፉ ራሳቸውን ያጠፋሉ፤ አንተ ግን እድለኛ ነህ» አለኝ። እርግጥ ነው እኔም ከፈተናው የተነሳ አንድ ሁለት ጊዜ ራሴን ለማጥፋት ሞክሬ ነበር፡፡ ግን አልሳካ ብሎኝ ነው። ይህም የሆነው በልጅነቴ ነው፡፡ በኋላ ላይ ግን ጽናቴ ሃይለኛ ሆነ፡፡ ነገሮች እንደሚቀያየሩ አምን ነበር፡፡ እርግጥ ነው በአቋራጭ መንገድ ባምን ኖሮ ብዙ አማራጮች ነበሩ፡፡ ግን እኔ ይህንን መንገድ አልፈለገውም ነበር፡፡ ምክንያቱም ዛሬ ተብለጭልጮ፤ ነገ የማዘን ሕይወት ውስጥ መግባት

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

አልፈልግም፡፡

በጥቅሉ የእኔን ሕይወት ልክ እንደወይራ ማየት ይቻላል፡፡ የወይራ ዛፍ ቶሎ አድጎ ፍሬ አይሰጥም፤ ልጅ ሆኖ ግን ይረገጣል፤ ይታሻል፤ ተመልሶ ያቆጠቁጣል። ልክ እንደወይራ እኔም ተረግጬ አውቃለሁ፡፡ እንደሚታወቀው በእኛ ሀገር ደምግባት የሌለውና ድሃ ሰው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ እኔም በዚህ ምክንያት መገፋትን፤ መናቅን አይቻለሁ። እንዳውም ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ጊዜ በእናት ብቻ የምገናኘው ወንድሜ የአባቱ ቤተሰቦች ሰርግ ጠርተውን አብረን ሄድን፡፡ ግን አለባበሳችንን ላየ የምንመስለው የሀብታምና የድሃ ልጅ ነው ፡፡ ምክንያቱም እሱ ድጋፍ የሚያደርጉለት ቤተሰቦች ስለነበሩት ነው፤ እኔ ደግሞ የለኝም። እናም በዚያ አጎቱ ሰርግ ላይ ድንኳን ውስጥ እናቴና እሱ ሲገቡ፤ እኔ ለሰርጉ የሚመጥን ልብስ ባለመልበሴ አጎትየው እኔን ከበር አስፈንጥሮ አባረረኝ። በኋላ ላይ ከሰፈር ለማኞች ጋር ትርፍራፊ ተሰጥቶኝ ተሻምቼ በላሁ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ዘመድም ያገላል፤ የሚያደሉት ከድሃው ይልቅ ላለው ነው፡፡ እነዚህ መገለሎችና ችግሮች ግን ሜዳ ላይ አላስቀሩኝም፡፡ ወይም ደግሞ በቀለኛ አላደረጉኝም። ይልቁንም ታታሪ አደረጉኝ። አቋራጭ መንገድ ፍለጋም በጭራሽ አልሄድኩም። እዚህ የደረስኩት መስመሬን ጠብቄና የሚገባኝን ያህል ለፍቼ በመሆኑም የምበላው ያገኘሁትን ንጹህ እንጀራ ነው፡፡ እርግጥ ነው አንዳንድ ሰዎች ከየት መጡ ሳይባል በድንገት ሊነሱና ሊከብሩ ይችላሉ፡፡ ግን መጨረሻቸው አያምርም፡፡ መስመሩን የጠበቀ እድገት ግን ውጤቱም ደስ ይላል፤ እርካታውም ያን ያህል ትልቅ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከነገር የወጣህበት አጋጣሚ ምን ነበር?**

**ኢንተርናሽናል ሼፍ አንተነህ፡-** በመጀመሪያ ስፔን ባርሴሎና የመሄድ እድል አገኘሁ፡፡ እድሉን ያገኙልኝ በስራ የማውቃቸው ስፔኖች ናቸው፡፡ መጀመሪያ ላይ እኔ እንዳውም አልሄድም ብዬ ነበር። ምክንያቱም በወቅቱ የራሴን ሬስቶራንት ከፍቼ ጥሩ ሥራ ነበረኝ። ከዚያ ይልቁንም የምፈልገውን ጎብኝቼ ለመመለስ ነበር። በኋላ ላይ ነገሮች እንደፈለኩት አልሄድ ሲሉኝና ተስፋ ሲያስቆርጡኝ ለመሄድ ወሰንኩኝ፡፡ በተለይ ነገሮች በጣም ሲበዙብኝ በጣም ስለምጨነቅ በልጅነቴ ደምግፊት ጀምሮኝ ነበር፡፡

ሃኪሞች ከጭንቀት ነፃ ካልሆንኩኝ የከፋ ነገር ሊደርስብኝ እንደሚችል ነገሩኝ፡፡ በኋላ ላይ ራሴን ለማዳን ስል እዚህ ያለውን ነገር ሁሉ እርግፍ አድርጌ ትቼ ተሰደድኩ፡፡ በእርግጥ ስደት ብዙ ዋጋ አስከፍሎኛል፤ ያም ቢሆን ውስጤ ጭል ጭል የሚል ተስፋ ስለነበረኝ እጅ ሳልሰጥ ቆየሁኝ። ከስፔን ወደ ጀርመን በመምጣት የጥገኝነት ጥያቄ አቅርቤ፤ እንደማንኛው ስደተኛ ካምፕ ገብቼ፤ የካምፑን ክፉም ደግም ሁኔታ አየሁኝ። ከዚያ በኋላ እንግዲህ ነገሮች እየተቀየሩ መጡ፡፡ በዋናነነት እጅ ሳልሰጥ ቋንቋቸውን በመማር ቶሎ ግንኙነቴን ማጠናከር ጀመርኩ፡፡ በአሁኑ ወቅት በጀርመን ትልቁና አለ በተባለው ሆቴል ውስጥ በሼፍነት እየሰራሁ እገኛለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የሕይወት ታሪክህን ጽፈህ ለማሳተም የተነሳህበት ምክንያት ምን ነበር?**

**ኢንተርናሽናል ሼፍ አንተነህ፡-** እንዳልኩሽ ያሳለፍኩት ነገር በመፅሃፍ ደረጃ እንኳን ለመግለፅ በጣም ከባድ ነው። እውነት ለመናገር አሁን የተናገርኩትም በጥቂቱ ነው።፡ ያም ቢሆን ግን ሕይወቴ ለሌሎች በጣም ያስተምራል ብዬ አምናለሁ፡፡ አስቀድሜ እንዳልኩት ያሳለፍኩትን ሁሉ ነገር እወደዋለሁ። አንድ ሰው ለሌላ ሰው ለመስጠት የሚያስበው የሚወደውን ነገር ነው፡፡ ያሳለፍኳቸው ነገሮች ቀላል እንዳልሆኑ እኔ ራሴ እረዳለሁ። በተጨማሪም በተለይ ለወጣቶች አስተማሪ እንደሆነ አምናለሁ፡፡ ቶሎ ተስፋ ለሚቆርጡና ምክንያት ለሚሰጡ ሰዎች አስተማሪ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

እርግጥ እኔ ራሴ እጄን አጣጥፌ ለመቀመጥ የምደ ረድራቸው ምክንያቶች ነበሩኝ፡፡ ግን ከሥራ ስባረር እንኳን ለመቀመጥ ምክንያት አልሰጥም፡፡ አንዱ ሲዘጋ ሌላውን በር አንኳኳለሁ፡፡ የማገኛቸውን እድሎች በሙሉ እጠቀማለሁ፡፡ በተለይ በሰው በኩል እድለኛ ነኝ፤ የማገኛቸውን ሰዎች ሁሉ እጠቀማለሁ። አገኘሁ ብዬም አልኮፈስም፤ ስላላገኘሁም ተስፋ አልቆርጥም፡፡ የምፈልገውን ነገር የምጠይቀው በግልፅ ነው፡፡ የምገባው በመጠየቄ ጥሩም ሆነ መጥፎ ምለሽ ሊሰጡኝ እንደሚችሉ አምኜ ነው። መማር ካለብኝ እማራለሁ፡፡ ስለዚህ መጽሐፉን ጽፌ በማሳተም ለአንባቢያን ያደረስኩት፤ እኔ ያለፍኩት ውጣ ውረድ የበዛበት መንገድ ለሌሎች ትልቅ አቅም ይሰጣል ብዬ ስላሰብኩ ነው፡፡

እውነት ለመናገር ከዚህ ከአማርኛው መጽሐፍ በፊት መጽሐፍ ጽፌ አላውቅም፡፡ ግን እንዲሁ ስናደድና ስደሰት ለራሴ መፃፍ እወዳለሁ፡፡ ግን ከፃፍኩኝ በኋላ ቀዳድጄ እጥለዋለሁ፡፡ ተመልሼ አላነበውም፡፡ የምፈልገው ስሜቴ ከእኔ ውስጥ እንዲወጣ ብቻ ነበር፡፡ ወረቀቱ ላይ ካሰፈርኩኝ በኋላ ውስጤ ሰላም ያገኛል፡፡ አንድ ወቅት ላይ ግን ሁልጊዜ እንደዚህ ከማደርግ ለምን አልፅፈውም ብዬ አሰብኩኝ። አንዳንድ ሰዎችም ታሪኬን እንድፅፍ ይመክሩኝ ነበር። ሆኖም



ለመፃፍ የሚያስችል ጊዜ አልነበረኝም። በተለይ ኢትዮጵያ እያለሁ እረፍት የሚባል ነገር አልነበረኝም፡፡ የሚገርመው ከሰኞ እስከ አርብ ተቀጥሬ እየሰራሁ ሳለ፤ እሁድና ቅዳሜ ደግሞ ለሰርግና ድግስ ምግብ እሰራ ነበር፡፡ ስለዚህ ቁጭ ብዬ ለመፃፍ የሚያስችል ፋታ አልነበረኝም፡፡ በኋላ ላይ ግን ኮቪድ መጣና ለወራት ቤት ውስጥ ቁጭ ስንል ያለውን ጊዜ ተጠቅሜበት መጽሐፌን ፃፍኩኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡-ይህ መጽሐፍ ከአማርኛ ወደ ጀርመንኛም ተተርጎሞ በዓለም ገበያ ላይ ውሏል፤ ስለመሆኑ ተቀባይነቱ ምን ይመስላል?**

**ኢንተርናሽናል ሼፍ አንተነህ፡-** መጀመሪያም ቢሆን መጽሐፉን የፃፍኩት ሰው ይቀ በለዋል፤ አይቀበለውም ብዬ አይደለም፡፡ ተቀባይነት ይኖረዋል ተብሎ የሚፃፈው ለገበያ የሚፃፍ ሲሆን ነው፡፡ የግል ሕይወት ታሪክ ስለሆነ ተቀባይነት ማግኘት እኔን ያ የሚያሳስበኝ አይደለም፡፡ የምጽፈው በሕይወቴ የሆነውን ሳልጨምር ሳልቀንስ ነው፡፡ ስለዚህ ሰው ሲያነብ በእኔ ሕይወት ውስጥ የሚማረው ነገር ይኖራል። መጽሃፌን ያረሙትም በትልልቅ ስራዎቻቸው የሚታወቁ የእነሃይለመለኮት መዋልና የብርሃኑ ሰሙ እጅ አርፎበታል፡፡ እነዚህ ሰዎችም ሆኑ መጽሐፉን ያነበቡ ሰዎች የነገሩኝ ከዚህ ቀደም ተሞክሮ እንዳለው ደራሲ መፃፌን ነው።

የሰጡኝ ምላሽ ታሪኩም መሳጭ በመሆኑ ለማቆም አይጋብዝም የሚል ነው፡፡ በነገራችን ላይ መጽሐፉ ፊልም እንዲሰራም ሁሉ የጠየቁኝ ሰዎች አሉ፡፡ በአጠቃላይ በጣም ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ እውነት ለመናገር ለማስተዋወቅ እንኳን ገንዘብ አልከፈልኩም፡፡ በሬዲዮ ላይ መጽሐፉ ሲተረክና ሲወያዩበት ሰምቻለሁ፡፡ ሽያጩም ያለቀው ወዲያው ነው፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ስመጣ ሁለተኛ ዙር ይታተማል ብዬ አስባለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በጀርመንኛ ተተርጉሟል። እንዲያውም የተሰራው ከአማርኛው በተሻለ በጣም ጥሩ ተደርጎ ነው፡፡ በትርጉም ስራ በጣም ታዋቂ የሆኑ ኢትዮጵያውያን የጀርመን ምሁራን ተሳትፈውበታ። የአፄ ኃይለስላሴ የልጅ ልጅ የሆኑት አልጋወራሽ አስፋወሰን ረድተውኛል፡፡ መጽሐፉ የጀርባ ገጽ ላይ ያለው የእርሳቸው ጽሁፍ ነው፡፡ እኚህ ሰው በጀርመን ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው የቋንቋና የታሪክ ምሁር ናቸው። እንዳልኩሽ በጀርመንኛ የተተረጎመው መጽሐፍ በጣም የተዋጣለትና በቋንቋ ብቃቱም የጎለበተ ነው፡፡ በአጠቃይ በዚህኛው መጽሐፍ ላይ ስድስት ሰዎች ተሳትፈውበታል፡፡ አሁን ገበያ ላይ ውሏል፤ አማዞን ላይም አለ፡፡

በቀጣይ እንግዲህ በሌላ መጽሐፍ ደግሞ ከአንባቢዎች ጋር እገናኛለሁ ብዬ አስባለሁ፡፡ ከሙያዬ ጋር በተያየዘ እና ለሆቴል ኢንዱስትሪው እድገት በጣም ጠቃሚ ይዘት ያለው መጽሐፍ በማዘጋጀት ላይ ነኝ። በተለይ እዚህ ሀገር የያኋቸውን ለእኛ ሀገር ሆቴል ኢንዱስትሪ ለውጥ ያመጣሉ ብዬ የማስባቸውን ነገሮች ሁሉ ለማካተት እየሞከርኩ ነው። በመሆኑ ከዚህኛው መጽሐፍ በተሻለ ቆንጆ መጽሐፍ እንደሚወጣ አልጠራጠርም፡፡ የመጀመሪያውን መጽሐፌን ወደ እንግሊዝኛ ተተርጎሞ በመላው ዓለም እንዲነበብ የማድረግ እቅድም አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያዊነት ለአንተ ምንድን ነው?**

**ኢንተርናሽናል ሼፍ አንተነህ፡-** እኔ ኢትዮጵያዊ በመሆኔ ደስ ይለኛል፡፡ እውነት ለመናር ግን አንዳንድ ጊዜ ኢትዮጵያዊ በመሆኔ አንገቴን የምደፋበት ነገር ደግሞ አለ። በተለይ አሁን ላይ በሀገራችን የሚታየው ጭካኔ፤ ክፋት፤ አላዋቂነት እጅግ ከመንሰራፋቱ የተነሳ የማፍርበት ሁኔታ አለ፡፡ ሁኔታው እየባሰ በመጣ ቁጥር በጣም ያስፈራኛል፡፡ እንዳውም አሁን ላይ እኔ በበኩሌ ለፈጣሪ እጅ እየሰጠሁኝ የመጣሁ ይመስለኛል፡፡ አንድ ቀን እሱ በፈቀደው ጊዜ ልክ እንደእኔ ሕይወት ያስተካክለዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ እውነት ለመናገር እኔ ያደኩባት የማውቃት ኢትዮጵያ ሁሉን በእኩል አቅፋ፤ ሁሉም በፍቅር የሚኖርባት፤ ለሁላችንም በቂ የነበረችውን ኢትዮጵያ ነው። ለምሳሌ ልጅ ሆነን ስንጫወት ማን ምንድነው? የመጣው ከየትኛው ጎሳ ነው? ተባብለን አናውቅም፡፡ ሰፈራችን ውስጥ በየቀኑ ኳስ እየተራገጥን ስንውል ጓደኝነታችን እንጂ የማንነታችን ጉዳይ ጨርሶ ተነስቶ አያውቅም። በቤተሰብ ደረጃም እናቴ ለምሳሌ ማህበር ፤ እድር ውስጥ ትሳተፋለች፤ እነዚህ ማህበራዊ ተቋም ውስጥ ማን ምን እንደሆነ ተጠይቆ አያውቅም፡፡ ጽንፍ የሚባል ነገር አይቼ አላውቅም። ሕዝቡ ቢጣላ እንኳን ለመታረቅ ቅርብ ነበር። ገንዘብ ባይኖራቸውም በበረከት ይኖሩ የነበሩት ለዚያ ይመስለኛል፡፡

አሁን ያለውን ሁኔታ ግን በጣም ያሳዝናል፡፡ ያሳዝናል ብቻ ሳይሆን ያስፈራልም፡፡ ለምሳሌ እዚህ ሀገር ከእኛ በላይ በብዙ ችግርና ጦርነት ውስጥ ያለፈ ሕዝብ ነው፡፡ ያሳለፉት ችግር ትምህርት ሆኗቸውና ሰክነው ዘር ወይም ጎሳ የሚባለው ነገር ከህሊና መዝገባቸው እንዲወጣ አድርገዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር እንደሚመስለኝ የእውቀት ችግር ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አወቅን የሚሉ ሰዎች በጣም ነገሮችን ያወሳስባሉ፡፡ ይህንን ስመለከት አደጋ ላይ ነን ብዬ እንዳስብ ያደርገኛል፡፡

እግዚአብሔር ትልቅ፤ አየሯም ሆነ መሬቷ የተባረከ ሀገር ናት፡፡ ሕዝቡም ቢሆን ያን ያህል ክፉ የሚባል አይደለም። እንዳውም ደንጋጣና ፈጣሪን የሚፈራ ቶሎም የሚመለስ ሕዝብ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ መመራት አይችልም ይባላል እንጂ መሪ ካገኘ በስርዓት የሚኖር ሕዝብ ነው፡፡ በትንሽ ነገር የሚደሰት ሕዝብ ነው። ስለዚህ ትንሽ ነገር የሚያስደስተውን ሕዝብ መምራት ቀላል ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም የፖለቲካ ተዋናዮች ሰከን ብለው ሀገሪቱን ወደፊት ማሻገር ይጠበቅባቸዋል፡፡

እኔ ኢትዮጵያ ሀብታም ሀገር እንደምትሆን ትልቅ ተስፋ አለኝ፡፡ እርስ በርስ ባለመግባባት ከድህነት የምንወጣበትን ጊዜ ልናራዝመው አይገባም፡፡ የምፈራው እንደእስራኤል ሕዝብ እንዳንሆን ነው። የእስራኤል ሕዝብ ወደ በረከት ሀገራቸው በ40 ቀን መድረስ ሲገባቸው በራሳቸው ችግር ምክንያት 40 ዓመት እንደፈጀባቸው ይታወቃል፡፡ ስለዚህ እኛም በራሳችን ጥፋት የመከራችንን ጊዜ ማራዘም የለብንም። ችግራችን በአጭሩ እንዲቀጭ በሥርዓት መመራት አለብን። አንዳንድ ጊዜ በፖለቲካ እያሳበቡ ራስ ወዳድነት ጎልቶ ይታያል፡፡ ከፖለቲከኞቹ ባሻገር የቤት አከራዮች፤ ነጋዴዎችና ደላሎች በሕዝቡ ላይ የሚፈጽሙት ግፍና ጭካኔ ካላቆሙ ፈጣሪ ይታረቀናል ብዬ አላምንም፡፡ ይህ ሲባል ግን ጥሩ ሰዎች የሉም ማለት አይደለም፤ አሉ፡፡

አሁን የምናየው የብዙ ጨካኞች ድምር ውጤት ነው። በፊት ሌባ ለመስረቅ ሲል ብቻ ሰው አይገድልም ነበር፡፡ አሁን ግን የሰው ገንዘብ ለመቀማት ሲሉ በጠራራ ፀሃይ ሳይታሰብ ከጀርባ ሰው ደፍተው የሚሄዱ አሉ፡፡ እናም እንዲህ ዓይነት ጭካኔ ውስጥ ከገባን ያለነው አደገኛ ነገር ውስጥ ነው፡፡ አሁን እኮ ማታ ማታ ሰዉ እንደፈለገ ዘና ማለት አይችልም፤ ሁሉም ቤቱ የሚሰበሰበው ሳይወድ በግዱ በጊዜ ነው። ሰው በገዛ ሀገሩ በነፃነት የማይመለስ ከሆነ ጤናማ ሥርዓት አለ ለማለት አይቻልም፡፡ እነዚህ ነገሮች ቀላል አይደሉም፡፡ ያም ቢሆን ይህ ችግር መፈታቱ አይቀርም፡፡ ሁሉም ከተባበረ፤ መንግሥትም ሆነ ሕዝቡ ሃላፊነቱን ከተወጣ የማይስተካከል ችግር አይኖርም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አንተ የምትኖርባት ጀርመን በታሪክ የምትታወቅበትን ዘረኝነት ላይ መሰረት ያደረገውን የናዚ ጭፍጨፋ ትውልዱ ላይ ጥላቻና በቀል እንዳይሻገር ከሠሩት ሥራ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን መማር ይችላል?**

**ኢንተርናሽናል ሼፍ አንተነህ፡-** እጅግ በጣም ብዙ ነገር መማር እንችላለን ብዬ አስባለሁ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እነሱ ጦርነትን በጣም ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ የዓለም ክፋትን ጥግ እነሱ ሀገር ላይ ተፈጽሟል፡፡ ግን አሁን ላይ ያሉት ጀርመኖች ግን በጣም ምርጥ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ሀገራቸውንም ለሁሉም የሰው ልጅ የሚመች አድርገውታል። እኛ ሀገር ለምሳሌ አሁን ላይ የሚሰሩ ሕንፃዎች ሰማይ ጠቀስ ናቸው፡፡ ገንዘብ ያለው በሙሉ የሚውለው ድንጋይ ላይ ነው፡፡ ጀርመኖች ግን ብዙ ገንዘብ ቢኖራቸውም ትልልቅ ህንፃ አይሰሩም። ገንዘባቸውን የሚያውሉት ሰው ላይ ነው። ትውልድ ላይ፤ ትምህርት ላይ ነው፡፡

ትኩረት የሚያደርጉት ለሰው ልጅ የሚመች ነገር ላይ እንጂ ሕንፃ ቢገነቡ ከእኛ 40ና 50ሺ እጥፍ ይገነባሉ፡፡ አንድ ሕፃን ልጅ ከተወለደ ጀምሮ እስከ 18 ዓመቱ ቢያንስ አንድ ሚሊዮን ዩሮ ይወጣበታል። ይህንንም የሚከፍለው መንግሥት ነው፡፡ ስለዚህ ገንዘባቸውን ትውልድ ላይ አድርገውታል፤ እንዲሁ ድንጋይ ላይ አፍሰስው መና እንዲቀር አያደርጉትም፡፡ እኛ ሀገር ደግሞ በተቃራኒው ነው፡፡ ሰው ላይ የሚሰራ ነገር የለም፤ አብዛኞቹ ፖሊሲዎች ከትውልድ አንፃር ሊስተካከሉ ይገባል፡፡

እርግጥ ነው ከዚህ ቀደም በነበረው መንግሥት ጥቃቅና አነስተኛ በማደራጀት ሰዎች ሕይወታቸውን እንዲቀይሩ ጥረት ተደርጎ ነበር፡፡ ሆኖም ከጥቅሙ ይልቅ መጥፎ ጎኑ በማድላቱ ውጤቱ አመርቂ አልሆነም፡፡ ለምሳሌ ወጣቱን ከማደራጀት በፊት የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ይጠበቅ ነበር። ሰዎችን ሳያሰለጥኗቸውና የአመላከከት ለውጥ ሳይመጣ ድንገት አምጥተው ገንዘብ ሲሰጧቸው የባሰ እዳና ሱስ ውስጥ ተዘፈቁበት እንጂ አልተለወጡበትም። አንዳንዶቹ እንደውም ብሩን ካጠፉት በኋላ ከሀገር የተሰደዱ አሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንደውም መንግሥትም ራሱ ወጣቱን ከሀገር ማባረሪያ ዘዴ አድርጎ የተጠቀመበት ይመስለኛል። መሆን የሚገባውን ግን በአግባቡ ጥናት ተደርጎበት ሥርዓት ተበጅቶለት መሆን ነበረበት፡፡

ጀርመኞች ዘረኞች አይደሉም፤ እኔ ኢትዮጵያዊ ሆኜ እነሱ ሀገር የምኖረው ሰላምና ደህንነቴ ተጠብቆ ነው። ከኢትዮጵያ ይልቅ ደረቴን ነፍቼ በነፃነት በጨለማ፤ የፈለኩትን ተናግሬና መብቴን አስከብሬ ነው የምኖረው። ሥርዓቱ አስቀድሞም ስለተፈጠረ መብቴ የሚከበረው በቀላሉ ነው፡፡ ስለለበስኩና ሳላለበስኩ፤ ጥቁር ወይም ነጭ ስለሆንኩኝ ሳይሆን መብቴ የሚከበረው የተፃፈ ሕግ ስላለና በተጨባጭም ስለሚከበር ነው፡፡ የሕግ የበላይት በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚከበር ነው፡፡ በተወለድኩባት ኢትዮጵያ ግን የዚህን ያህል ነፃነት የለኝም። እርግጥ ነው አሁንም ጥቂት ዘረኛ ናዚዎች አሁንም አሉ፡፡ ግን የፈለገውን ያህል ዘረኛ ቢሆኑ ከሕግ በላይ አይደሉም፡፡ ሕጉ ስለሚከበር ሁሉም ሰው ተከባብሮ ይኖራል፡፡ እየጠላም ጥላቻውን በአፉ መናገር አይችልም፡፡

ኢትዮጵያም ሕግ አለ፤ ግን አልተከበረም፤ ፍትህም ተዛንፏል፡፡ ሙስኝነትም በጣም ተስፋፍ ቷል። ከፍተኛ የሆነ የጉቦ ሥርዓት ተፈጥሯል፡፡ እሱ አደገኛ ነገር ነው። እርግጥነው የኑሮ ውድነቱም፤ ሌብነቱ መስፋፋት ምክንያት ሊሆን ይችላል፤ ግን የሀገሪቱ መንግሥትና ኢኮኖሚስቶች መፍትሔ መፈለግ አለባቸው፡፡ በፊት ጉቦ ሰጪም ሆነ ተቀባይ በድብቅ ተሳቀው ይቀባበሉ ነበር፡፡ አሁን ሁለቱም የሚያደርጉት በነፃነት ነው፡፡

ሁለተኛ ችግር ደግሞ የህጉ አፈፃፀም መላላት ነው፡፡ እኔ ለምሳሌ በቅርቡ ቦሌ አካባቢ ሌባ አጋጠመኝና ለፖሊሶች ስነግራቸው እኛ ብናስራቸውም መልሰው ስለሚፈቷቸው ፖሊስ ጣቢያ መውሰድ ትተናል አሉኝ፡፡ እናም እንዲህ አይነት ነገር እያለ ሕግ ማስከበር አይቻልም፡፡ አብዛኛው ሕዝብ ፖሊስ ይጠብቀኛል የሚል እምነቱን አጥቷል። እርግጥ ነው በጣም ምግባረ ሰናይ የሆኑ የፀጥታ አካላት አሉ። በተቃራኒው ደግሞ ከሌባ ጋር አብረው የሚሰሩ አሉ። የፍትህ አካላቱ ራሱ በሌቦች ከተዘፈቀ ሀገር አደጋ ላይ ነች። እንደሚታየው በየጊዜው መኪና ይጠፋል፤ ሰው ይጠፋል አሁንማ የሰው ሕይወት ቀላል ሆኖብናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**ኢንተርናሽናል ሼፍ አንተነህ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## የወባ በሽታ ስርጭትና የኢትዮጵያ ጥረት

**ሰላማዊት ውቤ**

ወባ ከዓለማችን ገዳይ በሽታዎች አንዱ ነው። ከምዕራባዊቱ አሜሪካ ጀምሮ ምዕራብ ፓስፊክ አካባቢ፤ ምሥራቅ ሜዲትራኒያዊ፤ ደቡብ ምስራቅ ኢሲያ በአጠቃላይ ከምድር ወገብ በታች ያሉ አገራት ለበሽታው ተጋላጭ መሆናቸው ይነገራል። በተለይ በአፍሪካ ተስፋፍቶ ይስተዋላል። ለአብነትም ከሳሐራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሃገራት በከፍተኛ ተጋላጭነታቸው እንደሚጠቀሱ የዓለም አቀፉ የጤና ድርጅት መረጃ ያሳያል። በበሽታው ከሚሞቱት ሰዎች መካከል ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆነ ህፃናት መሆናቸው በእጅጉ ያሳስባል። የሚያጠቡና ነፍሰጡር እናቶች አብዝተው በሞት የሚጠቁበት ሁኔታም መኖሩን መረጃው ያመለክታል። እንደ መረጃው እ.ኤ.አ በ2017 በ87 የዓለም አገራት 219 ሚሊዮን ሰዎች በወባ ተይዘዋል። በዚሁ ዓመት ከተያዙት ውስጥ በትንሹ 435 ሺ ሰዎች እንደሞቱም ይገመታል። በፈረንጆቹ 2017 በወባ የተጠቁ ሰዎችን የተመለከተ መረጃ እንደሚያሳየው ግማሽ ያህሉን ካስመዘገቡት አምስት አገራት አራቱ አፍሪካውያን ሲሆኑ እነሱም ናይጀሪያ፤ ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ፤ ሞዛምቢክና ዩጋንዳ ነበሩ።

የወባ በሽታን ከገፀ - ምድሯ ለማጥፋት የተለያዩ መርሐ ግብሮች ዘርግታ በመንቀሳቀሱ ረገድ ከአምስት አሥርት ዓመታት በላይ ባስቆጠረችው ኢትዮጵያም ወባ የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን በጤና ሚኒስቴር የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ዳይሬክተር ወይዘሮ ሕይወት ሰለሞን ይናገራሉ። የወባ በሽታን እ.አ.አ በ2030 ከኢትዮጵያ ጨርሶ ለማጥፋት የሚያስችል ስትራቴጂክ ዕቅድ ተነድፎ ወደተግባር መገባቱን ያወሱት ዳይሬክተሯ 75 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ መልካ ምድር ለወባ በሽታ ስርጭት ምቹ መሆኑ ደግሞ በበሽታው የሚደርሰውን ጉዳት አስፍቶታል። በዚህ አካባቢ ከሚኖረው ሕዝብ በአጠቃላይም ከኢትዮጵያ ሕዝብ 52 በመቶ ያህሉ ለወባ በሽታ ተጋላጭ የሆነውም ለዚህ ነው ብለዋል። በኢትዮጵያ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች የወባ ስርጭት የሚከሰተው የዝናብ ወራቱን ተከትሎ እንደሆነ ያስታወሱት ዳይሬክተሯ ከመስከረም እስከ ታኅሣሥ ድረስ ባሉት ወራት ውስጥ እንደሚከሰትም ያስረዳሉ። የበልግ ዝናብን ተከትሎም በሚያዚያ እና በግንቦት ወራት በተወሰነ መልኩ ስርጭቱ የሚባባስበት ሁኔታ እንደሚከሰትም ያወሳሉ። በረጅም የዝናብ ወቅት እና ጎርፍ በበዛበት ጊዜያትም የስርጭቱ ምጣኔ ከፍ የሚልበት ሁኔታ መኖሩንም ያነሳሉ።

የበሽታው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ የጎላ ነው ያሉት ዳይሬክተሯ በምርት መሰብሰቢያ ወቅትና የክረምቱን ዝናብ ተከትሎ ከመከሰቱ በፊት መከላከል ካልተቻለ ጉዳቱ የከፋ እንደሚሆንም አስምረውበታል። በተጨማሪም አርሶ አደሩ የግብርና ሥራውን በአግባቡ እንዳያከናውን፤ ተማሪዎችም ትምህርታቸውን በተገቢ መልኩ እንዳይከታተሉ የልማት ጣቢያ ሰራተኞችም ውጤታማ ሥራ እንዳይሰሩ ያደርጋል።

በሽታው በወረርሽኝ መልክ ሲከሰት ደግሞ የሚያስከትለው ተፅዕኖ እጅግ ከፍተኛ ይሆናል። በጥቂት ጊዜ ውስጥ ብዙ ሰዎችን ለህመምና ለሞት የሚዳርግበት ጊዜ አለ። በዚህ ምክንያትም እንደ አገር ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚዊ ቀውስ ይከሰታል። የንግድና የቱሪዝም እንቅስቃሴንም በማስተጓጎል በአገር ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል።

የዓለም የጤና ድርጅት ሪፖርትን ዋቢ አድርገው ዳሬክተሯ እንደተናገሩት በሽታው በዓለም አቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ በ2020 በአንድ ዓመት ብቻ በ14 ሚሊዮን መጨመሩን አሳይቷል። ከዚህ ቁጥር መካከል 95 በመቶ የሚሆነው ድርሻ የአህጉረ አፍሪካ እንደሆነም ነው የተናገሩት።

እንደሳቸው በዓለማችን ፕላስሞድየም ፋልሲፓረም፣ ፕላስሞድየም ማላሪዬ፣ ፕላስሞድየም ኦቫሌ እና ፕላስሞድየም ቫይቫክስ የተሰኙ የወባ ፓራሳይቶች ይገኛሉ። ፕላስሞዲየም ፋልሲፓረም እና ፕላስሞዲየም ቫይቫክስ የሚባሉት ሁለት ዓይነት የወባ ፓራሳይቶች ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ነው የሚገኙት። ሰዎች በነዚህ ፓራሳይቶቹ በተያዙ ወባ አስተላላፊ እንስት ቢምቢዎች ከተነከሱ በወባ በሽታ ይያያዛሉ ።

በኢትዮጵያ ላለፉት 50ና በላይ ዓመታት ወባ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጥረት ሲደረግ የቆየ መሆኑን የሚያስታውሱት ዳይሬክተሯ በሁሉም ክልሎች ወባን የመከላከል ስራው በጤና ሚኒስቴር በኩል በሰፊው እንደሚሰራም ያብራራሉ። የወባ በሽታ ስርጭት በሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች የዝናብ ወቅትን ተከትሎ የመጨመር እና የመቀነስ ሁኔታ ያለው በመሆኑ ጎን ለጎንም ይሄንኑ መሰረት ያደረገም የመከላከል ሥራ በስፋት እየተሰራ እንደሚገኝም አክለዋል።

‹‹የተግባሩ ውጤታማነት በዓለም ጤና ድርጅት ተቀባይነት አግኝቷል›› ያሉት ዳይሬክተሯ ባሳለፍነው በ2013 ዓ.ም ከስምንት ሚሊዮን በላይ አጎበር መሠራጨቱንም ነው የሚናገሩት። ዘንድሮም 20 ነጥብ 6 ሚሊዮን አጎበር ለማሠራጨትና 1 ነጥብ 6 ሚሊዮን ቤቶችን ኬሚካል ለመርጨት እየተሠራ እንደሚገኝም አውስተዋል። በ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት በ10 ወራት ውስጥ በወባ በሽታ ለተጠረጠሩ 5 ሚሊዮን 909 ሺህ 196 ህሙማን ምርመራ ማድረግ ተችሏል። በ 1 ሚሊዮን 302 ሺህ 360 ወይም 22 በመቶ ወባ ለተገኘባቸው ህሙማን ሕክምና ተሰጥቷል። ይሄ ከነውን ከአምናው 2013 ዓ.ም ጋር ሲነፃፀር በ16 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል ። ዳይሬክተሯ የወባ ህሙማን ቁጥር መጨመር አስመልክቶም ምክንያት ያሏቸውን ዘርዝረዋል። እንደ ሙቀትና እርጥበት መሰል ለወባ መራባት ምቹ የሆነ የአየር ሁኔታ መኖር በምክንያትነት ይጠቀሳል። ከአየር ንብረቱ ጋር ተያይዞ ድርቅ የነበረባቸው አንዳንድ አካባቢዎች ዝናብ መዝነቡ በዚህ ምክንያትም ለወባ ትንኝ መራባት ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውም ለወባ ህሙማን ቁጥር መጨመር ሌላው ምክንያት ነው። በተጨማሪም የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የተሳለጠ መርሐ ግብር አተገባበር ክፍተት መኖሩ እንዲሁም የማህበረሰቡና በግለሰብ ደረጃ የሚካሄዱ የወባ መከላከል ሥራዎች መሥራት ላይ ክፍተት መኖሩም የህሙማን ቁጥር ለመጨመሩ በምክንያትነት የሚነሳ ነው። በተለይ ደግሞ የአጎበር አጠቃቀምና የአካባቢ ቁጥጥር ሥራዎች ላይ ክፍተትና መዘናጋቶች መኖራቸው ለቁጥሩ መጨመር እንደ ችግር ተወስዷል። በግብርና ልማት ሥራዎች መስፋፋት ምክንያት ለወባ ትንኝ መራባት ምቹ የሆኑ ቦታዎች መኖራቸውም እንደ አንድ ችግር የሚነሳ ነው። በሽታውን የመከላከል ተግባሩ እነዚህን ሁሉ ችግሮች መሰረት አድርጎ የሚከናወን ነው።

እንደ ዳይሬክተሯ በተለይ ዘንድሮ በዘጠኝ ወራት ውስጥ በወባ በሽታ መከላከል ዙርያ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ያለበት ሁኔታ አለ። በ229 ወረዳዎችና በ 4ሺህ 400 ቀበሌዎች ላይ ሰፊ የማኅበረሰብ ንቅናቄ በመፍጠር ከ25 ሚሊዮን ለሚበልጥ ሕዝብ በሽታውን በመከላከሉ ዙሪያ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ መሰራቱን ለአብነት ወስዶ ማየት ይቻላል ።

በተጨማሪም የመከላከል ሥራውን በፈጣን ቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግም የተሰሩ ሥራዎች አሉ። 5 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሕሙማን ለመመርመር የሚያስችል ፈጣን የወባ መመርመሪያ ኪት ግዢ የሥራዎቹ ማሳያ ይሆናል። የመመርመሪያ ኪት ግዢውን ተከትሎ 565 ወረዳዎች ወደ ማኅበረሰብ አቀፍ የምርመራና ምላሽ ትግበራ እንዲገቡም ተደርጓል። ዳይሬክተሯ 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሕሙማን ማከም የሚያስችል የፀረ ወባ መድሃኒት ግዢና ስርጭትም የተካሄደበት ሂደት አለ።


‹‹በተለይ ወባማ አካባቢዎች ሕብረተሰቡ ሳያሰልስ የአልጋ አጎበር በመጠቀም በሽታውን መከላከል ይችላል›› የሚሉት ዳይሬክተሯ ለዚህ ሲባልም የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚያስችል የአልጋ አጎበር በስፋት መሰራጨቱንም አንስተዋል። በመጀመሪያ ዙር 2 ነጥብ 9 ሚሊዮን አጎበር ተገዝቶ እየተሰራጨ መሆኑን በማሳያነት ጠቅሰዋል። የአጎበር ስርጭቱ ሂደት በታቀደለት ጊዜ መሰረት ይከናወናልም ብለዋል። ከዚህ በተጨማሪም 1 ነጥብ 6 ሚሊዮን ቤቶችን ለመርጨት የሚያስችል የፀረ ወባ ትንኝ ኬሚካል ተገዝቷል። ወደ ወረዳዎች ለማሰራጨትም ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

አሁን ላይ ኢትዮጵያ ወባ በሽታን ለዘለቄታው በመከላከሉ ብሎም በማስወገዱ ረገድ በዚህ መልኩ እየሰራች ትገኛለች። በተለይም ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ ሪፖርት የተደረገችውን የወባ አስተላላፊ ትንኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የድርጊት መርሐ ግብር ተዘጋጅቷል። መርሐ ግብሩ ወደ ትግበራ የገባበት ሁኔታ አለ። በተጨማሪም ወባን ለማስወገድ የሚረዱ ሰነዶችን የወባ ማስወገድ ፍኖተ ካርታ፣ የወባ ማስወገድ አፈጻጸም መመርያዎችና ፎርማቶች የሚመለከታቸውን የፌዴራል፣ የክልልና የአጋር ድርጅቶች ባለሙያዎች በማሳተፍ ክለሳ እንደተደረገበትም ዳይሬክተሯ ተናግረዋል። የመከላከሉን ግንዛቤ በሕብረተሰቡ ዘንድ ከመፍጠሩ አንፃር የተሰሩ ሥራዎች መኖራቸውን ያወሱት ዳይሬክተሯ ለምሳሌ በተከለሱ መመሪያዎችና ማንዋሎች ላይ ከአገሪቱ ክልሎች ተመልምለው በወባ ማስወገድ ላይ ለሚሰማሩ ባለሙዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል። በስልጠናው 1 ሺህ 825 ባለሙያዎች መሳተፍ የቻሉ ሲሆን ከዚሁ ጋር የተያያዘ የበጀት ድጋፍም ተደርጓል።

በአጠቃላይ የወባ በሽታ ወቅታዊ ስርጭትን አስመልክቶ ‹‹አሁን ላይ ወባ በሽታ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍሎች በወረርሽኝ መልክ አልተከሰተም›› የሚሉት ዳይሬክተሯ ሊከሰት ያልቻለው መከላከል ላይ ያተኮሩ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች በመሰራታቸው እንደሆነም አበክረው ይናገራሉ። በተለይ ደግሞ የበሽታውን ወቅታዊ ስርጭትን አስመልክቶ የተወሰኑትን ዘርዝረዋቸዋል። አንዱም ለውሳኔ አሰጣጥ በሚረዳ መልኩ ለመተንተን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን አስፈላጊው እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል። የህሙማን ቁጥር በጨመረባቸው አካባቢዎች ባለሙያዎች ተመድበው ሙያዊ ድጋፍ እየሰጡ የሚገኙበት ሁኔታ አለ። የመረሐ ግብሩን አተገባበር ከበፊቱ የተሻለና የተሳለጠ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ ለሁሉም ክልሎች ከ280 ሚሊዮን ብር በላይ ተልኳል ብለዋል።

በመከላከል ስራው ላይ የገጠሙ አንዳንድ ተግዳሮቶችንም ሲያነሱ መድሃኒቶችና መመርመሪያ መሣሪያዎች በበቂ ደረጃ ቢሰራጭም በአንዳንድ ጤና ተቋማት ላይ የስርጭት መቆራረጥ ፤ በሕብረተሰቡ ዘንድ የተሰራጩ አጎበሮችን በአግባቡ አለመጠቀምና ለሌላ ተግባር ማዋል እንደ ችግር አንስተዋል። የአካባቢ ቁጥጥር ሥራዎች ላይ የማህበረሰብ ተሳትፎ መቀነስ፤ በሽታውን ከማስወገድ አንፃር በሽታው ቀንሷል በሚል መዘናጋት እንዲሁም በባለድርሻዎች ዘንድ ተገቢውን ትኩረት አለመስጠትና በአንዳንድ አካባቢዎች በፀጥታ ችግር ምክንያት ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት እንቅፋት መሆን ከገጠሙ ተግዳሮቶች ይጠቀሳሉ ሲሉም አብራርተዋል።

እንደ ዳይሪክተሯ በነዚህ ተግዳሮቶች ምክንያት ዘንድሮ በከምባታ ጠንባሮ፤ በቤንች ሸካ ዞን፤ በምዕራብ አርሲና ምስራቅ ወለጋ ፤በኢሉባቦር፤ በአማራ ክልል ምዕራብና ማዕከላዊ ጎንደር ወረዳዎች የመጨመር አዝማሚያ ተስተውሏል። ሆኖም በ2013 በጀት ዓመት የወባን ስርጭት ምጣኔ በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 1ነጥብ 7 ሚሊዮን ወደ 1ነጥብ 2 ሚሊዮን መቀነስ ተችሏል። በወባ ምክንያት የሚሞቱ ህሙማንን ምጣኔም ከ 0 ነጥብ 39 በመቶ ወደ 0 ነጥብ 28 በመቶ መቀነስ የተቻለበት ሁኔታ ተስፋ ሰጪ መሆኑን ተናግረዋል



ፎቶ፡- በፀሐይ ንጉሴ

ወይዘሮ ሕይወት ሰለሞን በጤና ሚኒስቴር የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ዳይሬክተር

# ነፃ ሃሳብ



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## የፓርላማችን ውሎ ያስታወሰን ቁምነገሮች

**ታሪካዊ ዳራ፤**

የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ፖለቲካ በፓርላሜንታዊ ሥርዓት መመራት ከጀመረ አንድ ክፍለ ዘመን ሊሞላው የቀረው አሥር ያህል ዓመት ብቻ ነው። ፓርላማው የመቶ ዓመት እድሜ ሻማውን የሚለኩሰው፤ አራት ቀሪ የሥልጣን ዓመታት ከፊቱ የሚጠብቁት የዛሬው "የብልጽግና መንግሥት" ሩጫውን ጨርሶ (ዕድል ከቀናውም በሁለተኛ ተርም የሥልጣን ቤትኛነቱን ሊያስቀጥል ይችላል) እና ከእርሱ በኋላ የሚከተለው መጻኢው ወራሴ መንግሥት አምስት ዓመቱን አጠቃሎ ለተረኛው ሦስተኛ ሸንጎ በሚያስረክብበት የመጨረሻው ዓመት ግድም ነው። 3650 ቀናት ያረገዘው አሥሩ ዓመት ሩቅ መስሎ እንዳያዘናጋን እኛ ተመሪዎችም ሆንን የእኛ መሪዎች "ዕድሜና ቁረንጮ ተበጣጥሶ ማለቁን" ልብ ልንል ይገባል። ወንበረተኞቹም ቢሆኑ "ቀን ሳለ" ለሕዝቡ እንቆቅልሽ መፍትሔ መስጠቱ ላይ ቢረባረቡ ይበጃቸዋል።

የዕድሜን ነገር ከጠቃቀስን ዘንዳ የፓርላማችንን ያለፉትን ዘመናት ዜና መዋዕል በወፍ በረር ቅኝትም ቢሆን አስታውሶ ማለፉ ተገቢነት ይኖረዋል። "የኢትዮጵያ መሬትም፣ ሕዝቡም፣ ሕጉም በጠቅላላው የንጉሠ ነገሥቱ ነው" (ክፍል ሁለት)፤ በሚል ጠቅላይነት ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በችሮታነት "በተሰጠው ሕገ መንግሥት" የቆመው የመጀመሪያው ፓርላማ ሥራውን በይፋ የጀመረው ጥቅምት 23 ቀን 1924 ዓ.ም ነበር።

"የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኢየሩሳሌም ንጉሥ ከሰሎሞንና ንግሥተ ሣባ ከተባለችው ከኢትዮጵያ ንግሥት ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ተያይዞ ከመጣው ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘር ከተወለደው ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ እንዳይወጣ ተወስኗል (ክፍል 3)፤ በሚል "በሞአ አንበሳዊ" ውርስ በፀና የብረት ግንብ በታጠረው ሕገ መንግሥት ሥራውን "ሀ" ብሎ የጀመረው ፓርላማ የቆየው እስከ ፋሽስት ወረራ እስከ 1928 ዓ.ም ድረስ ነበር።

ወራሪው የፋሽስት ሠራዊት በሽንፈት ከተባረረ በኋላ ፓርላማው እንደገና አንሰራርቶ ሥራውን የጀመረው በ1935 ዓ.ም ነበር። ለአሥራ አምስት ዓመታት ያህል ተግባሩን ያከናወነው ይህ ፓርላማ በሕገ መንግሥቱ ላይ ክለሳ ተደርጎ "ከሕዝብ በተመረጡ" በተባለላቸው "ተወካዮች" አማካይነት ሥራውን ያስረከበው በ1948 ዓ.ም ሲሆን፤ ሁለተኛው የንጉሡ ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ በቆየባቸው 20 ዓመታት ውስጥም አምስት ያህል ጊዜያት የፓርላማ "ምርጫ" ተደርጓል።

የአፄው ሥርዓተ መንግሥት የአርባ ዓመታት ጉዞና የፓርላማው የወንበር ሥልጣን ያከተመው ወታደራዊው ደርግ ሥልጣኑን በተቆጣጠረበት በ1967 ዓ.ም ነበር። የደርግ መንግሥትም በፊናው፤ 835 "የሕዝብ እንደራሴዎችን" ያቀፈውን የፓርላማ ሥርዓት ያቋቋመው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢሕዲሪ) መንግሥት የተቋቋመበት ሕገ መንግሥት ጥር 24 ቀን 1979 ዓ.ም ከጸደቀ በኋላ ነበር።

"የዝሆኖች ሸንጎ" በመባል የሚታወቀውና አንዲቱን ተርም እንኳን ለመጨረስ ያልታደለው ያ የኢህዲሪ ፓርላማ የቅጽል ስያሜውን ያገኘው የአሸናፊዎቹ ወንበረተኞች የምርጫ ምልክት በሙሉ "ዝሆን" እንዲሆን ኢሠፓ በወሰነው መሠረት ነበር። በፈጠጠ የድርጅታዊ አሠራር መንበሩን የተቆጣጠረው የዚያ ሸንጎ የምርጫ ሂደት "ተጨፈኑና ላሞኛችሁ" ይሉት ዓይነት አሠራሩን ጊዜው ሲፈቅድ በዝርዝር እንመለስበታለን።

"የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ በሠራተኛውና በገበሬው ኅብረት፣ በምሁሩ፣ በአብዮታዊ ሠራዊት፣ በዕደ ጥበብ ባለሙያውና በሌሎች ዴሞክራሲያዊ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ መንግሥት ነው (አንቀጽ 1፡1)" የተባለለት አዲሱ ኢሠፓውያን የተሰባሰቡበትና ከደርግ አገዛዝ ወደ ኢሕዴሪ ተለወጠ የተባለለት ሥርዓተ መንግሥት ቆይታው እስከ 1983 ዓ.ም ለአራት ዓመታት ያህል ብቻ ነበር።

**በ**ስድስተኛው ዙር ምርጫም "ድምጻችን ድምጽህ ነው" ብለን የመረጥነው የብልጽግናው ገዢያችን እየመራ ያለው የ27 ዓመት ዕድሜ ያስቆጠረው ነባሩ ሕገ መንግሥት ባጎናጸፈው "በትረ ሙሴ" አማካይነት ስለሆነ ደፈር ብለን ለምሥጋና፤ ጨከን ብለንም የሕገ መንግሥቱን ሰነድ ለመተቸት ጊዜው ስላይደለና "የያዘን ስለሚይዘን" ትዝብታችንን አምቀን "በሆድ ይፍጀው" ብሂል ማለፉን መርጠናል። "እንዲህ ያለ ነገር ለወሬም አይመች" ያለው ድምጻዊ ማን ነበር?

በሀገራችን መንግሥታዊ ሥርዓት በሦስተኛነት የፓርላሜንታዊ ሥርዓት የሚጠቀሰው "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ" ፍልስፍና አራማጁ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት ነው። ኅዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም የጸደቀውና "ከ550 የማይበልጡ" የወንበረተኞቹን ቁጥር የወሰነው ሕገ መንግሥት (የቁጥሩን ብዛት በተመለከተ ታማኝ ባይሆንም)፤ ለስድስት ያህል ጊዜያት የምክር ቤት አባላት "ስመ ምርጫ" ተካሂዶበታል።

በስድስተኛው ዙር ምርጫም "ድምጻችን ድምጽህ ነው" ብለን የመረጥነው የብልጽግናው ገዢያችን እየመራ ያለው የ27 ዓመት ዕድሜ ያስቆጠረው ነባሩ ሕገ መንግሥት ባጎናጸፈው "በትረ ሙሴ" አማካይነት ስለሆነ ደፈር ብለን ለምሥጋና፤ ጨከን ብለንም የሕገ መንግሥቱን ሰነድ ለመተቸት ጊዜው ስላይደለና "የያዘን ስለሚይዘን" ትዝብታችንን አምቀን "በሆድ ይፍጀው" ብሂል ማለፉን መርጠናል። "እንዲህ ያለ ነገር ለወሬም አይመች" ያለው ድምጻዊ ማን ነበር?

**የፓርላማችን ክራሞት፤**

ከአሁን ቀደም በፓርላማችን አዋዋልና በተከበሩ አንዳንድ የምክር ቤት አባላት ዙሪያ በሕዝብ መካከል የሚያሳዩትን የማይመጥናቸውን ተግባር በተመለከተ በመረጃና በማስረጃ አስደግፌ ተደጋጋሚ ትዝብቴን በዚሁ ጋዜጣ ላይ መግለጼ ይታወሳል - ለምን ቢሉ "ተወካዮቻችን ነበሩዋ!"። "የፓርላማው የሰዓት ደውል" እንኳን ሳይቀር በምን ምክንያት ልሳኑ ሊዘጋ እንደቻለ የዓለም አቀፍ ታሪኮችን ዳራ እያጣቀስኩ "ለሰሚዎቹ ይድረስ!" ማለቴን አስታውሳለሁ።

በዚህ አጋጣሚ በወቅቱ ጽሑፉን ያነበቡት ክብርት የፓርላማው ጽ/ቤት ኃላፊ ስልክ ደውለው ዝምታ ያረበበትን የፓርላማውን የሰዓት ደውል በተመለከተ የችግሩን ምክንያት ካስረዱኝ በኋላ ፈጣን "የጥገና" ምላሽ እንደተሰጠው ገልጸውልኝ ነበር። ክብርት ኃላፊዋን ዛሬም ደግሜ አመሰግናቸዋለሁ። ወደ አራት ኪሎ ብቅ ስል ልብ ተቀልብ ሆኜ ጆሮዬን አልሰጠሁ ከሆነ ይቅርታ አይነፈገኝና ዛሬስ ቢሆን በፓርላማችን የሕንጻ አናት ላይ ተሰቅሎ ከታዳጊነት ዕድሜ እስከ ዛሬው ጉልምስናችን በድምጹና በቀስቃሽነቱ ትዝታው በውስጣችን የተተከለው "የሰዓት ደውል" ሥራውን እየሠራ ይሆን ወይንስ እንደለመደው አሸልቧል?

**የበቀደሙ ውሎ…**

ሰኔ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ክቡር የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) ከተከበረው የተወካዮች ሸንጎ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የተገኙበትን ጉባኤ የተከታተልኩት ልቤንም ጆሮዬንም ከፍቼ ነበር። በአጠቃላይ የዕለቱ የውሎ መርሃ ግብር መልካም ነበር ማለት ይቻላል። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሕዝብ ተወካዮቹ ለተነሱት ጥያቄዎችም የሰጧቸው ዝርዝር ምላሾች አጥጋቢና ጊዜውን የዋጁ ነበሩ።

ተጨማሪ እውቀት የሚያስጨብጡት ገለጻዎችም ቦታቸውንና ዐውዱን አገናዝበዋል የሚል ጥቅል አስተያየት አለኝ። በግሌ ከሌሎች ውሎዎች በተለየ አኳኋን ፓርላማው እንደዚያ ተነቃቅቶ በማየቴ የዘራኋት ቅንጣቷ የምርጫ ካርዴ የተመኘሁትን ፍሬ አፍርታለች የሚል ስሜት አጭሮብኛል።

በአንዳንድ የጥያቄዎች ይዘት ላይ ግን ብዥታ ተፈጥሮብኛል። ጉዳዩን እንደማሳነስ አይቆጠርና፤ ፓርላማው የፌዴራል አጀንዳዎች የሚስተናገዱበት መድረክ እንጂ "የእኔ የምርጫ አካባቢ" እየተባለ ከራስ ሰፈር ድልድይ ግንባታ መጓተት እስከ የውስጥ ለውስጥ ጥርጊያ መንገድ ሥራ መዘግየት ድረስ ዝቅ ያሉ ችግሮች የሚተረኩበት ትክክለኛ ቦታ አይመስለኝም (ምሳሌዎቼ ለማሳያነት የተጠቀሱ መሆናቸውን ልብ ይሏል)።

ለመሆኑ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የቀበሌ ወዘተ. እየተባለ የሸንጎ መዋቅሩ ተዘርግቶ የለ? እኒህን መሰል ችግር የሚስተዋልባቸውን አካባቢዎች ወክለው ለተመረጡ "የየአካባቢው ተመራጮች" እስከ ክልል ምክር ቤት ድረስ ጉዳዩን ለማሳወቅ ዕድሉ ወለል ተደርጎ የተከፈተላቸው የፓርላማው እንደራሴዎች ለምን በየደረጃው ካሉ የየክልሉ ሹማምንት ጋር ተነጋግረው ግፊት አያደርጉም? እነዚህን መሰል የፌዴራል መንግሥት ሥልጣን ያልሆኑ ችግሮችን ለማንሳት በርግጡ ፓርላማው ትክክለኛ ቦታ ነው? "ጥያቄ አቅርቤያለሁ መልስ ብትሰጡኝ…" አለ ድምጻዊው።

እስከ ዛሬ ያልገባኝና ሊገባኝ ያልቻለ ወይንም የሚያስረዳኝን ሰው ያላገኘሁለትን አንድ ሁለት ግርታዬን ልፈነጣጥቅ። የተከበሩ የምክር ቤቱ አባላት በሺህና በሚሊዮን የሚቆጠር የመራጮችን ድምጽ ያገኙት ፓርቲያቸው ደጀን ስለሆናቸው ወይንም የዕድል በለስ ስለቀናቸው ብቻ አይመስለኝም። በፓርቲያቸው ግምገማ መሠረት "በንቃትም ሆነ በመሪነታቸው ተሰጥኦ የወከሉትን ሕዝብ ሊመጥኑ ይችላሉ" ተብሎ ታምኖባቸው እንደሆነ እንገምታለን።

እንዲዚያ ከሆነ ዘንዳ ጥያቄያቸውን በሚመለከተው የፓርላማው አካል በኩል አስመዝግበው በተፈቀደላቸው ደቂቆች በአጭሩና በተብራራ ሁኔታ በቃላቸው ከማቅረብ ይልቅ "ጥያቄዎቼንና አስተያየቶቼን በንባብ አሰማለሁ" የሚሉት ባህል በርግጡ ለዘጠና ዓመት አረጋዊ ፓርላማ የሚመጥን ወግ ነው? ሰዓት ለመቆጠብ ይሆን ወይንስ ሃሳብ እንዳይሸራረፍ ለመቆጣጠር? ምንም ሆነ ምን ይህ ባህል፤ "ተቀመጥ በወንበሬ፤ ተናገር በከንፈሬ" የሚለውን የሕዝብ እምነት የሚወክል አይመስለንም። ማሳመኛ ካለ ይሞግቱን።

እንደ ኮሚዩኒኬሽን ባለሙያ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ማለት ቢቻልም በገጽ ውሱንነት ብቻ ሃሳቡን ፈንጥቆ ማለፉ ይበጅ ይመስለናል። በንግግር ተሟግቶ መርታትና መረታት እያለ በጽሑፍ፤ ያውም በእንደነገሩ የአነባበብ ዘይቤ ተወካዮቹን መሸበብ በግሌ አዋጭ አይመስለኝም። የጥያቄ አቀራረቡ ለምን እንዲህ እንዲሆን እንደተፈለገም የሚያስረዳን ብናገኝ አንጠላም።

የወንበረተኞቹ የስብሰባ አካሄድ መመሪያ ላይም ማብራሪያ ቢሰጥበት ከውዥንብር ያድነናል። በቀዳሚው የትምህርታችን ሥርዓት በየትምህርት ቤቱ ይካሄድ የነበረው የክርክር ፕሮግራም ክሽፈት ያስከተለው ውጤት ለንግግር አይናፋርነት ዳርጎንም ከሆነ ጉዳዩ በትምህርት ሥርዓቱ መሪ ተቋም በኩል ቢጠና ክፋት የለውም። በነገራችን ላይ እንዲህ ዓይነቱ ልማድ በቀዳሚዎቹ የንጉሡና የኢሠፓ ሁለት ሸንጎዎች ላይ ጎልቶ የሚታይ ባህል አልነበረም።

ከነካካን አይቀር "ዴሞክራሲው ያጎናጸፈንን የመራጭነት መብት" በመጠቀም ደፈር ብለን አንድ ጉዳይ እናንሳ። እያንዳንዱ የሕዝብ ተወካይ አስተያየቱንና ጥያቄዎቹን ከመጀመሩ አስቀድሞ "ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ጥያቄዎቻችንን ለመመለስ በመሃከላችን ስለተገኙ እናመሠግናለን" ብሎ በጅምላ መንደርደር ፋይዳው ምኑ ላይ ነው? "ተወካዮቹ የሚተዳደሩበት የሥነ ምግባር መመሪያ ስለሚያስገድድ ነው!" ቢባል እንኳን፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራሳቸው ይሄንን መወድስ ስለመውደዳቸው እርግጠኞች አይደለንም።

በተከበሩት አፈ ጉባዔው በኩል አስቀድሞ ምስጋናው በጅምላ ውክልና ቢቀርብና ቀጥታ ወደ ጉዳዩ መግባቱ አይሻልም? መቼም ይሄ የመረጥንበት ካርድ "የተወካዮቻችንን" ውሎ በሚገባ እንድንፈትሽ ስለሚያበረታታንና ዋስትናም ስለሚሰጠን ያልገባንን መጠየቁ ተገቢነት ይኖረዋል። በዚህ ጸሐፊ እምነት ግን ምሥጋናው አንዴ ከቀረበ በቂና ከበቂ በላይ ስለሆነ በቀጥታ ጥያቄን ወይንም አስተያየትን ማቅረቡ የተሻለ የሚሆን ይመስለናል።

የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን አጥንተውና መርምረው፣ የሀገራቸውን ጉዳይ ጠለቅ አድርገው በመፈተሽ በመረጃ የተደገፈና "ዋው!" የሚያሰኝ የመሟገቻ ሃሳብ ይዘው የሚቀርቡ "ተወካዮችን" ማየት የዚህ ጸሐፊ ምኞትና ናፍቆት ነው። ለምን የሌላውን ሀገር የሸንጎ አባላት አዋዋል እያየንና እያደመጥን በመንፈሳዊ ቅናት እንቃጠላለን? ፈጣሪ ሆይ "እንደ ልባችን" የምንላቸውን ተወካዮች እባክህ አብዝተህ ስጠን!?

የሕግ አውጪነትን ከፍተኛ ሥልጣን የተሰጠው ይህ የሕዝብ ተወካዮች ሸንጎ "ምክር ቤት" የሚለው ስያሜስ አያንስበትም ይሆን? ፓርላማ የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ከምክክርም ከፍ ያለ የወሳኝነት ሥልጣን ስላለው ዛሬም ባይሆን ወደፊት "ሕገ መንግሥታችን" ለሕዝብ ውይይት ቀርቦ ሲፈተሽና ሲበጠር ይህ የስያሜ ጉዳይ ትኩረት እንዳይነፈገው ከወዲሁ ይታሰብበት እንላለን። ታዲያ ምን ይባል? ከተባለም፤ በጊዜው አማራጭ ሃሳቦችን ለማቅረብ የቤት ሥራውን ከወዲሁ እንወስዳለን።

ጽሑፎቼን አዘውትሮ የሚያነብ አድናቂዬ ባፋጠጠኝ አንድ ወሳኝ ጥያቄ ልደምድም። "ለመሆኑ አንድ የሕዝብ እንደራሴ (በተለይም በፓርቲ ጥላ ሥር ተጠልሎ ምክር ቤት የገባ ተወካይ) ወገንተኝነቱ ለማን ነው? ቤተኛ ለሆነበትና ላስመረጠው ፓርቲ ወይንስ ‹አለኝታ ሁነኝ› ብሎ ለመረጠው ሕዝብ?" ጥሬውን ጥያቄ እንዳለ የወረወርኩት ሃሳቡን የሚያበስልልን ያገባኛል ባይ አለሁ እንዲለን ነው። ለጠያቂዬ ብቻም ሳይሆን ለእኔውም ቢሆን ግር ስለሚለኝ ምላሹን የምጠባበቀው በትእግስትና ልብ ተቀልብ ሆኜ በመጓጓት እንደሆነ መሸሸግ አልፈልግም። ሰላም ይሁን!

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ለሰው ቀመር ቀንበር አንሁን

ተገኝ ብሩ

ሁሌም በሰዎች ተፅእኖ ጉዳዮችን የምንመለከት፣ ሌሎች አስበውና አልመው ባወጡት መርሀ የምንመራ፣ በሰዎች አስተሳሰብ እራሳችንን የምንመረምር፣ ከግል ስብዕናና አቋም የራቅን ብዙዎች አለን። እንዴት የራሳችንን ቀለም አደብዝዘን ሌላን ለመሆን እንጥራለን ጎበዝ? ስለምን ያልሆነውን የሌሎችን ማንነት እንላበሳለን? እኛነታችን እኛው የሰራነው፣ መነሻና መድረሻችን እኛው ያሰመርነው ዓላማና ግብ የለየን፤ ያንን ለማሳካት የሚያስችል ቁመናን የተላበስንና በራስ መተማመን ያጎለበትን መሆን ይገባናል።

ሰዎች ብዙውን ጊዜ በራሳቸው መንገድ ርቀው የመጓዝ ልምድ የላቸውም። ያለ ሌሎች እርዳታ አንድም እርምጃ መራመድና ፍላጎታቸውን አልያም አላማቸውን ለማሳካት የሌሎች እርዳታ የግድ ነው ብለው የሚያምኑ ብዙዎች ናቸው። በእርግጥ ከሰዎች ጋር የግል ዓላማችንን ለማሳካት መተጋገዝና መረዳዳት ሊኖርብን ይችልላል። ነገር ግን በሁለት እግራችን ለመቆምና ዓላማችንን ለማሳካት የሌሎች ጥገኛ መሆን አይኖርብንም።

"ምን ነገር በራሴ እወጣዋለሁ" ብለን በራስ መተማመናችንን ማጎልበት ለራሳችን ዋጋ መስጠት ይኖርብናል። አዎን እኔ ያለማንም እርዳታ ጉዳዮችን በራሴ መንገድ የመመርመርና የራሴን አቋም የመግለጽ ሙሉዕነት የተላበስኩ ነኝ ብሎ ማመን ይገባናል። በዚህ መንገድ ርቀው መሄድ የሚችሉት ደግሞ በራስ መተማመናቸው ከፍ ያለና ስኬታማም ናቸው። ልኬታችንን አውቀን በዚያ ልክ እራሳችንን በሚገባን ቦታ ማስቀመጥም ይገባል። እኛን በሚመጥን ልክ ስለኛ የሚሆን ለእኛም የሚበጅ ምን እንደሆነ እኛው ለእኛው መምረጥ ይኖርብናል።

ሰዎች የእኛን ምርጫ ሊመርጡልን ዓላማና ግባችንን ሊያሳኩልን ሳይሆን እንድናሳካ የሚያግዙን እንጂ ለሌሎች ግብና ዓላማ ማሳኪያ ቁስ ሊያደርጉን አይገባም። ጎበዝ ድንበር ይኑረን እንጂ፤ ለራሳችን የምናሰምረው ለልኬታችን የሚስማማ በእኛ ልክ ወደኛ የከለልነው ወደሌሎችም ተሻግረን የማንሄድበት ድንበር እናብጅ።

እኔ ያልኩት ድንበር ይሄ ከጎረቤታችን ጋር በአጥር የከለልነው የኔ ወሰን ይሄ ነው፤ የአንተ ደግሞ ወዲያ እያልን የምንለውን አይደለም። ድንበር የምለው፤ በስብዕናችን ውስጥ እኛን መስለን እኛ ሆነን በራሳችን የምንቆምበት ከሌላ የምንለይበት የራሳችን ማንነትና አቋም የምናንፀባርቅበት ማንነት ነው። ያ ድንበር በእኛና በሌሎች መካከል ያለ እኛ የራሳችንን የምንፈልገውና ያሻን በራሳችን ዛቢያ የምንከውንበት ከሌሎች ተፅዕኖ ነፃ ሆነን በራሳችን የራሳችን ቀለም የምንፈካበት ድንበር ነው።

አዎን እኛ በራሳችን ልክ የራሳችን የምንለው ድንበርማ ያሻናል። ሰዎች ከራሳችን አቋምና መርህ በአጋጣሚ ቀርበው የእነሱን ሊጭኑብን የምንገባ መሆን የለብንም። በእርግጥ ከእኛ የሆነውን ለሌሎች አንሰጥም፣ እኛም ጋር የጎደለውን ከሌላው አንቀበልም እያልኩ አይደለም። እያልኩ ያለሁት በሌሎች ትርኪ ምርኪ ወይም ሚዛን የሌለው ሃሳብና እቅድ አንመራ ነው። የራሳችን አቅጣጫና ግብ ይኑረን ነው።

የራሳችን መስመር እናብጅ፤ ያ መስመር ደግሞ እኛው ለእራሳችን በምንሰጠው ዋጋ ልክ መሆን ይገባዋል ነው። ታዲያ ይሄን መስመር ስናሰምር በልካችን ይሁን ሌሎች እንደኛ ያሰመሩትን ድንበራቸው የማንገፋ እኛም ሰፍቶ የሚያስቸግረን ሳይሆን በእኛው ልክ የተለካ ይሁን ነው። በሌላ አባባል በልካችን በአቋማችንና በመርሀችን መደራደር የለብንም ማለት ነው።

ያ የእኛ የሆነው መርህና ያሰመርነው ድንበር ለሌሎች አሳልፈን የማንሰጥ የሌሎችም መብት እና መርህ የምናከብር በዚያም ውስጥ በጥበብ የምንኖር መሆን ይኖርብል። እኛ ሰዎች ስንባል የእኛነታችን መገለጫ የሆነው ስብዕና የተላበሰ፣ በሰዎች እኩልነት የሚያምን፣ መብትና ግዴታውን ለመወጣት የሚጥር፣ አገራዊ ፍቅሩን በተግባር የሚያረጋግጥ፣ ፅኑ የሆነ ዜጋ የራሱ መርህ ያለው የማይብረከረክ አቋም የተላበስን ልንሆን ይገባል።

በመርህ የሚመራና በራስ መተማመኑ ከፍ ያለ ዜጋ የማይደራደርባቸው፣ በማያወላዳ መልኩ ለግቡ መሳካት ያስቀመጣቸው ጉዳዮች መሳካት ሁሌም የማይታክት ቆራጥ ነው። በዚህ በቡድን በሚፈረጅበትና አንድ የራስ የሆነ አቋም መያዝ ግድ በሚልበት ወቅት በተለይ የራስን ያልተበረዘ አዎንታዊ እሳቤን ይዞ መቆም በራስ መተማመን ማሳያ ነው።

ሰዎች በጋራ የፈረጁት ጉዳይ በራሳችን በተለየ አተያይ የምንመለከት ስንቶቻችን ነን። አዎን ተሰባስበው አንድን ጉዳይ በተመሳሳይ መልኩ ሲኮንኑ ሲያወግዙና አንድ የሆኑ ያህል ጉዳዩን ተገቢ ባልሆነ መልኩ እየተመለከቱት እንኳን አይ ልክ አይደላችሁም፤ እስኪ በዚያ መልክ ደግሞ ተመልከቱት ማለት እንዴት ይሳነናል። እኛም በሰዎች ምልከታ የእኛን አመለካከትና እይታ ሸፍነን መመሳሰሉ ቀሎናል።

እንዴት ሁልጊዜ ትችትና ነቀፋ ዋነኛ መርሀችን ይሆናል፣በጎን አለመመልከት ደግሞ የዘወትር ልማዳችን ይሆናል ጎበዝ? ያየነውን ስህተት የምናነውረውን ያህል የሚሰራውን በጎ ነገር እንዴት ቢያንስ ጥሩ ነው ማለት ያቅተናል። ጎበዝ እስኪ ቆም ብለን አካሄዳችን እንመልከት፤ ትችታችን ገደብ አላለፈም? ጉዳዮችን በበጎ ተመልክተን ከምንሰጠው አስተያየት ይልቅ ትችትና መዛለፋችን አልበዛም? እንዴት በዚህ መልኩ በመንጋ ስንፈርድና በደቡ ስንዛለፍ አይ ይሄ ነገር ቆም ብለን በሌላ መልኩ እንመርምረው ማለት ያቅተን።

ወንድሜ በጎ ዜና እንደ ኮሶ መሮህ የሸብር፣ የመለያየት፣ የጦርነትና ግጭት ወሬ እንደ ማር የሚጣፍጥህ ከሆነ ባልሰማኸውና ባላየኸው እንዲሁ ባሉ ብቻ የራስህን አቋም አሽቀንጥረህ ጥለህ የሌሎችን አቋም ላይ ከቆምክ ጤነኝነት አይደለምና እራስህን መርምር። ጥሩ ንግግርን ንቀሽ የማይጠቅምሽ ላይ ካዘወተርሽ፣ እውነታን አሳንሰሽ ያልተጨበጠው ላይ ጊዜሽን ከፈጀሽ አንቺ ከከሳሪዎቹ ተርታ ነሽ።

ጎበዝ ነገሮችን በንቃት እንመልከት እንጂ። የራሳችን የሆነ መርህ በራሳችን ሁኔታዎች አይተን የምንመዝን እንሁን እንጂ። እኛ እስከመቼ የሰዎች ሀሳብ ተሸካሚ የሰዎችን ቀመር ቀንበር የምንሆነው። ባሉ ብቻ ሳታመዛዝን አንተም ፈራጅ ከሆንክ ያየኸውን ጉዳይ በጎነት አንዴም ሳታወራ ነገሮችን ሁሉ በትችትና በነቀፌታ የምትመለከት ከሆነ ሚዛን ስተሀል።

ሚዛን ከሳትክና በራስህ የማትመራ ከሆነ ሁሌም ወሬህ ፅልመትን አግዝፎ የሚያሳይ ብርሃንን የከለለ ከሆነ ወዳጄ አንተ አደጋ ውስጥ ነህ። እንዴት መልካም ነገር መልካም መሆኑን መመስከር ሳትችል በጎ አስተያየቱን መለገስ ይሳንሀል። ይህ ፈፅሞ የሚጣረስ ነውና እራሰህን ከራስህ ጋር አስታርቀው።

በአንፃሩ ደግሞ መጥፎው ከመልካሙ አብልጠህ ማግዘፍ በየትኛው አተያይ ልክ ሊሆን ይችላል ብለህ አሰብክ። ጤናማ አተያይ መላበስ ሚዛናዊ ምልከታ እጅጉን ያስፈልጋል። ልኬት የተዛባ ነገር በትክክለኛ ክብደቱ ለማወቅ ያግዛል። ጉዳዮችን በሚዛን መመልከት ጥሩ ነው። ጎበዝ እራሳችንን ከዚህ የተዛባ ምልከታ እናርቅ። ፅልመትን ደጋግሞ ማመላከት ከብርሀናማ ሕይወት ያርቃል። በጎ ከምንለው አስሳሰብ፤ ሰላም ከምንለው የፍስሀ መነሻ በብዙ ያርቃል። በራስ መተማመናችን በማጎልበት የሌሎች ሀሳብና እሳቤ ማረፊያ እንዳይሆን እራሳችን ላይ መስራት ይኖርብናል። አበቃሁ፤ ቸር ይግጠመን።

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ከሳውዲ ኤምባሲ ፊት ለፊት ያለውን መንገድ በጀማል ኻሾግጂ ስም ሰየመች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ዋሸንግተን የሚገኘው የሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ ፊት ለፊት የሚገኘው መንገድ ጀማል ኻሾግጂ በሚል ተሰየመ። ጋዜጠኛ ጀማል ኻሾግጂ በሳውዲ አረቢያ የደኅንነት አባላት ቱርክ ውስጥ ከተገደለ በኋላ በመላው ዓለም መነጋገሪያ ሆኗል።

የአሜሪካ ርዕሰ ከተማ አስተዳዳሪ ስያሜው ጀማል ኻሾግጂ መንገድ መባሉ የጋዜጠኛው ሞት "እንዳይሸፋፈን ያግዛል" ብለዋል።

የአሜሪካ ደኅንነት ግድያውን በተመለከተ በደረሰው ድምዳሜ ላይ የሳውዲው ልዑል አልጋ ወራሽ ሞሐመድ ቢን ሳልማን ግድያው እንዲፈጸም ውሳኔ ሰጥተዋል። ልዑሉ ግን ያስተባብላሉ።

በሚቀጥለው ሳምንት ልዑሉ ከአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ተገናኝተው ይመክራሉ።

የመንገዱ ስያሜ በጋዜጠኛው ስም መሆኑን በማስመልከት የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች፣ የአሜሪካ የኮንግረስ አባላት እና የአካባቢው ባለሥልጣናት ተገኝተዋል።

"ከዚያ አጥር ጀርባ የተደበቁት ሰዎች በየቀኑ፣ በየሰዓቱ ይህ የጀማል ኻሾግጂ መንገድ መሆኑን እንዲያስታውሱ ለማድረግ ያለመ ነው" ያሉት የዴሞክራሲ ፎር ዘ አረብ ዎርልድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሳራ ሊያ ናቸው።

ድርጅቱ በጀማል ኻሾግጂ የተቋቋመ ቡድን ነው። ሳውዲ አረቢያዊው ጋዜጠኛ መቀመጫውን አሜሪካ አድርጎ የነበረ ሲሆን ለዋሽንግተን ፖስትም ይጽፍ ነበር።

ጋዜጠኛው እአአ በ2018 ኢስታንቡል በሚገኘው የሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ ውስጥ በአገሪቱ ደኅንነት አባላት ተገድሏል።




ጀማል ኻሾግጂ መንገድ

የአሜሪካ ደኅንነት ጉዳዩን በቀጥታ ከልዑል ሞሐመድ ጋር አያይዘውታል። ልዑሉ ግን በግድያው ውስጥ እጃቸው እንደሌለበት አስተባብለዋል። የሳውዲ ዐቃቤ ሕጎች ገዳዮቹ "ሕገ ወጥ" ወኪሎች ናቸው ሲሉ ይከሳሉ።

ግድያው ቁጣን የቀሰቀሰ ሲሆን ልዑሉም ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዲገለሉ አድርጓል።

የዴሞክራቲክ ፓርቲ ፕሬዚዳንታዊ ዕጩ ለመሆን በሚፎካከሩበት ወቅት ፕሬዚዳንት ባይደን "ሳውዲ ዓረቢያ ለሠራችው ሥራ ዋጋዋን እንድታገኝ አደርጋለሁ" ሲሉ በግድያው ዙሪያ ተናግረው ነበር።

ማክሰኞ ዕለት ዋይት ሐውስ እንዳስታወቀው ባይደን በመካከለኛው ምሥራቅ በሚኖራቸው ጉብኝት ከልዑል ሞሐመድ ጋር ፊት ለፊት ይገናኛሉ።

የባይደን አስተዳደር ከፍተኛ ባለሥልጣን እንዳሉት የሰብዓዊ መብት ጉዳይ ከውይይቶቹ አጀንዳዎች አንዱ ነው። ሌሎች ደግሞ ውይይቱ ሳውዲ ምንም መሻሻል ሳታሳይ ዕውቅና ሊሰጣት ይችላል ሲሉ ያስጠነቅቃሉ።

ዋሸንግተን በተገደሉ ሰዎች ስም ከኤምባሲዎች ፊት ለፊት መንገድ ስትሰይም ጀማል ኻሾግጂ የመጀመሪያው መንገድ አይደለም።

እአአ በ2015 በክሬምሊን ለተገደለው ቦሪስ ኔምሶቭ መታሰቢያ እንዲሆን የከተማዋ አስተዳደር የሩሲያ ኤምባሲ ፊት ለፊት የሚገኘውን መንገድ በግለሰቡ ስም ሰይሞታል።

## ዩክሬን በአስቸኳይ የአውሮፓ ሕብረት ዕጩ አባል እንድትሆን ድጋፍ አገኘች

በጋዜጣው ሪፖርተር

የፈረንሳይ፣ የጀርመን፣ የጣሊያ እና የሩሜኒያ መሪዎች ዩክሬን የአውሮፓ ኅብረት አባል እንድትሆን የተዘጋጀውን ረቂቅ የደገፉት ሲሆን "በአስቸኳይ" የኅብረቱ ዕጩ አባል መሆን አለባትም ብለዋል።

በኪዬቭ በተደረገው የጋራ ስብሰባ ላይ የጀርመኑ መራሔ መንግሥት ኦላፍ ሾልዝ "ዩክሬን የአውሮፓ ቤተሰብ መሆን ይገባታል" ብለዋል። ሆኖም አሁንም ዩክሬን ማሟላት የሚጠበቅባት መስፈርቶችን አላሟላችም ብለዋል።

በሌላ በኩል የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን 27ቱ የአውሮፓ ኅብረት አባል አገራት ዩክሬን ሩሲያ ላይ ድል እስክትቀዳጅ ድርስ ከጎኗ ልንቆም ይገባል ሲሉ አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮላድሚር ዜሌንስኪ የሩሲያ በአውሮፓ አንድነት ላይ ጦርነት አውጃለች ያሉ ሲሆን፣ እጅግ ውጤታማው መሣሪያም አንድነት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በተጨማሪም ዩክሬን ራሷን እንድትከላከልና በሞስኮ የተያዙባትን ቦታዎች ለማስመለስ በአስቸኳይ ተጨማሪ



የአውሮፓ አገራት መሪዎች ከዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ጋር

የጦር መሳሪያዎች እንዲቀርቡላት ተማጽነዋል።

ትላንትና አራት የአውሮፓ ኅብረት መሪዎች ከኪዬቭ አቅራቢያ የምትገኘውን እና በሩሲያ ቁጥጥር ስር የነበረችውን ኢርፒን የተሰኘችውን ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባትን ከተማ ጎብኝተዋል።

በዚህችም ከተማም ይሁን በአቅራቢያዋ ባለችው ቡቻ በተባለችው ከተማ የሩሲያ ወታደሮች የጦር ወንጀል ፈጽመዋል ስትል ዩክሬን ትከሳለች። ሆኖም ሞስኮ ይህንን ክስ ታስተባብላለች።

የአውሮፓ ኅብረት መሪዎች ኪዬቭን በሚጎበኙበት ወቅት የሩሲያ ወታደሮች በምሥራቅ ዩክሬን በምትገኘውን ሴቬርዶንስቲክ ከተማ ላይ ጥቃት መፈጸማቸውን ቀጥለዋል።

ሴቬርዶንስቲክ እና ሊሲሼንክ ከተሞች መቆጣጠር ለሳምንታት የሩሲያ ቀዳሚ ወታደራዊ ግብ ሆኖ የቆየ ሲሆን ሞስኮ ሉሃንሳክ የተባለውን ክልል ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር ፍላጎቷ አካል ነው ተብሏል።

የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ማክሮን፣ የጀርመኑ መራሔ መንግሥት ሾልዝ፣ የጣልያኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ማሪዮ ድራጊ እና የሩሜኒያው ፕሬዚዳንት ክሉስ ለሆኒስ በጋራ ኪዬቭን የጎበኙ ሲሆን፣ ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ ሀገሪቱን ሲጎበኙ ይህ የመጀመሪያ ነው ተብሏል።

መሪዎቹ ኪዬቭን ከመጎብኘታቸው አንድ ቀን ቀደም ብሎ የአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽን ዩክሬንን በዕጩነት ደረጃ የኅብረቱ አባል እንደትሆን ምክረ ሃሳብ አቅርቦ ነበር።

በሚቀጥለው ሳምንት 27ቱ የአውሮፓ ኅብረት አባል አገራት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት እንደሚገናኙ ይጠበቃል።

የተወሰኑ የአውሮፓ ኅብረት አባል አገራት ዩክሬን አባል እንድትሆን ፍላጎታቸው እምብዛም ሲሆን፣ በኅብረቱ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ፈረንሳይ፣ ጀርመንና ጣሊያን ቀስ በቅስ አቋማቸውን ሊቀይሩ እንደሚችል ይታመናል።

ሆኖም በዕጩነት ደረጃ ተቀባይነት ማግኘት ዓመታትን ሊፈጅ ለሚችለው ሙሉ አባልነት የሚረዳ እርምጃ እንጂ ከዚያ የዘለለ ጥቅም አይኖረውም።

የአውሮፓ ኅብረት መሪዎች ኪዬቭን ከመጎብኘታቸው በፊት የዩክሬን ባለሥልጣናት በተደጋጋሚ ፈረንሳይ፣ ጀርመን እና ጣሊያን በፍጥነት መሣሪያ አላቀረቡልንም በሚል ሲወቀሱ ቆይተዋል።

በዚህ ወር መጀመሪያ ፕሬዚዳንት ማክሮን ሩሲያ ዩክሬንን በመውረሯ ልናዋርዳት አይገባም ሲሉ ተደምጠዋል። ፕሬዝዳንት ፑቲን ለፈጸሙት "መሰረታዊ ስህተት" መውጫ ሊሰጣቸው ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ለፌዴራል መስሪያ ቤቶች ኪራይ የሚወጣውን ወጪ የማስቀረት ጥረት

**መሳኩ ኤሮሴ**

የኢትዮጵያ መንግሥት ለፌዴራል መስሪያ ቤቶች ዓመታዊ ኪራይ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚያወጣ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር መረጃ ያሳያል። ጥቂት የማይባሉ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች የራሳቸው ቢሮ የሌላቸው ከመሆኑ የተነሳ ተከራይተው አገልግሎት ይሰጣሉ። የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ህንጻዎችን ለመከራየት የሚያወጧቸው ወጪ አገሪቱ ለሌሎች መሠረተ-ልማቶች ታውል የነበረውን ከፍተኛ መዋዕለ-ነዋይ ለኪራይ ወጪ በመዳረጉ ለአገሪቷ እድገት እንቅፋት እንደሚሆን ይታመናል።

ለእድገት እንቅፋት ከመሆኑም በላይ የመንግሥት መስሪያ ቤቶቹ ተከራይተው የሚሰሩባቸው አብዛኞቹ ህንጻዎች መስሪያ ቤቶቹ መደበኛ ሥራዎቻቸውን ለማከናወን የማይመቹ፣ ለሥራ ተነሳሽነት የማያበረታቱና የማይማርኩ፣ ለተገልጋይ ደንበኛም ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት የማይጋብዙ ናቸው። ከዚያ ባሻገር መስሪያ ቤቶቹ ቋሚ አድራሻ ስለማይኖራቸው ተገልጋይ ደንበኞችን ለእንግልት ሲዳርጋቸውም ይስተዋላል።

ለህንጻዎቹ ኪራይ መንግሥት የሚያወጣውን ወጪ እና ሌሎች ተያያዥ ችግሮችን ለማስቀረት ፕሮጀክት ቀርጾ በርካታ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይቷል። ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በመንግሥት ውሳኔ መሠረት የፌዴራል መንግሥት ህንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በሚል ስያሜ የተቋቋመ ተቋምን ዘርግቶ ዘመናዊና ጥራታቸውን የጠበቁ፣ በዋጋ ተደራሽ፣ በታቀደው ጊዜ ተጠናቅቀው ለሥራ ምቹ የሆኑ የሥራ አካባቢዎችን መፍጠር እንዲቻል ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኝ የከተማ እና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር መረጃ ያሳያል፡፡

ከዚህ ቀደም በርካታ ህንጻዎች ተገንብተው ሥራ ላይ የዋሉ ሲሆን፤ ሥራ ላይ ከዋሉት መካከል የጤና ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር፣ የፌዴራል ኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተር፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ቢሮ፣ የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር ቢሮ፣ የማዕከላዊ ስታስቲክስ ቢሮ፣ የፌዴራል መሬት ተቋማት ቢሮ፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ቢሮ፣ የአገልግሎት ዘመናቸውን ላጠናቀቁ የመንግሥትና የአገር መሪዎች የመኖርያ ቤት፣ የብሔራዊ የመረጃ ደህንነት አገልግሎት፣ የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የህንጻ ግንባታዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት ጥቅም ላይ ከዋሉት ህንጻዎች በተጨማሪ ግንባታቸው ለተጠናቀቁት ህንጻዎች የኢንሳ፣ የቪ አይፒ መኖሪያ፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች እና የፌዴራል ዳኞች መኖሪያ ዲዛይን ለማዘጋጀት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ የተከናወነ ሲሆን የፌዴራል ዳኞች መኖሪያ አፓርትመንት ህንጻ ግንባታ የማስተካከያ እርማት በማድረግ የመጨረሻ ርክክብ እንዲፈጸም አስፈላጊው ሁሉ ርብርብ እየተደረገ እንደሚገኝም ጠቁመዋል፡፡

ይህን እንጂ አሁንም በርካታ የፌዴራል መንግሥት ህንጻዎች በግንባታ ላይ ናቸው። በመገንባት ላይ ከሚገኙት ህንጻዎች መካከል የፌዴራል ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ የቢሮ ህንጻ፣ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት ህንጻ፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ህንጻ፣ ኢትዮጵያ የሲቪል አቪዬሽን የቢሮ ህንጻ፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቲያትር ፕሮጀክቶች፣ የቀድሞ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት የነበረበት እየተገነባ ያለው 4 ቤዝመንት + ጂ+16 ኮምፕሌክስ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ህንጻዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በመገንባት ላይ የሚገኙ የመንግሥት ህንጻዎች የግንባታዎች መጠናቀቅ ምቹ የሥራ አካባቢን ከመፍጠር ባሻገር በመሀል ከተማ ተመሳሳይ ህንጻዎች ተገንብተው ለከተማዋ እይታ የገጽታ ግንባታ የሚያስገኙት ፋይዳ የጎላ ከመሆኑ ባለፈ ከፍተኛ ዓመታዊ የቤት ኪራይ ወጪን ለማስቀረት እንደሚያስችል የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ጠቁሟል፡፡

በዚህ ዘርፍ የተሠማሩ ተዋናዮች ተጠቃሚው ዜጋ፣ አሠሪዎችና ባለሙያዎች ለዘርፉ ዕድገት የሚኖራቸው



**እየተገነቡ ካሉ የፌዴራል መንግሥት ሕንጻዎች አንዱ፤**

አስተዋፅኦ የማይተካ ሲሆን፣ የአማካሪዎችና ተቋራጮች ማህበራት ሚናም ለዘርፉ እድገትና ሙያዊ ሥነ-ምግባር መከበር እጅግ የላቀ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

ሰሞኑን የሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸውን የ2014 በጀት ዓመት የ10 ወራት አፈጻጸም ሪፖርት ያቀረቡት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ የፌዴራል መንግሥት ህንጻዎች ግንባታና አስተዳደርን በተመለከተ በሰጡት ማብራሪያ፤ በአጠቃላይ የመንግሥት ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

ባለፉት 10 ወራት ውስጥ የፌዴራል ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ የቢሮ ህንጻ ግንባታን 14 ነጥብ 69 በመቶ ግንባታ ለመስራት ታቅዶ እንደነበር ጠቁመው፤ በተለያዩ ምክንያቶች ከእቅድ በታች 9 ነጥብ 2 በመቶ ግን መከናወኑን እና የፕሮጀክቱ አፈጻጸሙ 63 ነጥብ 17 በመቶ ላይ እንደሚገኝ አብራርተዋል። እንዲሁም የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት ህንጻ ግንባታ 40 በመቶ ለመስራት ታቅዶ 27 ነጥብ 85 በማከናወን አጠቃላይ አፈጻጸሙ 69 በመቶ መድረሱን ተናግረዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ማብራሪያ፤ በተለያየ የግንባታ ደረጃዎች ላይ የሚገኙ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ህንጻዎች ግንባታ መቶ በመቶ ለመፈጸም ታቅዶ ነበር። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሜትሮሎጂ አጀንሲ ሎት አንድ ግንባታ 42 ነጥብ 68 በመቶ ለመሥራት ታቅዶ 25 ነጥብ 61 በማከናወን 58 ነጥብ 7 በመቶ ማድረስ የተቻለ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ሎት 2 ህንጻ ግንባታ 38 በመቶ ለመስራት ታቅዶ 31 ነጥብ 71 በማከናወን 83 ነጥብ 4 በመቶ ማድረስ መቻሉን ነው ያብራሩት፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ማብራሪያ፤ ለቀድሞ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት፣ ታስቦ የነበረውና በአሁኑ ወቅት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር 4 ቤዝመንት + የጂ+16 ኮምፕሌክስ ህንጻ ግንባታ 15 ነጥብ 25 በመቶ ግንባታ ለማከናወን 2 ነጥብ 76 በመቶ ግንባታ ተከናውኗል። በተመሳሳይ ኢትዮጵያ የሲቪል አቪዬሽን የቢሮ ህንጻ ግንባታ 16 በመቶ ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ ሥራ ተቋራጭ መረጣ ጊዜ በመውሰዱ ወደ ሥራ ሳይገባ በመቅረቱ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ሊሆን ችሏል።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር ቤትን ለማዘመን ቴአትር ቤቱ በሚገኝበት ስፍራ ዘመናዊ አዲስ ህንጻ ለመገንባት ታቅዶ ግንባታው ቢጀመርም ከአንድ ዓመት በፊት ባጋጠመው መጓተት ሊቋረጥ ችሎ ነበር። በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ተመድቦለት ነበር። ሚኒስትሯ እንደተናገሩት ባለፉት 10 ወራት የ 17 ነጥብ 06 በመቶ ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ምንም አልተገነባም ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ የመንግሥት ህንጻ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዝቅተኛ የሆነበት በርካታ ምክንያቶችን የዘረዘሩ ሲሆን፤ ዋነኛው ምክንያት ከቀድሞ ኮንትራክተሮች ጋር የነበረው ውል ተቋርጦ አዲስ ውል ከሌሎች ኮንትራክተሮች ጋር ለመግባት ሰፊ ጊዜ የወሰደ መሆኑ አንዱ ምክንያት ነው። የመንግሥት ፕሮጀክቶችን የሚገነቡ ነባር ኮንትራክተሮች ውል ለማቋረጥ ህጋዊ አሰራር ተከትሎ የሚከናወን መሆኑ ጊዜ የሚጠይቅ ነው። ከዚያ ባሻገር አዳዲስ ኮንትራክተሮችን ለማስገባት እንዲሁ ጊዜ ጠይቋል ይህም በፕሮጀክቶች ላይ ለተስተዋለው መጓተት የራሱን ሚና ማበርከቱን ነው የጠቆሙት።

ወቅታዊ የኮንትራክሽን ግብዓት ዋጋ መናር እና አቅርቦት ዝቅተኛ መሆን፤ በተለይ የሲሚንቶ አቅርቦት ዝቅተኛ መሆን እና በሚፈለገው ልክ አለመገኘት ለፕሮጀክቶቹ መጓተት ሌላኛው ምክንያት ሆኗል።

ሚኒስትሯ በሪፖርታቸው እንደጠቆሙት፤ የፕሮጀክት ማኔጅመንት፣ የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅም ውስንነት ለአፈጻጸም ማነስ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል። የፕሮጀክት ማኔጅመንት ክህሎት ማነስ፣ አመራርና የሙያተኛ የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅም ውስንነት፤ የተንዛዛ የግዥ ሥርዓትና አሰራር መኖር፣ የግንባታ ግብዓት ዓለም አቀፍ ዋጋ ንረት ለፕሮጀክቶቹ መጓተት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ናቸው።

በዘላቂነት የመንግሥት ህንጻ ፕሮጀክቶችን ለመሥራት እንዲቻል የፌዴራል ቤቶች ባህሪን መሰረት ያደረገ ጥናት ተደርጎ አራት አይነት ዲዛይኖች ተዘጋጅተዋል። በቀጣይም የፌዴራል መንግሥት ህንጻ ፕሮጀክቶች የአሰራር ማዕቀፍ ውስጥ እደሚካተቱም ጠቁመዋል፡፡

በኢፌዴሪ ፓርላማ የከተማ መሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በአዲስ አባባ በተለያዩ አካባቢዎች የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ህንጻ ግንባታ አፈጻፀምን ጎብኝቷል። ቋሚ ኮሚቴው ባደረገው የመስክ ምልከታ ከተመለከታቸው የመንግሥት ህንጻዎች ውስጥ የንግድ ሚኒስቴር፣ ብሄራዊ ቲያትር፣ የፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ እና የብሄራዊ ሜትሮሎጅ ህንጻ ግንባታዎች ይገኙበታል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው አባላት የህንጻ ግንባታዎች መጓተት መንግሥትን ለአላስፈላጊ እና ተጨማሪ ወጪ እየዳረገው መሆኑን ጠቁመዋል። የተጀመሩ የመንግሥት መስሪያ ቤት የህንጻ ግንባታዎች በተቀመጠላቸው እቅድ መሰረት እንዲጠናቀቁ ተገቢውን ክትትል እንዲያደረግ የፌዴራል መንግሥት ህንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽቤትን አሳስበዋል።

ተቋራጮች በበኩላቸው የውጭ ምንዛሬ እጥረት እና በግንባታ እቃዎች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ መኖር ለግንባታ ሥራ አፈፃፀም እንቅፋት እንደሆነባቸው እና የዲዛይን ሥራ ተሟልቶ አለመቅረብን በችግርነት አንስተዋል። የፌዴራል መንግሥት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ተክለፃዲቅ ተክለአረጋይ በበኩላቸው በተቋራጮች በኩል የሚታዩ ድክመቶችን በማረም በኩል ውል ከማቋረጥ ጀምሮ የተለያዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ እንደሆነና በተቋራጮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት እየሰሩ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ሸዊት ሸንካ በበኩላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የህንጻ ግንባታዎች መጓተት እንደሚታይባቸው እና የሕዝብ ሀብት ለብክነት እና ለተጨማሪ ወጪ እየተዳረገ በመሆኑ ሊታረም እንደሚገባ አሳስበዋል። አክለውም ግንባታዎቹ በተቀመጠላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ተገቢው ክትትል እና በተጓተቱ ግንባታዎች ላይም የማካካስ ሥራ መሠራት እንዳለበትም አስገንዝበዋል፡፡

የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ህንጻ ግንባታ ጨምሮ የተለያዩ ግንባታ ሥራዎች እንዲጓተት መንስኤ እየሆኑ ያሉ ችግሮችን በተለይም የኮንትራክሽን ግብዓት ዋጋ መናር እና አቅርቦት ዝቅተኛ መሆን፤ የፕሮጀክት ማኔጅመት፣ የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅም ውስንነት ለአፈጻጸም ማነስ፤ የተንዛዛ የግዥ ሥርዓትና አሰራር መኖር ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

# መጋቢ አዕምሮ

# ለመደራደር መንደርደር

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

ከሰሞኑ የምንሰማው የሰላም ወሬ መሰረት የያዘ ሆኖ ደም የመቀባቱ ምዕራፍ መቆም ይችል ዘንድ በማሰብ ከዚህ በፊት ይቅርታ፤ አይቅር ብለን ያስነበብነው ጽሁፍ "ለመደራደር መንደርደር" ብለን አቅርበነዋል። የሀገሬ ልጆች ቆም ብለን የሰላምን መንገድ በጋራ ፈልገን ወደ ውጤት የምንደርስበት ወቅት ነው። ሁላችንም የሰላምን ዜና በማስተጋባት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ውጤት እንዲደርስ መሻቴን እገልጻለሁ። በምናብ ታሪካችን እንጀምር።

የምናብ ታሪካችን ወደ ችሎት ይወስደናል። ለመጀመሪያ ጊዜ በፍርድ ቤት ችሎት ለመገኘት የተገኙ እናትን በችሎት የተነገረ አስተያየትን። እኚህ እናት አስቀድመው በተለያዩ ቦታዎች ላይ ስለ ብዙ ጉዳይ የሆነን ሰፊ ሰልፍ ተመልክተዋል። ቀበሌ ሄደው ከሸማቾች ለመግዛት ተሰልፈዋል። ዳቦ ለመግዛት ተሰልፈዋል። አውቶብስ ወረፋ ለመያዝ ተሰልፈዋል። ዛሬ ደግሞ ፍርድ ቤት መጥተው በሰው ጋጋታ ውስጥ ናቸው። ፍርድቤትም የሰው ጋጋታ ይኖራል ብለው ፈፅሞ አልጠበቁም።

የፍርድ ቤቱ መዝገብ ክፍል እጅግ ብዙ በሆነ መዝገብ ተሞልቶ ሲመለከቱ ግርምትን ፈጥሮባቸዋል። በየችሎቱ ስማቸው እየተጠራ ለመግባት ጥሪ የሚጠብቁትን የሰዎችን ትርምስምስ ተመልክተው እርሳቸውን ለፍርድቤት በር የዳረጋቸውን ጎረቤታቸውን "ምን አደረኩህ ልጄ?" አሉት። እርሳቸው የሚያውቁት እንደ ባህላችን በሽማግሌ ችግርን እየፈቱ በይቅርታም ሁሉም አሸናፊ እንደሚሆኑ ነው።

እማማ ከችሎት ያስገኛቸው ሁለት ተከራዮቻቸው እርስበእርስ ተጣልተው ምስክር ሆነው መጠራታቸው ነው። እማማ በትርምሱ ውስጥ ሆነው ንግግራቸውን በመቀጠል "ልጆቼ እዚህ ሁሉ ነገር ውስጥ ከመግባት ምናለ በጓዳችን መክረን ችግራችንን ብንፈታ? እዚህ እንግልት ውስጥ በመግባት ጊዜያችሁን ገንዘባችሁን ለምን ታጠፋላችሁ? በመነጋገር ችግራችንን ፈተን በይቅርታ ብናልፈው አይሻልም?"አሉ። ከሳሽ ተከራይም ለምስክርነት የጠራቸውን አከራዩን "እማማ በይቅርታ ችግሩን መፍታት ያሉት እንኳን ይቅር፤ ይቅርታ እያልን አንተም ተው አንተም ተው በሚል ነገሮች እየተባባሰባቸው ሄዱ እንጂ መፍትሔ አላመጣም። ያለኝ አማራጭ በህግ ፊት መፋረድ ነው" አላቸው።

እማማም "ይቅርታው እንኳን ይቅር" የሚለውን አገላለፅ መላልሰው እያሰቡ ብዙ በሃሳብ ሄዱ። በይቅርታ በህይወት ዘመናቸው ያለፉትን ትልልቅ ጥፋት እያሰቡ ከራሳቸው ጋር አወሩ። ደም የተቃቡ ሰዎች እንኳን ነገራቸውን በሽማግሌ እግር ስር አስቀምጠው ችግርን እየፈቱ በኖሩበት ዘመን ውስጥ እንዲህ ቀላል ጉዳዮች ወደ አደባባይ ደርሰው ወረፋ ሲይዙምአስገረማቸው። ይቅርታ ሲቀር አብሮ መኖር የማይቻልበት እርስ በእርስ በጎሪጥ እየተያዩ መመላለስን የሚያመጣ አንዱ አሸናፊ ለመሆን ሌላውም ላለመሸነፍ ሁሉም ተሸናፊ ሆኖ እንደሚኖር በመረዳት ከራሳቸው ጋር መከሩ።

ችሎቱ ድረሱ ባላቸው ሰዓት ቢደርሱም ችሎቱ በሰዓቱ ሊጠራቸው ባለመቻሉ የመድኃኒት ሰዓት ደረሰባቸው። አዛውንቷ አከራይ ለጡረታቸው ብለው የሰሯቸውን የሰርቪስ ክፍል ቤትን በማከራየት ገቢ ያገኛሉ። የተከራዮቻቸው ፀብ ወደ ችሎት አምጥቷቸው የመድኃኒት ሰዓታቸውን አዛባባቸው። ይህም ችሎቱ የማይመዘግበው ወጪያቸው ነበር። የችሎቱ ሰዓት ደርሶም ተጠሩ። የምስክር ቃልም መሰማት ጀመረ እማማም ወደ ዳኛው እየተመለከቱ "ልጄ እኔ ምስክር ሆኜ የመጣሁት ያየሁትን ለመመስከር ነው።

እርሱንም አደርጋለሁ። ነገርግን የእናንተንም ሰዓት ላለመሻማት ሁሉንም ነገር ሰዎች እዚህ ይዘው ሲመጡ ለምን ትቀበላላችሁ? አንዳንዱን በአካባቢ ሽማግሌዎች በወጋችን ለምን አንፈታውም? አሁን እኔም የመድኃኒት ሰዓቴ ደርሶ እዚህ መምጣቴ አግባብ ነው?እንዴት ሰው ተነጋግሮ ይቅርታ በመጠያየቅ ውስጥ ያለውን ግሩም መፍትሔ ትቶ ይጠላለፋል?" አሉ። የችሎቱ ዳኛም የችሎት ስርዓትን አላከበሩም ብሎ ከዚህ በላይ እንዳይናገሩ አስቆማቸው።

እማማም ‹‹ዳግመኛ እግሬን አላነሳም›› እያሉ ከራሳቸው ጋር እያወሩ ምስክርነታቸውን አሰምተው ተመለሱ። ሁለቱም ተከራዮች ወደ ሰፈር ሲመለሱ እማማን ማንገላታታቸው ያስቆጫቸው በመሆኑ እማማን ሽማግሌ አድርገው ነገራቸውን ለመፍታት ተስማሙ። እማማ በሽምግልናቸው ካሳ ቢበይኑ ለመካካስ፤ ይቅርታም በቦታው ሥራውን እንዲሰራም ተስማሙ። እንደ እማማ አይነት የሚገሰፅ ኖሮ ችግሮችን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መፍታት ቢቻል ምንኛ መልካም በሆነ ነበር።አለመግባባትን በመቀነስ፤ ሲፈጠርም በአነስተኛ ዋጋ ለመፍታት በመስራት።

### አለመግባባት

የሰዎች ልጅ በረጅም ታሪኩ ውስጥ ግጭት በጉልህ የሚታይ ነው። የሰው ልጅ ከግጭት ተፋቶ መኖር የማይችል ነው ብለን መደምደም እስክንችል ድረስ የሚያደርስ የግጭት ታሪክ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በጉልህ ይገኛል። ሰው አጠገቡ ካለው ሰው ጋር የመወዳጀትም ሆነ የመጋጨትን ጊዜዎችን ሊያሳልፍ ይችላል፤ ደግሞም ነው። አለመግባባት አድጎ ወደ ግጭት ሲያመራም ኪሳራው ይከተላል። ኪሳራውም በቀላሉ የሚከፈል ወይንም ፈጽሞውኑ የማይከፈል ሆኖም ያልፋል። የሰው ልጅ ህይወት ፈጽሞውኑ የማይከፈል ኪሳራ ውስጥ ተመድቦ እናገኘዋለን።

ግጭት ክቡር የሆነውን የሰውን ልጅ እየቀጠፈ ባለበት በዚህ ጊዜ ስለግጭት ማስረዳት አንባቢውን ማሰልቸት ሊሆን ይችላል። የግጭት መነሻ የሚሆንን አለመግባባትን ወደ መግባባት ለመቀየር ሊሰራ የሚገባው ሥራ ካልተሰራ አለመግባባት ግጭትን እያበዛ የሚቀጥል መሆኑ አይቀሬ እንደሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው።

አለመግባባት በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር የሚችል ሲሆን ዋናው ጉዳይ ግን አለመግባባት እንዳይፈጠር ለማድረግ መሞከር፤ ከተሞከረም ፍሬያማ በሆነ በአነስተኛ ዋጋ ሊፈታ የሚችልበትን መንገድ መፈለግ ነው። አለመግባባት ወደ ውጤት እንዳይመጣ የሚያደርገው ኢ-ፍትሃዊነት ዋናው ጉዳይ ነው። አንድ አካል እኔ ብቻ የፈለኩትን ላድርግ አንተ ግን ፍላጎትህን አምቀህ ኑር ቢል ይህ ኢ-ፍትሃዊነትን አለመግባባትን፤ አለመግባባትም ግጭትን ይፈጥራል።

ከትላንት ታሪካችን እንደ አገር መማር እንዳንችል በአብዛኛው አንዱ የሌላኛውን ጥፋት ለማሳየት የሚሄደውን ያህል ራሱ ምን ያህል ለችግር አስተዋጽኦ እንዳደረገ መመልከት አለመቻሉ ነው። እያንዳንዱ ሰው የሚፈጥረውን ኢ-ፍትሃዊነት ወደ ጎን አድርጎ ሌሎች የሚፈጥሩትን ችግር የምናጎላ ከሆነ ወደ መፍትሔ መድረስ ሳንችል ቀርተን በአለመግባባትና በግጭት አዙሪት እንከርማለን። የመፍትሔ መንገዱ ብዙ ቢሆንም በዚህ ጽሁፍ የፍላጎት ልዩነትን ማጥበብንና የይቅርታን በር እንደ መፍትሔ እናነሳቸዋለን።

### የፍላጎቶች ልዩነት

በአካባቢያችን ያሉ ልጆችን ስንመለከት ከምንረዳቸው ነገሮች መካከል አንዱ እርስበእርስ የሚኖራቸው ግጭት የሚነሳበት ዋና ምክንያት ይገኛል። ልጆች አብረው ሲሆኑ ሲጫወቱ፣ ሲያጠኑ ወይም ሲመገቡ በአጠቃላይ በሰላም ቆይተው በቅፅበት ድብልቅልቅ ያለ ፀብ ውስጥ ገብተው ልናገኛቸው እንችላለን። ቅድም ደማቅ በሆነ ጨዋታ ውስጥ የነበሩት ልጆች እንዴት በቅጽበት ጩኸት ወደ በረከተበት ፀብ ሊያመሩ ቻሉ ብለን ብንጠይቅ ምላሹ ከመካከላቸው አንዱ ኢ-ፍትሃዊነት የገጠመው መሆኑን እንረዳለን። ልጆቹ በተስማሙበት ህግ መሰረት ጨዋታው ሳይሄድ ሲቀር፤ አንዱ ልጅ የእርሱን ድርሻ የተነጠቀ ሲመስለው ግጭት ይፈጠራል። የቅድሙ ፍቅር በቅፅበት ወደ ፀብ ይቀየራል።

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ኢ-ፍትሃዊነትን መቀበል የማይችል በመሆኑ የፍላጎቶች ልዩነት መኖሩ የሚያመጣው አለመግባባት በቀላሉ የሚታይ አይደለም። መፍትሄው ፍትሃዊነትን በማስፈን ፍላጎትን ማቀራረብ እንጂ አስቀድሞ የሆነውን በማድረግ የተለየ ውጤት መጠበቅ አይደለም። ህፃናት ለመቀበል የሚቸግራቸውን ኢ-ፍትሃዊነት አዋቂ ሰው በተለይም የእውቀት ነፃነት የመረጃ ፍሰት ከፍተኛ በሆነበት ዘመን ሊቀበል የሚችልበት እድሉ አነስተኛ ነው። በመሆኑም አለመግባባትን እየፈታን ሰላማዊ ሕይወትን በግላችን፣ በቤታችን፣ በሥራቦታ መኖርን ስናስብ ልንገነዘብ የሚገባው እውነት ፍላጎቶቹን የማቀራረብን ጥቅም ነው።

የዛሬ 28 ዓመት በሩዋንዳ ውስጥ በእያንዳንዱ ቀን ከ10 ሺ በላይ ሰዎች ይጨፈጨፉ ነበር። ብሔርን ማዕከል አድርጎ የተነሳው ግጭት ለሦስት ወራት ያህል ቀጥሎ ከአንድ ሚሊዮን የማያንሱ ሰዎችን ህይወት ቀጥፎ ምድሪቱ በደም ጎርፍ ተመታ ነበር። ከአንድ ሚሊዮን ሰዎች እንደ አንዱ ከሞት ጋር ፊትለፊት እንደተገናኘ ሰው ሆነን ራሳችንን ስንመለከት ለሰላም የሚሰጥ ዋጋ ያለውን ቦታ እንረዳለን። በጭንቅ ሰዓት የሰላም ትርጉሙ ከፍተኛ መሆኑን እንገነዘባለን። ሰውን በግፍ ከመጨፍጨፍ መለስ በጥሞና ፍላጎቶችን ማቀራረብ ላይ መስራት ቅድሚያ ቢሰጠው ኖሮ በታሪክ ውስጥ አንካሳ ታሪክን ጥሎ ማለፍ ባልሆነ ነበር።

በመግቢያችን ላይ ያነሳነው የፍርድቤቶች መኖር ለሰላም ያላቸው አስተዋጽኦ ቀላል ባይሆንም ፍትህን ለማግኘት ውድ በሆነበት ሁኔታ፤ የፍትህ ስርዓቱም አሸናፊና ተሸናፊ ብሎ በሁለት ጎራ ከፍሎ መዝገቡ በሚዘጋበት ሁኔታ፤ ፍላጎትን አቀራርቦ ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት መንገድ ላይ መገኘትን አዳጋች ሊያደርገው ይችላል። የፍላጎቶች ልዩነት በሰፋ ቁጥር ግጭት አይቀሬ መሆኑን ስንረዳ አንዳችን በሌላችን ጫማ ውስጥ የማሰብን የወርቃማውን ህግ መሰረታዊነት እንረዳለን።

### አንዳችን በሌላችን ጫማ

"ጎረቤቴ የሚለቀው ፍሳሽ ለጤናዬ እክል ሆነብኝ"፤ "ጎረቤቴ የሚያሰማው ድምጽ ሰላም ነሳኝ"፣ "ከጎረቤቴ የሚመጣው ጭስ አላስተኛ አለኝ" ወዘተ ብለው ሰዎች ፍትህን ፍለጋ ወደሚመለከተው አካል ከመሄዳቸው በፊት በሌላኛው ጫማ ውስጥ ቢኬድ ጥሩ ይሆን ነበር። አንዳችን በሌላችን ጫማ ሆነን ማሰብ በተሳነን ጊዜ ተጎድቼያለሁ የሚለው ሰው አለኝ በሚለው መንገድ ፍትህን ይፈልጋል ወይንም የሚፈልገውን ለማድረግ ጥረት ያደርጋል። አንዳችን በሌላችን ጫማ ሆነን ስንገኝ የሰላም አየር አካባቢያችንን ይከበዋል። በተፈጥሮ እናት ለልጆች አንዳች ጥቅምን ፈልጋ ብዙ እርቀት ትሄዳለች። ሰው ሁሉ ይህን እርስበእርሱ ማድረግ ባይችል እንኳን በሞራል ህግ ለእኔ እንዲሆን የምፈልገውን ለሌላው፤ በእኔ ላይ እንዲሆን የማልፈልገውን በሌላው ላይ ወዘተ ብለን ማሰብ ይኖርብናል።

ዋልት ዴዝኒ "አንድን ነገር ለመጀመር ዋናው ነገር ማውራትን አቁሞ የተግባር እርምጃን ማድረግ ነው" እንደሚለው አንዳችን በሌላችን ጫማን ለመተግበር የሚፈልገው የተግባር እርምጃን ብቻ ነው። ግጭትን ለመፍታት በመሄድ ውስጥ አንዳችን በሌላችን ጫማ ውስጥ መሆናችን ጥቅሙ ለሁሉም ነው። ይህም ሁሉ ሆኖ በሰዎች መካከል በተለያየ ምክንያት ግጭት ሊፈጠር ይችላል። በተለይ ከእኛ የሚጠበቀውን ተወጥተን ነገርግን አይቀሬ የሆነ ግጭት ውስጥ ስንገባ መፍትሔው አንዳችን በሌላችን ላይ ቢላ መሳል ሳይሆን ተነጋግሮ በይቅርታ ፋይሉን መዝጋት ነው።

ይቅርታ አይቅር ብለን የምናነሳው ነጥብም የዚህ ጽሑፍ ማጠንጠኛ የሆነበት ምክንያት በይቅርታ ውስጥ ያለውን መንፈሳዊም ሆነ ሥነ-ልቦናዊ ጥቅምን በማሰብ ነው። ለእኛ እንዲሆን የምንፈልገው ስለሆነ። የሰው ልጅ የጋራ ኑሮ ያለይቅርታ ትርጉም ሊኖረው ስለማይችል፤ ይቅርታ አይቅር ብለን ንባባችንን እንቀጥል።

### ይቅርታ አይቅር

ኔልሰን ማንዴላ የሕይወት ታላቁ ክብር "ፈጽሞ አለመውደቅ ሳይሆን በወደቅን ቁጥር መነሳት መቻል ነው" ማለቱ ከመውደቅ መነሳት ዋና በመሆኑ ነው። ይቅርታ ደግሞ ከውድቀት የመነሻ አንዱ ነገር ነው። ሩዋንዳን ያለፉት 28 ዓመታት የሚሊዮን ዜጎችን ህይወት የቀጠፈውን ታሪክ በየዓመቱ እያስታወሰች



ምን ሆነን ነበር ትላለች። ምን ሆነን ነበር የሚለው ጥያቄ ያኔ የመጀመሪያው ቢላ ከሚሳልበት ቅጽበት በፊት ቢሆን ኖሮ ምንኛ ጥሩ በሆነ ነበር። የሆነው ከሆነ በኋላ ግን ችግሩን በይቅርታ ለመፍታት የሄደችበት መንገድ አስተማሪ ነው።

በደቡብ አፍሪካም ታሪክ ውስጥ ለይቅርታ የተሰጠው ቦታ አስተማሪነቱ ብዙ ነው። የከበደውን ቁስል ግን በይቅርታ በማለፍ አዲስን ምእራፍ በስምምነት የመከፈት ምእራፍ። ይቅርታ ያለውን ትልቅ ቦታ የምንረዳው የግድ ጉዳዩ በአገር አቀፍ ደረጃ ባለ ጉዳይ ስለሆነ አይደለም።ዛሬ ብዙሪያችን ካሉ ሰዎች ጋር ያለንን ሰላም መሆን መርምረን የይቅርታ ጉዞችንን መፈተሽ ይኖርብናል። በመነጋገር እና ትላንትናን በእውነተኛ ይቅርታ በመዝጋት ወደ ውጤት ነገሮችን ማምጣት ይቻላል። ይቅርታ አይቅርም የምንለው ለዚህ ነው።

የይቅርታ በቦታው መገኘት እረፍቱ ለበዳይም ለተበዳይም መሆኑን ስንረዳ የሕይወታችን መገለጫ እናደርገዋለን። በዳይ ጥፋቱን እንዲረዳ የሚያደርገው፤ ተበዳይም በሞራል ልእልና ውስጥ ገብቶ ነገሮን ትቶ የሰላምን ኑሮ እንዲኖር የሚረዳው ነው። ግጭት የማይኖርበትን ጊዜ ምድር ላይ ከማለም ግጭት እንዳይፈጠርና ከተፈጠረም እንዴት ሊፈታ እንደሚገባ ማሰቡ የተሻለው ነው። የተሻለውን መንገድ በእርግጥም የተሻለ መሆኑን የሚያስረዳው የይቅርታ አቅም ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ለይቅርታ የሚሰጠውን ቦታ ከፍ አድርጎ ማስቀመጡን የምንረዳው ተበዳይ ወደ በደለው ሰው ሄዶ ይቅርታን እንዲያደርግ የሚጠይቅ በመሆኑ ነው። በዳይ ወደ ተበዳይ ወይንስ ተበዳይ ወደ በዳይ የሚለውን አንባቢ በጥንቃቄ እንዲያስተውል እጠይቃለሁ። ምላሹ ተበዳይ ወደ በዳይ የሚል ነው። በዳይ ወደ ተበዳይ መጥቶ የሚጠይቀውን ይቅርታ ሁላችንም የምናውቀው ቢሆንም በተቃራኒው ሲሆን ግን ግርታን የሚፈጥር ሊሆን ይችላል። ይህ የሚያሳየው ለይቅርታ ሊሰጥ የሚገባው ቦታ ከፍተኛ መሆኑን ነው።

እያንዳንዳችን ለይቅርታ ያለንን ቦታ እንፈትሽ? በትዳር ሕይወታችን ውስጥ ይቅርታ ምን ያህል እየተጠቀምንበት ነው?በሥራ ቦታስ? በምንሳተፍበት የትኛውም አይነት ማህበራዊ መስተጋብርስ? ምናልባትም ከራሳችንስ ጋርስ? አንዳንዴ ግጭቱ ከራሳችን ጋር ይሆንና ለራሳችን ይቅርታን ማድረግ ተስኖን ራሳችንን ለመቅጣት የምንሄድበት መንገድ አለ። ራሳችንን በመጣል የምንሄድበት መንገድ ራስን የመቅጫ መንገድ ሆኖ ሊታይ ይችላል።

ይህ በሆነ ጊዜ ጎልማሶቹ ሥራቸው ላይ የሚያተኩሩ፤ አዛውንቷን ለሽምግልና እንጂ ለማንገላታት ምክንያት የማይሆን፤ ታማሚዎች በአግባቡ አስታማሚ የሚያገኙ መድኃኒታቸውን በጊዜ የሚወስዱበት፤ ልጆች በሰላም ተጫውተው በሰላም ተጋጭተውና ታርቀው ተፈጥሮ ሥራዋን በአግባቡ የምትሰራበት ይሆናል። ለይቅርታ ቦታን ሰጥተን የምናደርገው ውይይትም ሆነ ድርድር ወደ ውጤት የሚያደርሰን ይሆናል። እነሆ ለመደራደር፤ መንደርደር! መንደርደሪያውም ለይቅርታ ቦታ መስጠት!።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## ‹‹ውሎዬ ከማሳ፣ አዳሬም ከአይሱዙ ላይ ነው››

ቃልኪዳን ጠብቀው

**ፍሬሕይወት አወቀ**





ምዕራብ ጎጃም፣ ደምበጫ ከተማ ተወልዳ ያደገችበት አካባቢ ነው።ከትውልድ አካባቢዋ አክስቷ ወዳሉበት አዲስ አበባ ያቀናቸው ገና በጠዋቱ ነበር።ትምህርቷንም በደምበጫ እና አዲስ አበባ ተከታትላ የ10ኛ ክፍል ትምህርቷን አጠናቅቃለች።በትምህርቷ ከ10ኛ ክፍል በላይ ባትዘልቅም በግብርና ሥራ እና በንግዱ ዘርፍ ግን ሰፊ አበርክቶ አላት።ውሎዋን ከእርሻ አዳሯን ደግሞ ምርቶቿን ወደ ገበያ ሽክፎ ከሚንቀሳቀሰው አይሱዙ መኪና ላይ አድርጋለች።

ብዙ ጊዜዋን በእርሻ ቦታ በማድረግ መሬት የሰጠቻትን ምርት ወደ ገበያ አውጥታ ትነግዳለች። ሩጫዋ ከልባችን ምት እኩል ከሚነጉደው ከጊዜ ጋር ነው። ‹‹በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ›› እንዲል ቃሉ፤ ሮጣ በማይደክማት በጉብዝናዋ ወራት ለነብስ ስጋዋ ከላይ ታች በማለት ትታትራለች። ወጣትነቷ ከጨመረላት ትጋትና ሞራል በበለጠ ለሥራ ያላት ተነሳሽነትና ፍላጎት ‹‹አልሠራሁም›› ከሚለው ቁጭቷ ጋር ተዳምሮ የምርት እጥረትና የዋጋ ንረት በተለይም በሽንኩርት ዋጋ ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት ሌት ተቀን ተፍ ተፍ ትላለች።

ሽንኩርት በማምረት ቤተሰቡን የማስተዳደር ኃላፊነት የወደቀበት የወንድሟን ዱካ ተከትላ ወደ ግብርና የገባችው የዕለቱ እንግዳችን ለግብርናው ዘርፍ በተለይም ለመሬት ልዩ ፍቅር አላት።ወንድሟ እያመረተ የሚያቀርበውን ሽንኩርት በመሸጥ ታግዘው የነበረችው የያኔዋ ነጋዴ ያሁኗ አርሶ አደር ነጋዴ፤ ሽንኩርትን ጨምሮ የተለያዩ አትክልቶችን በማምረት ትታወቃለች።የተመረተውን ምርት በአይሱዙ መኪኖቿ በመጫን ሌሊቱን ስትጓዝ አድራ ንግዱን የምታቀላጥፈው የዕለቱ የስኬት እንግዳችን አርሶ አደርና ነጋዴ ቃልኪዳን ጠብቀው ናት።

ቃልኪዳን፤ ከ10 አመት አስቀድማ ወደ ግብርናው ዘርፍ በመሰማራት በተለያዩ አካባቢዎች አትክልትና ፍራፍሬን እያመረተች ለገበያ ታቀርባለች።ያመረተችውን ምርት ከማሳዋ ላይ ማንም ነጋዴ አያነሳውም።በገዛ መኪኖቿ ጭና ወደ አዲስ አበባ ከተማም ይሁን በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ፍላጎት ወዳለበት ታቀርባለች።አምራችና ነጋዴ እንደመሆኗም ‹‹ውሎዬ ከማሳ አዳሬም ከአይሱዙ ላይ ነው›› ትላለች።

ቃልኪዳን ወንድሟ አምርቶ የሚያቀርበውን አትክልት በምትሸጥበት ጊዜ የምርት እጥረትና የዋጋ ንረት የሚከሰተው ብዙ አምራች ባለመኖሩ እንደሆነና ወደ ምርት መግባት እንዳለባት ታስብ ነበር።በዚህ እሳቤ ውስጥ እያለች ታድያ ወንድሟ ከግብርና ሥራው ለቆ መውጣቱ ጥሩ አጋጣሚ እንደሆነላትና በቀጥታ ወደ ማምረት መግባቷን ትናገራለች።

በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በተለይም በሽንኩርት ምርት ላይ በስፋት የተሰማራችው ታታሪዋ አርሶ አደር ነጋዴ፤ ምንም እንኳን አርሶ አደር ከሆነ ቤተሰብ የመጣች ባትሆንም ለግብርና ሥራ ጥልቅ ፍቅር ያላትና ‹‹መሬትን የሚያህል ትልቅ ሀብት ይዘን፤ ወቅት ጠብቆ የሚፈራረቅን ምቹ የአየር ጸባይን ታድለን ለምን ተራብን? ለምንስ ድሆች ሆንን?›› የሚል ቁጭት የወለደውን ጥያቄ ታነሳለች።ለዚህም ‹‹ከዚህ በበለጠ መሥራት ማምረት ባለመቻሌ ነው›› በማለት ራሷን ተወቃሽ ታደርጋለች።

ያደገችበት አካባቢን ጨምሮ አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ሴት ልጅ በዚህ ደረጃ ወጥታ ወርዳ መሥራት የሌለባትና የቤት እመቤት መሆን እንዳለባት ያምናል።የቃልኪዳን ቤተሰቦችም የዚሁ ማህበረሰብ አካል እንደመሆናቸው ሥራዋን አይወዱላትም።የእነርሱ ፍላጎት አግብታና ወልዳ ኑሮ ስትመራ ማየት፤ ይህ ካልሆነ ደግሞ የቢሮ ሠራተኛ መሆን ትልቁ ግባቸው ነውና ሥራዋን አልተቀበሉትም።ካለመቀበላቸውም ባለፈ ከዛሬ ነገ ትታ ትወጣለች የሚል ሀሳብ አላቸው።እርሷ ግን ሁሉንም ተቋቁማ ስኬታማ ገበሬና ነጋዴ ሆናለች፡፡

ከዛሬ 10 ዓመት በፊት ‹‹አፈር ቆፍሬ፣ ጭቃ አቡክቼ መሬት በምትሰጠኝ ምርት እራሴም ተጠቅሜ ለሌሎች እተርፋለሁ›› በማለት ወደ ግብርናው የገባችው ቃልኪዳን፤ ቀዳሚ ምርጫዋ የሆነው ወንድሟ ሲያመርትበት በነበረው ኦሮሚያ ክልል ቦሌኑራሄራ አካባቢ 32 ሄክታር የአርሶ አደር መሬት ተከራይታ መስራት ነበር።ሰፊ የገበሬ መሬት አንድ ቦታ ላይ የማይገኝ በመሆኑ በተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውራ በኪራይ በምታገኘው መሬት የተለያዩ አትክልቶችን የምታመርተው ቃልኪዳን፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመረተችው ቀይ ሽንኩርት እንደነበር ታስታውሳለች።ከቀይ ሽንኩርት ቀጥላም መሬት የማይቀበለው ነገር የለምና ካሮት፣ ቃሪያ፣ ድንች፣ ስኳር ድንች፣ የአበባ ጎመን፣ ሀባብና ሌሎችንም በማምረት ወደ ውጤት አምርታለች።

ቀይና ነጭ ሽንኩርት ለምግብነት ለመድረስ አራት ወራትን የሚፈልጉ ሲሆን፤ በሁለት ወራትና ከዚያም ባነሰ ጊዜ የሚደርሱ ሌሎች አትክልቶች መኖራቸውን የምትናገረው ቃልኪዳን፤ ሽንኩርትን በዓመት አራት ጊዜ እንዲሁም ሌሎች ምርቶችን በዓመት ስድስት ጊዜ አምርታ ለገበያ ታቀርባለች።ያመረተቻቸውን ምርቶችንም የመሸጫ ሱቅ ተከራይታ፣ በዋናነት ኃይሌ ጋርመንትና ሰባራ ባቡር በሚገኘው የአትክልት መሸጫ ቦታ፣ ታቀርባለች፡፡

በኦሮሚያ ክልል ቡሌሄራ አካባቢ የጀመረችው የግብርና ሥራ ተስፋፍቶ በሰመራ ዱፍቲ፣ ገዋኔ፣ መተሃራና ሀረር በሚባሉ አካባቢዎች እና በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ አቃቂ አካባቢ ከአርሶ አደሮች በኪራይ በምታገኘው መሬት የተለያዩ አትክልቶችን በስፋት ታመርታለች።ስፋት ያለው ምርት ደግሞ ሰፊ የገበያ መዳረሻዎችን ይፈልጋልና የአትክልት ምርቶቿን በስፋት ከሚፈለግበት አዲስ አበባ ከተማ በተጨማሪ ሀረር፣ ድሬዳዋ፣ ወለጋ እና ደብረ ማርቆስ ተደራሽ ታደርጋለች፡፡

ከእርሻ ቦታዋ የማትጠፋው ቃልኪዳን፤ ቱታዋን ለብሳ ቦቲ ጫማዋን ተጫምታ በማሳ ውስጥ ካሰማራቻቸው ሠራተኞቿ ጋር እኩል ስትቆፍር፣ ስትዘራ፣ ስትጎለጉልና የደረሰውን ሽንኩርት ስትለቅም ውላ ለሊቱን ደግሞ በአይሱዙ መኪኖቿ ጭና ወደ ገበያ ለማድረስ በውድቅት ለሊት መጓዟ የግድ ነው።ያኔ እህል ውሃ ማለትና ጎን ማሳረፍ ብሎ ነገር አይታሰብም። እዚያው ሽንኩርት ከጫነው መኪናዋ ውስጥ ሆና መንጋቱን ትጠባበቃለች።ጨለማው ለብርሃን ቦታውን ሲለቅ ደግሞ አትክልቶቹን ለገበያ ታቀርባለች።

ብዙ ልፋትና ድካም በሚጠይቀው የግብርና ሥራ አርሶ አደርነትን ከንግድ ጋር በማዋደዷ ምክንያት ውሎዋ ከእርሻ አዳሯም በአይሱዙ የለሊት ጉዞ እንዲሆን የግድ ቢሆንም በሴትነቷ የገጠማት ችግር እንደሌለ ስትገልጽ ‹‹ሴት በመሆኔ የቸገረኝና ወደኋላ የቀረሁበትን ጊዜ አላስታውስም፤ ከዚያ ይልቅ ያልሠራኋቸው በርካታ ሥራዎች እንዳሉና ከዚህ የበለጠ መሥራት ብችል አገሪቷ ላይ የማንኛውም ነገር እጥረት አይገጥማትም›› በሚል ቁጭት ነው።

‹‹የግብርና ሥራ በጭቃ ከመቡካቱ ጀምሮ ሁሉም ነገር የሚያስደስት ነው፤ በተለይም መሬትን አምነን የምንጥላት አንዲት ፍሬ ብዙ ሺ አፍርታ በእጥፍ ስትመልስልን ማየት ከምንም በላይ አስደሳችና ድካምን የሚያስረሳ ነው›› የምትለው ቃልኪዳን፤ ‹‹አንድ ፍሬ ብንሰጠው ታምኖ በብዙ እጥፍ የሚመልስልን ለም መሬት፣ ውሃና ምቹ የአየር ጸባይ እያለን መቸገራችን ባለመሥራታችን ነው።በአገር ውስጥ ያለው ለም መሬት ገና ብዙ የሚያሠራንና ምንም ያልተሠራበት ነው እኔም ሠርቻለሁ ብዬ አላምንም›› ትላለች።

ቃልኪዳን፤ አትክልት ለማልማት በተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ተንቀሳቅሳለች።ታዲያ በሁሉም አካባቢዎች የታዘበችው ነገር ቢኖር የተሰጠንን ጸጋ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ እንዳልተጠቀምንበት ነው።‹‹ምንም ያልተነኩና ጾም እያደሩ ያሉ ክፍት ቦታዎች በምርት ቢሸፈኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ችግር አይወራም።ልቡ ወደ ውጭ አገር የሚሸፍት ወጣትም አይፈጠርም ነበር። አሁንም ቢሆን ጊዜው አልረፈደምና መሬቱም እኛም ጾም ከምናድር ለም የሆነውን መሬታችንን በመጠቀም ምርትና ምርታማነት ላይ ብቻ አተኩረን በመሥራት ድህነትን እናሸንፍ›› በማለት ትናገራለች።

ሹፌሮችንና የሽያጭ ሠራተኞችን ሳይጨምር በቋሚነት ለ959 ሠራተኞች የሥራ ዕድል የፈጠረችው ቃልኪዳን፣ በቀጣይም ይህን ቁጥር በእጥፍ በማሳደግ በተለይም በጎዳና ላይ ያሉትን ወጣቶች አሰልጥና ወደ ሥራ ለማስገባት ሰፊ ዕቅድ አላት።ይህን ዕቅድ ለማሳካት በየአካባቢው ጾም እያደሩ ያሉ ቦታዎችን መጠቀምን ታስባለች። ለዚህም በኦሮሚያና በአማራ ክልል መሬት እንዲሰጣት ጠይቃለች።ይሁንና ለአማራ ክልል ያቀረበችው የመሬት ጥያቄ መስመር የያዘና ወደ ተግባር ለመግባት ጫፍ የደረሰች እንደሆነም አጫውታናለች።

የሽንኩርት ምርቷን ወደ አዲስ አበባ ከተማ ገበያ ለማቅረብ በምታደርገው የሌሊት ጉዞ የተመለከተችው ትእይንት ከአማራ ክልል በምታገኘው መሬት ላይ ስንዴን በስፋት ለማምረት አስገድዷታል።ነገሩ እንዲህ ነው በአንዱ የሌሊት ጉዞዋ በአዲስ አበባ አንዳንድ አካባቢዎች ከሌሊቱ ስምንት እና ዘጠኝ ሰዓት ላይ ሸገር ዳቦ ለመግዛት የተሰለፉ ዜጎቿን ትመለከታለች።ታዲያ በዚህ ጊዜ የተትረፈረፈ የስንዴ ምርት ማምረትና ይህን ታሪክ መቀየር እንዳለባት ለራሷ ቃል ገባች።ቃሏን ተግባራዊ ለማድረግም እንቅስቃሴ የጀመረችው ቃልኪዳን፤ ስንዴ ለማምረት በጠየቀችው መሬት ላይ ሠርተው፣ በልተውና ጠግበው ማደር የሚችሉ 58650 ዜጎችን እንደምትፈልግና እነዚህ የሥራ ዕድል የሚፈጠርላቸው ዜጎችም በዋናነት ከጎዳና ተነስተው በሚያገኙት ስልጠና ወደ ሥራ የሚገቡ እንደሚሆኑ አጫውታናለች።

‹‹አሁን ምን ያህል ካፒታል ላይ ደርሰሻል?›› ስንል ላነሳንላት ጥያቄ አርሶ አደርና ነጋዴዋ ቃልኪዳን፤ ስትመልስ ‹‹የገበሬ ሀብቱ መሬት ነው፤ መሬትን ደግሞ በዋጋ ልንተምናት አንችልም።ስለዚህ ስለካፒታል መጠየቅ ካለባትም መሬት እራሷ ናት መጠየቅ ያለባት።እኔ ያገኘሁትን ሁሉ መሬትን አምኜያት እሰጣታለሁ እሷም እጥፍ ድርብ አድርጋ ትመልስልኛለች›› በማለት ቁጥር ከመግለጽ ተቆጥባለች፡፡

ያፈራችውን ሀብት በቁጥር ከመግለጽ የተቆጠበችው ቃልኪዳን፤ ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻር ስላበረከተችው አስተዋጽኦም እንዲሁ ‹‹ቀኝ እጅህ ሲሰጥ ግራ እጅህ አይመልከት›› በሚለው አስተምህሮ መነሻነት በይፋ ከመናገር ተቆጥባለች።ለዚህም ‹‹ምክንያቱም ማንም ሰው ሰው በጠፋበት ቦታ ሁሉ ሰው ሆኖ መገኘት ከቻለ እሱ በቂ ነው።እኔም መክፈል ያለብኝን መስዋዕትነት ከፍዬ ሰው በሌለበት ቦታ ላይ ሰው ሆኜ እገኛለሁ›› ትላለች።

ከሁለትና ሶስት ዓመት በፊት ከፍተኛው የሽንኩርት ዋጋ በኪሎ ስምንት ብር የነበረ መሆኑን ያስታወሰችው ቃልኪዳን፤ በአሁን ወቅት አንድ ኪሎ ሽንኩርት 40 ብር መሸጡ አግባብ እንዳልሆነና ይህም የሆነው መሬት ጦሙን እያደረ ማምረት ባለመቻሉ እንደሆነ ትገልፃለች።በተለይ በአሁኑ ወቅት አብዛኛው ሰው ከሚሠራው ይልቅ በሰበብ አስባቡ ከሥራ ውጭ እንደሚሆንና ከሙያው ውጭ በመሆኑ ምርት ላይ ትኩረት አድርጎ እንዳይሠራ ስለማድረጉም ታስረዳለች።ስለዚህ ‹‹ለዋጋ ንረቱም ሆነ ለምርት እጥረቱ ተጠያቂዎቹ እኛው ነንና ሁላችንም በሙያችን እንሥራ›› በማለት የምትመክረው ቃልኪዳን፤ አምራች እንደመሆኗ ምርቶቿን በቀጥታ ለሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ገበያን የማረጋጋት ሥራ ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት አላት፡፡

ይሁን እንጂ ይህን ፍላጎቷን ዕውን ለማድረግ የመሸጫ ቦታ ያስፈልጋታል።የመሸጫ ቦታ እንዲሰጣት በአስራ አንዱም ክፍለ ከተሞች 150 መኪኖች የጫኑትን የተለያዩ አትክልቶች ማራገፍ የሚያስችላትን ቦታ ለማግኘት ጥያቄ ብታቀርብም አንዳቸውም ፈቃደኞች ሳይሆኑ ከአንድ ቢሮ ወደ ሌላኛው ቢሮ ትመላለሳለች።‹‹ሸማቹን በቀጥታ ላግኝ›› የሚለው ጥያቄዋ ዋጋን በመቀነስ ገበያን ማረጋጋት የሚችል ከመሆኑም በላይ የማህበረሰቡን ችግር በከፊል የሚያቀል እንደሆነ ይታመናልና ምነው ጥያቄው አልተመለሰም ? በማለት እየጠየቅን፤ መሰል ተግባራት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ፣ አምራቾችን በማበራከት ወቅታዊና አገራዊ የሆነውን የኑሮ ውድነት ከማቃለል ባለፈ ድህነትን በተባበረ ክንድ እናጥፋ በማለት አበቃን።

**ከኢፌዲሪ የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ዘወትር ረቡዕ እና ቅዳሜ የሚታተም**

# የማይታይ መጠን የተገታ መተሳሰፍ ዐቢይ ዓሳማ

**ዳንኤል ዘነበ**

በአለም ዓቀፍ ደረጃም ሆነ በአገራችን የማይታይ መጠን የተገታ መተላለፍ መርሃ ግብር ተግባራዊ ሲደረግ አንዱና ትልቁ ኤች . አይ . ቪ በደማቸው የሚገኝ ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ ነው። የመርሃ ግብሩ ትግበራ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ጤናማ፣ አምራች ሆነው እስከ ህይወት ዘመናቸው እንዲቆዩ ያደርጋል። ይህ በመሆኑ ለአገርም ለማህበረሰብም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያስችላል። እናንተ አንባቢዎቻችን በመርሃ ግብሩ ላይ በቂ ግንዛቤ ይኖራችሁ ዘንድ ባሳለፍነው እትማችን ‘ የማይታይ መጠን የተገታ መተላለፍ መርሃ ግብር ትግበራ ኤች.አይ .ቪ በደማቸው የሚገኙ ዜጎች ላይ የሚደርሰን መገለልና መድሎን ከማስቆም አኳያ ስለሚኖረው ሚና ‘ መመልከታችን ይታወሳል። በዛሬ እትማችን ደግሞ የማይታይ መጠን የተገታ መተላለፍ መርሃ ግብር አንደኛው ዓላማ ስለሆነው ኤች . አይ. ቪ በደማቸው የሚገኝ ሰዎች ጤናማ ህይወት እንዲኖሩ ማስቻልን በተመለከተ በሚኖረው ሚና ዙሪያ የሚያጠነጥን ይሆናል። በዚህ ጉዳይ እና የመርሃ ግብሩ ትግበራ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኙ ወገኖች የህይወት አቅጣጫን የሚቀየርበት መንገድ እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የፌደራል ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከል እና መቆጣጠሪያ ጽህፈት ቤት የህዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል በትረ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል። አቶ ዳንኤል ከመርሃ ግብሩ ጋር ተያይዞ የሰጡትን ሃሳብና አስተያየት እንደሚከተለው ይቀርባል።

የኤች .አይ . ቪ ስርጭት ለመቆጣጠር ከሚያግዙ መንገዶች መካከል ተመርምሮ ራስን ማወቅ ይጠቀሳል።

> **የኤች .አይ . ቪ ስርጭት ለመቆጣጠር ከሚያግዙ መንገዶች መካከል ተመርምሮ ራስን ማወቅ ይጠቀሳል። አንድ ሰው ለኤች አይ ቪ ተጋላጭ የሚያደርጉት ሁኔታዎች ከተፈጠሩ በፍጥነት መመርመር ይኖርበታል። የደም ምርመራ አድርጎ ኤች . አይ .ቪ በደሙ ተገኘ ማለት የህይወት ጉዞው እንደተገታ መቁጠር አይገባም**

አንድ ሰው ለኤች አይ ቪ ተጋላጭ የሚያደርጉት ሁኔታዎች ከተፈጠሩ በፍጥነት መመርመር ይኖርበታል። የደም ምርመራ አድርጎ ኤች . አይ .ቪ በደሙ ተገኘ ማለት የህይወት ጉዞው እንደተገታ መቁጠር አይገባም። ኤች. አይ. ቪን እንደማንኛውም አይነት ቫይረስ አይቶ ጤናን እየጠበቁ እና መንፈስን ሳያስጨንቁ ተረጋግቶ መኖር ይቻላል። የጸረ- ኤች .አይ .ቪ መድኃኒት መጀመር እና ሳያቋርጡ መውሰድ በጤና የመኖር መክፈቻ ቁልፍ እንደሆነ የህክምና ሳይንሱ ያስቀምጠዋል ። የማይታይ መጠን የተገታ መተላለፍ መርሃ ግብር ትግበራም ይሄንኑ መሠረት ያደረገ እደሆነ ሊታወቅ ይገባል። መርሃ ግብሩ የሚመለከተው ኤች . አይ . ቪ በደማቸው የሚገኝ ዜጎችን ሲሆን። በአገራችን የማይታይ መጠን የተገታ መተላለፍ መርሃ ግብር ከተጀመረ ሁለት ዓመት ያስቆጠረ ሲሆን መርሃ ግብሩ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጽንሰ ሃሳቡን በማስገንዘብ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። በዋናነትም ስለ መርሃ ግብሩ ምንነት በተመለከተ በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ ጽንሰ ሃሳቡን ለማስገንዘብ እተሰራ ይገኛል።

**ህይወትን በጤና የመምራት አስቻይ ሁኔታ መፍጠር**

በአገር አቀፍ ደረጃ የማይታይ መጠን የተገታ መተላለፍ መርሃ ግብር ተግባራዊ ሲደረግ የተለያዩ ዐበይት አላማዎችን በመያዝ ነው። ከነዚህ መካከል ደግሞ ኤች . አይ . ቪ በደማቸው የሚገኝ ዜጎች መድኃኒትን በትክክል ወስደው በደማቸው ያለውን የቫይረስ መጠን በሚገባ ቀንሰው በቫይረስ መጠን ልኬት ተለክቶ የማይታይ ደረጃ እንዲደርስ እና ከደረሰ በኋላ ያንን ዘለቄታዊ ባለው መልኩ በማቆየት ጤናማ ህይወት እንዲኖሩ ማስቻል አንደኛው ዓላማ በመሆን ይጠቀሳል።

**ሲዘነጋ የማይገባው**

ነገር ግን አንድ ሰው ኤች . አይ . ቪ በደሙ የሚገኝ ከሆነና መድኃኒቱን በአግባቡ ካልወሰደ ጤናው ይታወካል፣ ለተጓዳኝ በሽታዎች ይዳረጋል። ህመምተኛ ከሆነ ደግሞ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ብሎም ሥነ - ልቦናዊ ችግሮች በግለሰቡ ላይ ተጽእኖ ማሳደራቸው አይቀሬ ይሆናል። ስለዚህ በነዛ ተጽእኖ ውስጥ ያለ ሰው አምራች አይሆንም፤ ጤናማ አይሆንም። ይህ በመሆኑ ህይወቱ ይዛባል። ይህ በመሆኑም አንድ ሰው ጤናማና አምራች ሆኖ ለራሱ፣ ለቤተሰቡ፣ ለማህበረሰቡ እንዲሁም ለአገሩ እንዲጠቅም ኤች . አይ . ቪ በደሙ የሚገኝ ከሆነ የጸረ - ኤች . አይ . ቪ መድኃኒትን በአግባቡ መውሰድና በደሙ ውስጥ የሚገኘን የቫይረስ መጠን የማይታይ መጠን ማድረስ፤ ይሄንኑም በዘላቂነት እስከ ህይወት ዘመኑ ማቆየት ይኖርበታል፡፡

---



## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጥበቃ አገልግሎት ግዥ ጨረታ
## ጨረታ ቁጥር፡- AAUSC/05/2014/22

1. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ንግድ ስራ ት/ቤት ከላይ የተጠቀሰውን አገልግሎት በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡
2. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ንግድ ስራ ት/ቤት ከላይ የተጠቀሰውን አገልግሎት ለማቅረብ ፍላጎትና ብቃት ያላቸው ተጫራቾች በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ጨረታ ሰነድ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ንግድ ስራ ት/ቤት እንድታቀርቡ ትጋበዛላችሁ::
3. ተጫራች ድርጅቶች በቅድሚያ ሊያሟሉ የሚገባቸው ከፌደራል ፖሊስ የታደሰ ፈቃድ ያለው፣ ህብረ-ብሄር የሰው ኃይል ማቅረብ የሚችል፣ ወቅታዊ የኢንሹራንስ የገባበትን ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል ፣ ድርጅቱ ቢያንስ 5 ዓመት የግልጋሎት ዘመን ያለው መሆኑን የሚጠቅሱ ዶከመንቶችን ማቅረብ የሚችል እና ጨረታው የሚከናወነው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት የመንግሥት ግዥ አዋጅ በተገለጸው ብሔራዊ ግልጽ የጨረታ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ይፈጸማል፡፡ ጨረታው የሚከናወነው ብቁ ከሆነ ተጋባዥ ተጫራች እና ከስራው ጋር አግባብነት ያለው ሆኖ የ2014 ዓ.ም የታደሰ ህጋዊ የንግድ ስራ ፍቃድ ያለው፤ የዘመኑ ግብር መከፈላቸውን የሚገልጽ ወቅታዊ ደብዳቤ ከአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን፣ በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ መመዝገባቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ዌብሳይት ላይ ፕሪንት አርጋችሁ እንዲሁም ቲን ሰርተፍኬት እና ቫት ሰርተፍኬት ኮፒውን ማቅረብ የሚችል ይሆናል፡፡
4. ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች ከዚህ በታች በተራ ቁጥር /7ሀ/ በተገለፀው አድራሻ የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ 100.00 (አንድ መቶ) ብር በመክፈል መውሰድ ይችላሉ፡፡
5. የጨረታ ሰነዱን ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 7 (ለ) በተገለጸው አድራሻ ሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ.ም. እስከ ጠዋቱ 4:00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይችላሉ፡፡ የጨረታ ማስከበሪያው በተጫራቾች መመሪያ በተዘረዘረው መሠረት አያይዘው ያቀርባሉ። ዘግይተው የቀረቡ የጨረታ መልሶች ተቀባይነት የላቸውም በጨረታው ላይ ለመገኘት የፈለጉ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በቁጥር 7 (ሐ) በተጠቀሰው አድራሻ ሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ በ4:30 ሰዓት ይከፈታል፡፡
6. ተጋባዥ ተጫራቾች ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 7 (ለ) በተገለጸው አድራሻ ሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ.ም. ከጠዋቱ በ4:00 ሰዓት ወይም በፊት በተዘጋጀው የጨረታ ሣጥን ውስጥ የጨረታ ሠነዱን ማስገባት በግዥ ቡድን መሪ ቢሮ ከጨረታ መክፈቻ ጊዜ በፊት በማቅረብ ይሆናል፡፡ ተጋባዥ ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ብር 20,000.00 (ሀያ ሺ) በሲፒኦ ወይም በሁኔታ በቅድመ ላይ ባልተመሰረተ የባንክ ዋስትና አያይዘው ማቅረብ አለባቸው።
7. ሀ/ ሰነዶቹ የሚመጡበት አድራሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ንግድ ስራ ት/ቤት ግዥ ቢሮ ቁጥር 209.

ለ/ የጨረታው ሰነድ የሚገባበት አድራሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ንግድ ስራ ት/ቤት ግዥ ቡድን ቢሮ ቁጥር 209.

ሐ/ ጨረታው የሚከፈትበት አድራሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ንግድ ስራ ት/ቤት ግዥ ቢሮ ቁጥር 209.

8. ት/ቤቱ በከፊልም ሆነ በሙሉ ጨረታን የመሰረዝ መብት አለው፡፡

ስልክ ቁጥር፡- 0115-58-47-46 ወይም 0115-58-48-53

**የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ንግድ ስራ ት/ቤት**

# ርዕሰ አንቀፅ

## አሸባሪው ሕወሓት ስለ ሰላም የሚያዜመው ዜማ ተአማኒነት ሆነ ተቀባይነት እንዲያገኝ

ስለ ሰላም የሚዜም ዜማ የሰላምን ሁለንተናዊ ጥቅም ከማወቅ የሚመነጭ፤ የሰላም እጦት የቱን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል በአግባቡ ከመረዳት የሚነሳ፤ ከእውነተኛ የራስ ማንነት የሚቀዳ ሊሆን ይገባል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ የሚዜም የሰላም ዜማ በሰላም በራሱ የማፌዝ ያህል ነው። ይህ ደግሞ ሊያስከፍል የሚችለው ዋጋ ከግምት በላይ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ አይከብድም።

ከራሱ ጋር ሰላም የሌለው ግለሰብ ሆነ የግለሰቦች ስብስብ/ቡድን በየትኛውም መልኩ የሰላም ሀዋሪያ ሊሆንና የሰላም ዜማ በአደባባይ ሊያዜም የሚያስችል ፍጥረታዊ ማንነት ሊኖረው አይችልም። ከዛ ይልቅ ከራሱ አልፎ ለቤተሰቡ፣ ለማህበረሰቡ ከዚህም ከፍ ካለ ለአገር የሰላም እጦት ችግር ምንጭ መሆኑ የማይቀር ነው።

ይህ ገና ከጅምሩ ከአስተዳደግ፤ ከተሳሳተ የአስተሳሰብ ግንባታና የታሪክ አረዳድ የሚነሳ ችግር፤ ግለሰቡ ከራሱ ጋር ተስማምቶ ሰላም እንዳይፈጥር ተግዳሮት ይሆናል። ችግሩ እያደገ ሲሄድ በተበላሸ /በሳተ የአስተሳሰብ መሰረት ላይ የተገነባው የግለሰቡ ስብእና ስለ ሰላም ከማዜም ይልቅ የሰላም ጠንቅ እንዲሆን ያደርገዋል። ለዚህ ደግሞ ቤተሰብ እና ማህበረሰብ ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ።

እነዚህ ጠንቀኛ ግለሰቦች በታሪክ አጋጣሚዎች በሚፈጠሩ ክፍተቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የመደመጥ እድል ካገኙ ሊያስከትሉት የሚችሉት ማህበራዊ ምስቅልቅል፤ ከዛም ባለፈ ሕዝብንና አገርን ሊያስከፍሉ የሚችለው ዋጋ ለትርክት የሚመች አይደለም። በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ በጥቁር ጠባሳነት የሚጠቀሱ ናቸው።

የጀርመኑን አዶልፍ ሂትለር፤ የጣሊያኑን ------- መሶሎኒ የኡጋንዳውን ፊልድ ማርሻል ኢዲያሚን ማየት በራሱ በቂ ነው። እነዚህ ግለሰቦች በውስጣቸው የተፈጠረው የማንነት የስነ ልቦና ቀውስ በየአገራቱ የተከሰቱ መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም ወደ ስልጣን በመምጣት ከአገራቸውና ከህዝባቸው አልፈው አለምን ብዙ ዋጋ አስከፍለዋል።

በኛም አገር ከአስተዳደግ፤ ከተሳሳተ የአስተሳሰብ ግንባታና የታሪክ አረዳድ በመነሳት ከራሳቸው ጋር የተጣሉ ግለሰቦችና የግለሰቦች ስብስብ /ቡድኖች አገር እንደ አገር ህዝባችንን፤ እንደ ህዝብ ያስከፈሉትና ዛሬም እያስከፈሉት ያለው ዋጋ ከፍ ያለ ነው። ለብዙ ሞትና ስደት፤ ለከፋ ረሀብና እርዛት ዳርገውታል።

ይህ ወደኋላ ሲሳብ ረጅም ዘመን ያስቆጠረው አገራዊ ችግር በተለይም በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ያስከተለው ማህበራዊ




ምስቅልቅል ከፍ ያለ ነው። አንድም በተቀዳ የባእድ የፖለቲካ ኢኮኖሚ አስተሳሰብና አስተሳሰቡ የወለደው ልበ ደንዳናነት፤ በሌላ በኩል አስተሳሰቡ በፈጠረው የተሳሳተ ትርክት ችግሩ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር፤ እርሾው ዛሬም ዋጋ እያስከፈለን መሆኑ ይታወቃል።

በተበላሸ የስነ ልቦና መሰረት ላይ የተዘራው ይህ ባእድ የፖለቲካ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ በአገሪቱ የፖለቲካ ማህደር ውስጥ የፈጠረው የንባብ ጥራዝ ነጠቅነት ላለመደማመጥ ምክንያት ሆኖ አገር ተስፋ ያደረገችው ትውልድ ለሰላም እድል መስጠት አቅቶት እርስ በእርሱ ተገዳድሎ አገርን እንደ አገር የሀዘን ቤት ማድረጉ የቅርብ ትዝታ ነው።

ከዚህ ታሪካዊ ክስተት ቁዘማ በአግባቡ ሳንወጣ ከአስተዳደግ፤ ከተሳሳተ የአስተሳሰብ ግንባታና የታሪክ አረዳድ ችግር ውስጥ የተወለደው፤ የ1966 ዓ.ም አብዮት የፈጠረው አገራዊ ትርምስ መልካም አጋጣሚ የፈጠረለት አሸባሪው ሕወሓት ሰላምንና የሰላምን ዜማ የትንሽነት መለኪያ አድርጎ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። ጦረኝነትንና ከዚህ የሚመነጭ ጀብደኝነትን ዋነኛ መገለጫው አድርጎ ቆይቷል።

በዚህም የተሳሳተ አረዳዱ ከትጥቅ ትግሉ ጀምሮ አገርን ከሁሉም በላይ በነጻነት ስም የትግራይን ህዝብ ያስከፈለው ዋጋ ከፍ ያለ ነው። በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ወጣቶችን ለሞት፤ በመቶ ሺ የሚቆጠሩትን ደግሞ ለአካል ጉዳት ዳርጓል። ከዚህ ሁሉ ግን የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ ያተረፈው ነገር የለም። ህዝቡ በነጻነት ስም ያተረፈው የከፋ ባርነት፤ ሀዘን እና ከሀዘን የሚመነጭ የቁዘማ ሕይወት ነው።

በስልጣን በቆየባቸው 27 አመታትም እራሱ ሰላም አጥቶ መላው ህዝባችንን በአንድም በሌላ ሰላም ሲነሳ፤ በዚህም ብዙዎችን ለሞት ለአካል ጉዳት ለስነልቦና ቀውስና ለስደት ዳርጓል። ከስልጣን ከተወገደም በኋላም የሄደበት የጀብደኝነት መንገድ አገርን እንደ አገር ያስከፈለው ዋጋ ከፍያለ ነው። የአገርን ህልው አደጋ ውስጥ የከተተ፤ አገረ መንግስቱን ያንገጫገጨ ነው።

ዛሬም የመንግስትን የሰላም ቁርጠኝነት ተከትሎ የጀመረው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ለሰላም ያለውም ቁርጠኝነት ከማሳየት ይልቅ አጋጣሚውን የፖለቲካ ትርፍ ማግኛ ማድረግን ታሳቢ ያደረጉ ናቸው። ለዚህም በስሙ የሚያወጣቸው መግለጫዎችና ደብዳቤዎች እማኝ ናቸው።

ቡድኑ ስለ ሰላም ለማዜም ሆነ ለሰላም ለመቆም መጀመሪያ ከቀደመው የውልደት ማንነቱ ሊፋታ፤ በትግራይ ህዝብ ደም ከተገነባው የጀብደኝነት መንገዱ ሊወጣ፤ ከአስተዳደግ፤ ከተሳሳተ የአስተሳሰብ ግንባታና ከታሪክ አረዳድ ችግር እራሱን ሊታደግ ይገባል። ይህን ማድረግ ሲችል ስለ ሰላም የሚያዜመው ዜማ ተአማኒነት ሆነ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል።

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ፅሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ሽብር እና ሽብርተኞችን በማያዳግም ሁኔታ ለማስወገድ

ሶሎሞን በየነ

“አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ” ይላል ያገሬ ገበሬ። አንድ አርሶ አደር ማሳውን አደፋርሶና ሰርዶውን ከስሩ መንግሎ አጎልጉሎ ካላረሰ ማሳው ዳዋ ይወርሰዋል። በአረም ይወጣል። ይህም አርሶ አደሩ በሚያርስበት ወቅት በደንብ አርሶ አረሙን በእንጭጩ መቅጨት ካልቻለ በአረም ወቅት የአርሶ አደሩን ልፋት እጥፍ ድርብ ከማድረጉ ባሻገር አረሙ ከአቅሙ በላይ ሆኖበት የልፋቱን ፍሬ ሳያገኝ መና ያስቀረዋል። ልፋቱም ከንቱ ይሆናል።

በዚህ የመንደርደሪያ ሃሳብ ዛሬ ለማንሳት የወደድሁት ጉዳይ በተለይ በአገሪቱ ፖለቲካዊ ለውጡ ከመጣ በኋላ “ለምን የበላይነቴ ተነካ? እንዴት ከፈላጭ ቆራጭነቴ ተነስቼ እኩል እዳኛለሁ?” በሚል አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ህዝብን ሲያሸብር፣ ሲያፈናቅልና በየሳምንቱ የሞት ድግስ እየደገሰ አገሪቱን አኬል ዳማ አድርጓል። እያደረገም ይገኛል። እንዲሁም ከውጭ የአገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ተናቦ አገር ለማፍረስ ሲሰራም ቆይቷል። እየሠራም ይገኛል።

ይህ የሽብር ቡድን ይባስ ብሎ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሰሜን ዕዝ የአገር መከላከያ ሰራዊትን ከጀርባው በመውጋት የአገሪቱን ሉኣላዊነት አደጋ ላይ በመጣል የአገር ክደት ወንጀል መፈጸሙ ዓለም የሚያውቀው ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ነው። ጁንታው ይህንን ጥቃት መፈጸሙን እራሱ በአንደበቱ “መብረቃዊ ጥቃት” ሲል ገልጿታል።

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሸባሪ ተብሎ የተፈረጀውን የሕወሓት ቡድንን መንግስት አደብ ለማስገዛት በትግራይ ክልል ሕግ የማስከበርና የህልውና ዘመቻ ውስጥ ገብቶ እንደነበር ይታወቃል። ይህንንም ዘመቻ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ አቅም ያለው ጦርሜዳ ተሰልፎ በመዋጋት አቅም የሌለው የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ለወገን ጦር ደጀን ሆኗል። ደግፏል። በዚህ ዘመቻም ብዙዎች ለአገራቸው ተሰውተዋል።

መንግስት በተወሰደው የህግ ማስከበር ዘመቻ “የሽብር ቡድኑ ለአገሪቱ እንዲሁም ለህዝብ ስጋት በማይሆን ደረጃ ተመትቶ ተንኮታኩቷል። ሕወሓት ታሪክ ሆኗል” የሚል ዜና ሲናገር ሁሉም አገር ወዳድ ዜጋና ኢትዮጵያን እንዳይኑ ብሌን የሚሳሳላት ህዝብ ጮቤ እረግጦ ነበር። “ታሪክ ሆኗል” የተባለው አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ከተሰገሰገበት ዋሻና የቀበሮ ጉድጓድ ወጥቶ በአፋርና በአማራ ክልል በፈፀመው ወረራ ያደረሰውን ግፍና መከራ መናገር የጉዳቱ ሰለባ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በቁስላቸው ላይ ጋሬጣ እንደመስደድ ይሆንብኛል።

የሽብር ቡድኑ 700 ኪሎ ሜትር አቆራርጦ የአራት ኪሎ ቤተመንግስትን ለመቆጣጠር 200 ኪሎ ሜትር የማይሞላ መንገድ ቀርቶት ጣርማበር ደርሶ እልህ አስጨራሽ ትግል ተደርጎ ከባድ መሰዋዕትነት ተከፍሎ ነው የተመለሰው። በዚህም ህዝብ እንደ ህዝብ ጉዳት ደርሶበታል። በአንጻሩ አገረ መንግስቱም ቢሆን ከፍ ባለ የመፍረስ ስጋት ውስጥ ወድቆ እንደነበር የሚታወስ ነው።

አሁንም ይህ የሽብር ቡድን ዳግም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ጦርነት ለመክፈትና ወረራ ለመፈጸም ነጋሪት እየጎሰመ ይገኛል። አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የሽብር ቡድኑ በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ግዳን ወረዳ ወትወት፣ ጥራሪ በሚባሉ የገጠር መንደር እንዲሁም በራያ ቆቦ ወረዳ በሚገኙ የክልሉ አዋሳኝ ቀበሌዎች ሰርጎ በመግባት የንጹሃንን ሃብትና ንብረት ከመዝረፉ ባለፈ ወጣቶችን አፍኖ በመውሰድ “መከላከያ የት፣ የት ይገኛል? ምን ያህል ቁጥር አለው? ፋኖ የት ይሰለጥናል?” በሚል መረጃ ለማጣራት ንጹሃንን እያሰቃየ ይገኛል።

ከዚህ ባሻገር በዋግ ህምራ ዞን በጁንታው ከቀያቸው ተፈናቅለው በሰቆጣ ከተማ ከከተማዋ ህዝብ ቁጥር በላይ ተፈናቃዮች ይገኛሉ። በጠለምት፣ አደርቃይ በቁጥጥር ስር ያደረጋቸው የአማራ ክልል ቀበሌዎችም መኖራቸው ይታወቃል። ቡድኑ ከትናንት ጥፋቱ መማር የማይችል መሆኑ ከቀደመው ታሪኩ የሚቀዳ እውነት ከመሆኑ አንጻር ስለ ነገ በልበ ሙሉነት መናገር አይቻልም።

አሸባሪው በድኑ በትግራይ ሆነ ከትግራይ ውጪ አሁንም እያካሄዳቸው ባሉ የሽብር ተግባራት ንጹሃን ዜጎች ለብዙ ስቃይና መከራዎች ተጋላጭ ከመሆናቸው ባለፈ ህይወታቸውን እያጡ ነው። መንግስት ለዚህ አሸባሪ ቡድን ለሽብር ተግባሩ ተጨማሪ እድል ሊሰጠው አይገባም። ይህንን የሽብር ቡድን አደብ ሊያስገዛው ይገባል።

የቡድኑ ፍጥረታዊ ስብእናው ለሰላም ምንም አይነት እድል መስጠት የሚችል ባይሆንም ይሰጣል ቢሎ ከታመነም ድርድሩ ህዝብ ተሳታፊ የሚሆንበትና ዘላቂ መፍትሄ መምጣት የሚያስችል መሆን አለበት። ለቡድኑ ጊዜ መግዣ መሆን የለበትም።

መንግስት ዜጎችን ከየትኛውም አይነት ህገወጥ ተግባር ለመታደግ ካለበት ኃላፊነት አንጻርም የትግራይ ህዝብን ከሽብር ቡድኑ የግዞት ቀንበር የማላቀቅ ግዴታ አለበት። የትግራይ ህዝብም እንደ ህዝብ ይህንን ቀንበር ከጫንቃው ላይ መጣል የሚያስችል ቁርጠኝነት መፍጠር ይጠበቅበታል።

ሌላው በአገሪቱ የመጣውን ፖለቲካዊ ለውጥ ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል ለሚፈሰው ደም አጋፋሪ ተደርጎ የተወሰደው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሸባሪ ተብሎ የተፈረጀው ሸኔ ነው። ለውጡን ተከትሎ በሰላማዊ መንገድ እታገላለሁ ብሎ ወደ አገር ቤት የገባው ይህ የሽብር ቡድን በኦሮሚያ ክልል የንጹሃንን እያፈሰሰ ይገኛል።

በክልሉ በተለያዩ ቀናት ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ዜጎች በቡድኑ ጭካኔ የተሞላበት ተግባር ለሞት ተዳርገዋል። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው ተጠልፈው የገቡበት ደብዛ ጠፍቷል። በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል። ሃብት ንብረታቸው ተዘርፏል፤ ወድሟል።

መንግስትም በሽብር ቡድን ላይ የማያዳግም እርምጃ ወስጃለሁ ቢልም ቡድኑ በንጹሀን ዜጎች ላይ የሚሰነዝረው የከፋት ሰይፍ አልቆመም። ጊዜና ቦታ ለይቶ በሚያደርሳቸው ጥቃቶች ዜጎች ከፍ ያለ ዋጋ እየከፈሉ ነው። ይባስ ብሎ ከሰሞኑ ከጋምቤላ ነጻነት ግንባር ጋር በመሆን የጋምቤላ ከተማን ለመቆጣጠር ጦርነት ከፍቶ ብዙ ንጹሃን ዜጎች ላይ ጉዳት መድረሱ እየተነገረ ነው።

አገሪቱን የሽብርና የአሸባሪዎች ደሴት ለማድረግ እየተናበቡ የሚንቀሳቀሱትን እነዚህን አሸባሪ ቡድኖች ሆነ፤ ከነሱ ጋር በነጻ አውጪ ስም የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ሀይሎች ላይ መንግስት የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ ህዝቡን ከሰቀቀን፣ አገሪቱን ከአደጋ የመታደግ ኃላፊነት አለበት፤ ይህንን ኃላፊነት በስኬት ለመወጣት የጀመረውን የሕግ የማስከበር እና አገርን የመታደግ ዘመቻ በተጠናከረ መንገድ ሊቀጥልበት ይገባል፤ መላው ህዝብም ከመንግስት ጎን በመቆም ለሀገር ያለውን ፍቅርና ታማኝነት በተግባር ማሳየት ይጠበቅበታል። ከአገር ሊያስበልጠው የሚችለው ነገር የለም!።

ይህንን ማድረግ ካልተቻለ መነሻዬ ላይ ለማሳየት እንደ ሞከርኩት አንድ አርሶ አደር ማሳውን አደፋርሶና ሰርዶውን ከስሩ መንግሎ አጎልጉሎ ካላረሰ ማሳው ዳዋ እንደሚወርሰው። በአረም እንደሚዋጥ መጪው የተስፋ ዘመናችን ከፍ ባለ የአረም ስጋት ውስጥ መውደቁ እንደማይቀር መገመት አይከብድም። ፍሬ አልባ ሊያደርገን እንደሚችል መሳብ አላዋቂነት አይሆንም። አበቃሁ። ቸር እንሰንብት!

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## የእሳት ልጅ አመድ ሳስመባል - ስምን የመቀየር ፍልሚያ

ሰላማዊት ውቤ

በምቾት፣ በድሎት ያደገ ሁሉ በከፍታው ላይዘልቅ ላይቀጥል ይችላል። ዝቅ ፣ ጎንበስ ተብሎም ይኖሩበት አጋጣሚ ይከሰታል። በልጅነቱ ተቀማጥሎና ሞልቶለት ያደገ ሁሉ መጨረሻው ያምራል ማለት አይደለም። በትምህርቱም ሆነ በሀብቱ የት ይደርሳል የተባለ ሕይወቱ እንደታሰበው አልጋ በአልጋ የማይሆንበት አጋጣሚ የበዛ ነው።

በአብዛኛው እንዲህ አይነቱ በሕይወት ተስፋ አይቆርጥም። ለውጥ ባያገኝበትም እዚህም፣ እዛም እየተንቦራጨቀ ዕድሉን መሞከሩ የግድ ነው። ያም ሆኖ እንዳሰበው ካለበት የከፍታ ማማ መውረድ እንጂ በቀላሉ መውጣት አይሳካለት ይሆናል። ሕይወቱ እስካለች ግን ዛሬን ለማደርና ነገን ለመኖር የሚያደርገውን ጥረትና የኑሮ ፍልሚያ አይቋረጥም።

ዛሬ የሕይወት ተሞክሮዋን የምናካፍላችሁ ማዕከላዊት እሳቱም ከነዚህ ሰዎች አንዷ ናት። ማዕከላዊት ‹‹ግሩም ናት ድንቅ ናት ለምለሟ አገሬ ፣ የአክስቶቿ ብዛት፣ ድማማይ›› በሚሉና በብዙ ተደማጭና ተወዳጅ ዘፈኖቹ የሚታወሰው የድምፃዊ እሳቱ ተሰማ ልጅ ናት። ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ሰድስት ኪሎ መነን እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነው።

ማዕከላዊት አባቷ ያሳደጋት ያለ እናት ነው። እናቷ በወቅቱ መልከ መልካምና በአቋሟ ማራኪ ነበረች። ከአባቷ ባለመግባባታቸው በወለደቻት በ15 ቀኗ ጥላት ሄደች። ይህኔ አባት ሞግዚት ቀጥሮ ይንከባከባት ገባ። ጥቂት ቆየና እቴቴ የምትላት እንጀራ እናቷ አባቷን አግብታ ተቀበለቻት። ትምህርቷ ላይ ብቻ ትኩረት ታድርግ በሚል በስስት አቀማጥላ አሳደገቻት።

ይህች ሴት ልብሷን ቀርቶ መሀረብ አሳጥባት አታውቅም። እሳቱም ቢሆን ቀበጥና ባለጌ ልጅ አይወድም። ልጆቹን በሥርዓት አሳድጎ የሚያሻቸውን የሚያደርግ ደግ አባት ነው። እሷና ከእንጀራ እናቷ የተወለዱት እህትና ወንድሞቿ የፈለጉትን የሚጠይቁት እቴቴን ነበር።

ማዕከላዊት ለእንጀራ እናቷ የተለየ ፍቅር አላት። እንደሷ አባባል ወላጅ እናቷና እንጀራ እናቷ አብረው ቢወድቁ ቀድማ የምታነሳው እንጀራ እናቷን ነው። እሷ በስመ እንጀራ እናት መልካም እናቶችን በሙሉ ከፉ እያሉ የሚፈርጁትን አጥብቃ ትቃወማለች። ወይዘሮ ወርቅነሽ ደምሴን አሁን ድረስ ‹‹እቴቴ›› እያለች በፍቅርና በቁልምጫ ትጠራታለች። እቴቴን እንጀራ እናትሽ ሲሏት አትወድም። ፊቷ በቁጣ ይለዋወጣል።

ማዕከላዊት እናቷ በ15 ቀኗ ጥላት ብትሄድም፤ የእንጀራ እናቷ እጅ መልካም ሆኖ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል በስኬት አጠናቃለች። እንጀራ እናቷ ከራሷ ልጆች ይበልጥ ለማዕከላዊት ታደላ ነበር። ከእነሱ አስቀድማም ትምህርቷን በግል ትምህርት ቤት እንድትማር አድርጋለች። እንደታሰበው ግን የማትሪክ ውጤት መልካም አልሆነም።

የእሷም ሆነ የቤተሰቦቿ ፍላጎት ፤ በትምህርት ልቆ መሄድ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲ መግባት የሚያስችል ነጥብ አልመጣላትም። በትምህርት ገፍቶ ለመሄድ በነበራት ጽኑ ፍላጎት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያን ዳግም መውሰድ ፈልጋ ነበር። ሆኖም የአባቷና ፤ የወላጅ እናቷ የብቻ ኑሮ ሃሳቧን አላሳካውም። የግልዋ መፍጨርጨር ብቻውንም ውጤት አላመጣም። በወቅቱ እናትና አባቷ የየራሳቸውን ሕይወት ይመሩ ነበር። እሷ ግን ከማናቸውም ጥገኛ መሆንን አትሻም። ራሷን ለማውጣት ስትፍጨረጨር ኖራለች።

የ12ኛ ክፍል ትምህቷን ካጠናቀቀች በኋላ ድል ባለ ሰርግ ተዳረች። ጎጆ ወጥታ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች መሸጫ ከነበረው ባለቤቷ ጋር ለዓመታት ኖረች። ከትዳሯም አንዲት ሴት ልጅን አፈራች። ልጅቱ አሁን ከአባቷ ቤተሰቦች ጋር እየኖረች ነው። ዜግነቱ ሱማሌያዊ የሆነ አንድ የ10 ዓመት ወንድ ልጅም ወልዳለች። በአባቱ እጅ በአገረ እንግሊዝ ይኖራል።

ማዕከላዊት ሁሌም ከፍታን የምትፈልግ ሴት ነበረች።



ፎቶ በሳይ አሰፋቸው

ማደግ መለወጥን አብዝታ ትሻለች። ወደከፍታው ማማ ለመውጣት የአባቷ ታዋቂነት ሳይገድባት ዝቅ ብላ ብዙ ሥራዎችን ሰርታለች። ከሰል እስከ መሸጥም ደርሳለች። ለትዳሯ መፍረስ ምክንያት ከሆነው አንዱ በዚህ ጥረቷ መካከል የተፈጠረው አጋጣሚ ነበር። ከቀናት በአንዱ ዕለት ባለቤቷ ከእሷ በፊት ከሚያውቃት ሴት ጋር የፍቅር ግንኙነት እንዳለው አወቀች። ከዚያ በኋላ የእሷ ወደ ከፍታ ለመውጣት በትዳሯ ዋጋ መክፈል ትርጉም እንደሌለው ሲገባት። ከባሏ በፍቺ ተለያየች።

ከትዳሯ ፍቺ በኋላ ሕይወት እንደቀድሞ ቀጠለ። ማዕከላዊት መነን አካባቢ ወደሚገኘው የወላጆቿ ቤት ስትመለስ ፊት አልነሷትም። በተለይ እንጀራ እናቷ የበሉትን በልታ አብራቸው እንድትኖር ተማጽናት ነበር። ‹‹በጄ›› አላለችም። ወደ ካዛንቺስ አቅንታ መኖርን መረጠች። አንዳንዴ ማዕከላዊት የአቅሟን ታንጎራጉራለች። የአባቷን ሙያ ግን በወጉ መውረስ አልቻለችም።

ጥበብ እንዳሰበችው ባልጠራቻት ጊዜ የድምፃዊ አባቷን የእሳቱ ተሰማን ጓደኞችና የሚያውቁትን ሁሉ፣ በተለይም ዝነኞቹን ድምፃዊያን እየዞረች ተማልዳለች። ጽዳት እንኳን እንዲያስቀጥሯት ስትል በሀገር ፍቅር ፣ብሄራዊና ሌሎች ቲያትር ቤቶች ደጃፍ ተመላልሳለች። አልተሳካላትም።

ስለ አባቷ ስታስታውስ ከልብ ታዝናለች። እሳቱ ታዋቂ ዘፋኝ ነበር። በሙያው ብዙ አበርክቷል። ለአገሩም በተፈለገ ጊዜ ዘምቷል። ሆኖም ስም እንጂ ሀብት አላወረሳቸውም። የራሱ ቤት እንኳን ስለሌለው አሁን ድረስ ባለቤቱና ልጆቹ በኪራይ ቤት ይኖራሉ። እግሩን ሪህ ሲያመው ቆይቷል። እስከ ዕለተሞቱ ግን በሥራ ላይ ነበር።

እሳቱ በታመመ ጊዜ ድምፃዊ መሐሙድ አህመድ ድጋፍ ቢያደርግለትም ሌሎቹ የሙያ አጋሮቹ ረስተውታል። ለራሳቸው በኪነ ጥበብ ምሽትና በሌሎች ዝግጅቶች ይደጋገፉና ይታወሳሉ ‹‹ሌላው ቀርቶ ሚዲያ ላይ ዘፈኖቹ እንደሌሎቹ ተደጋግመው ሲቀርቡ አይስተዋልም። ቀደምቶቹን የሙያ አጋሮቹ በየምክንያቱ እየተነሱ ሲያስታውሱና ሲዘክሩ እሳቱን የዚህች አገር የእንጀራ ልጅ የሆነ ይመስል የተዘነጋበት እውነት ሁሌም ያበሳጫታል።

እሷ እንደምትለው በሕይወት ያለፉ አርቲስቶች ልጆች የሚደግፉበት፣ የሚታገዙበት አጋጣሚ የበዛ ነው። ለእሳቱ ቤተሰቦቹ ግን የማንም እጅ አልተፈታም። ሁሉም ነገር ቲፎዞ ይፈልጋልና ማዕከላዊትም ድጋፍ የሚያደርግላት አላገኘችም። ይህኔ ተስፋ ቆርጣ ቆየች ‹‹አማራጭ ባጣች ጊዜም ከጎዳና ወጣች። በጎዳና ሕይወት ብዙ ስቃይና መከራዎች ተፈራርቀውባታል። የምትበላውና የምትጠጣው እንዲሁም የምታድርበት አልነበራትም። ሆኖም በአለባበስም ሆነ በንጽሕና ራሷን በመጠበቋ ጎዳና የወጣች አትመስልም።

አዳዲሶቹን ዘመናዊ ሆቴሎች ጨምሮ በቀደምቶቹ በነጊዮን፣ ሂልተንና ሆቴሎች ጎራ ስትል ይደረግላት የነበረው የክብር አቀባበልም ፕሮቶኮሏን በመጠበቋ ነበር። እሷ ዘመናዊነትን በመውደዷ ዛሬም ድረስ ከፍ ያለ ነገርን ትወዳለች። አራት መቶ ብር በእጇ ካለ አንድ ማኪያቶ የሚታዘዝበት ባለ አራት ሆቴል ገብታ ዘና ፈታ ማለት ምርጫዋ ነው።

በጎዳና ላይ በቆየችበት ጊዜ አልጋ ይዛ የምታድርበት ብር እስኪታገኝ መዞር ግድ ይላት ነበር። በዚሁ ምክንያትም የሴት አዳሪነትን ሕይወት ገብታ ሞክራዋለች። የዛሬን አያድርገውና ከአስፋልት የምትቆመው ሞዴል መስላ፣ በእጅጉ ተውባ ነበር።የ ዛኔ ፈላጊዎቿ የበረከቱ ፣ ናቸው። ‹‹ገንዘብ በ20 ዓመት ልብ በ40 ዓመት›› እንዲሉ ሆኖ እንጂ ከቀረቧት አብዛኞቹ የጠየቀችውንና ከጠየቀችውም በላይ ገንዘብ አስታቅፈዋታል። የዛኔ ታዋቂ የሚባሉት ሳይቀር በደንበኝነት ከእሷ አይለዩም። ማዕከላዊት ከስሟ ጀምሮ ማንነቷን ደብቃ አታውቅም። አትደብቅም። ማነሽ ምንድነሽ ሲሏት የእሳቱ ተሰማ ልጅ መሆኗን ሳትፈራና ሳታፍር ትናገራለች።

ስራዋን ከሚያውቁት በርካቶቹ በሚሰሙት እውነት ይደነግጣሉ። የወታደር ልጅ ወታደር መሆኑ የሚገባቸው ደግሞ በቆመችበት ስራ ይሸማቀቃሉ። አንዳንዶች በሶማሌ ወረራ ጊዜ ዳር ድንበሩን ለማስከበር ካራማራ ዘምቶ ይሙት ይቁም የማይታወቀውን ወንድሟን ያስታውሳሉ። ደፈር ብለውም ይጠይቋታል።

ይፋጃል እሳቱ የሚባል ወንድም አለሽ? አዎ አለኝ ስትላቸው ደንግጠው ከእስዋ የተነጋገሩበትን ብር ከፍለው የሚሄዱበት ጊዜ ጥቂት አልነበረም። ማዕከላዊት አስቂኝም አሳዛኝም ገጠመኞች አሏት። በሴተኛ አዳሪነት ሕይወቷ እንደዋዛ የማይነገሩ በርካታ ፈተናዎችን አልፋለች። ከመኪና ተገፍትሮ ከመጣል ጀምሮ ጥርሷን እስከመስበር አደጋ ገጥሟታል። የተቀበለችውን ብር በጉልበት አስፈራርቶ ከሚነጥቅና ብሎም ከሚደበድብ ጨካኝ ጋር ማሳለፍም ልምዷ ነበር። የሴተኛ አዳሪነት ሥራ በይፋ ስለማይፈቀድ የሕግ ከለላ አይደረግላትም። አንዳንዴ ደግሞ ለሴትነቷ ክብር የሚሰጡ፣ አብልተው፣ አጠጥተው፣ ተንከባክበው፣ በጥሩ ገንዘብ አንበሽብሸው የሚሸኙ ገጥመዋታል።

ደጋግማ እንደምትለው በሴት አዳሪነት ኑሮ ማንም ሴት ወዳ አትገባም። አማራጭ በማጣት እንጂ። አንዳንዶች ደግሞ እንጀራቸው ቢሻግት ይጥሉታል እንጂ ለእንዲህ አይነቷ ሴት እርቧት ይሆናል ብሎ የሚሰጡ አይደሉም። ለሴተኛ አዳሪዎች ሕይወት የሚጨነቅና ያገባኛል ሲል የሚቆም አካልም የለም።

ማዕከላዊት በሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ያጋጠሟትን ወጣት ሴቶች ሁሌም ከመምከር አትመለስም። በዚሁ ስራ ተሰማርታ ከዓመታት በፊት በኤችአይቪ የሞተችን የእናቷን ልጅ ዋቢ አድርጋ ታስተምራለች። በዚህ መንገድ ሌሎች እንዳይቀጥሉም የራሷን ሕይወት እየጠቀሰች የስራውን ክፋት ትጠቁማለች

በአረብ አገራት ለዓመታት ተቀምጠው የተመለሱና አስፓልት ከመውጣት ያለፈ አማራጭ የሌላቸውን ሴቶች ታውቃለች። በየቡና ቤቱ እየዞረች ስታስተምር ዊዝ ድሮል ሞልታ ቡና ቤት የገባች የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማንጅመንት ተማሪም አጋጥማታለች።

አምስት ልጆቿን ምሽት ከመንገድ ቆማ በምታገኘው ገቢ የምታሳድግ እናትንም አግኝታለች። በቆይታ እንደታዘበችው ባብዛኛው ወደ ስራው የሚገቡት ሴቶች እንደ እሷ በሮች የተዘጋጉባቸውና የተቸገሩት ናቸው። ምንም አይነት መመዘኛ የማይጠይቅ ክፍት የሥራ ቦታ መሆኑን የተረዱ ሌሎችም እንደዋዛ የሚገቡበት ሕይወት መተዳዳሪያቸው ሆኖ ይቀራል። እሷም በዚህ ሕይወት ለዘጠኝ ዓመታት መዝለቋ ከባድ ዋጋ አስከፍሏታል።

አንዳንዴ ማዕከላዊት ብሩን ስታገኝ አልጋ ይዛ ለብቻዋ ታድር ነበር። በአልጋ በኩል ካዛንቺስ በግ ተራ አካባቢ በተለምዶ ትንሿ ቤት ተብላ የምትጠራው ሆቴል ባለቤት አቶ ገብሩን ከልብ ታመሰግናለች። እሳቸው ለረጅም ጊዜ የረዱት ባለውለታዋ ስለመሆናቸው ፈጽሞ አትረሳም። ሰውየው ሁሌም እንደልጃቸው ያቀርቧታል። ያለችበት ሕይወት እንደሚለወጥና ከሴተኛ አዳሪነት ሕይወት መውጣት እንደሚኖርባትም ይመክሯት ነበር። ገብሩ ስታገኝ ትከፍያለሽ እያሉም ጎዳና እንዳታድር ለብዙ ጊዜ ያለክፍያ አልጋ ሰጥተዋታል።

በቅርብ ጊዜ አንዲት ክፍል የቀበሌ ቤት አግኝታለች። ቤቷ ከአንድ አልጋና ከአንድ የከሰል ማንደጃ በላይ አትይዝም። በጊቢው መፀዳጃና ውሃም የለም። በግድግዳው የሰፈሩ ሰው የየራሱን ዘመናዊ ቆጣሪ ሲያስገባ የረሳው የዱሮ መብራት ቆጣሪ አለው። ‹‹መድሃኒዓለም ክብሩ ይስፋና አሁን ላይ ከፍቼ የምገባባትና ቆልፌ የምወጣው ቤት አለኝ›› ስትል ፈጣሪዋን ታመሰግናለች።

የማዕከላዊት ቤት ጠባብና ምቹ ባትሆንም ለኑሮዋ መለወጥ ሰበብና ምክንያት ሆናታለች። እንደዋዛ ከገባችበት ሴተኛ አዳሪነት ያላቀቀቻት በመሆኑም ትኮራበታለች። ቀደም ሲል በወረዳ 8 አካባቢ ሁለት በአራት የሆነች የሀገር ባህል ልብስ መሸጫ ተሰጥቷት ስትሰራ ቆታለች። በቅርብ ጊዜ ግን አምስት ዓመት ሞልቶሻልና ልቀቂ በመባሏ ሃሳብ ይዟታል። ቀጣይ ሕይወቷ ምን እንደሚሆን ባታውቅም በአባቷና በእንጀራ እናቷ ስም የሚሰየም እንደ አገር ተግባሩን ወደ ልማት የሚለውጥ ራዕይ ሰንቃ መንቀሳቀስ ከጀመረች ዓመታት አስቆጥራለች።

ያለምንም ድጋፍ በራሷ ወጪና ተነሳሽነት በየቡና ቤቱና በየጎዳናው እየዞረች ግንዛቤ ታስጨብጣለች። ሃሳቧን የሚደግፍላት ካገኘችም በርካቶችን አስተባብራ የትኛዋም ሴት በዚህ ሥራ እንዳትሰማራ የሚያስችል የልማት ተቋም መመስረት ነው።

የማከላዊት ዕቅድና ሃሳብ የሰፋ ነው። በሴተኛአዳሪነት ሕይወት ያሉትንና ልጆቻቸውን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችለውን ፕሮፖዛል በወረቀት እያሰፈረችው ትገኛለች። የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አበቤ፣ እንደ አገርም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በእሳቱ ተሰማ ስም የምትቀርጸውን ፕሮጀክት ደግፈው ህልሟን እውን እንዲያደርጉም አበክራ ትማፀናለች።

ለመኖር፣ ሕይወትን ለማሸነፍ በርካታ ውጣውረድን የተሻገረችው የእውቁ ከያኒ እሳቱ ተሰማ ልጅ፤ ነገን በብሩህ መንፈስ ታስበዋለች። ዛሬ ላይ ቆማ በአባቷ ስም በጎ ታሪክ ለማስፈርም ከትናንትናው ሕይወቷ የሚበጀውን ወስዳ ሴተኛ አዳሪነትን ‹‹ሕይወቴ›› ላሉ ወገኖች መንገዶችን መቀየስ ጀምራለች። ማዕከላዊት ሕይወትን በአማራጮች መኖር እንደሚቻል ለማሳየት ሩጫውን የጀመረችው በታላቅ ጽናትና በተለየ ጥረት ሆኗል። እሷ የእሳት ልጅ ዓመድ እንዳትባል የከያኔ አባቷን ስም አክብራ ማንነቷን ለማስከበር እንቅልፍ ይሉትን አታውቅም። እያሰበች፣ ታቅዳለች፣ እያቀደች ትሞክራለች፤ ትናንትና ሕይወትን እንዲያ ኖራው ብታልፍም፤ ነገን ደግሞ ‹‹እንዲህ ይኖራል›› ለማለት ሃሳቧ አይነጥፍም፣ ህልሟ አይከስምም፣ ሩጫዋ አይገታም።

# ‹‹ የእኛ መሻት በውጊያ የተገኘውን ድል በሰላም መድገም ነው››

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር



ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱት ጥያቄዎች የሰጡትን ማብራሪያና ምላሽ ክፍል ሁለት ትናንት ማቅረባችን ይታወሳል። በዛሬው በክፍል ሶስት እትማችን ከሰላምና ድርድር፣ ከጸጥታ ተቋማት ዝግጅት፣ ከመፈናቀል፣ ህግ ከማስከበር፣ በመብት ተሞጋቾችና በማህበራዊ ሚዲያ ዙሪያ ለተነሱ ጥያቄዎች ጠቅላይ የሰጡትን ምላሽና ማብራሪያ ይዘን ቀርበናል።

**የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ምላሽ፡-**

በመጀመሪያ ግጭቱን፣ ጦርነቱንና የሰላም ሂደቱን በሚመለከት ለተነሳው ጉዳይ የተከበረው ምክር ቤት እንደሚያስታውሰውና እንደሚገነዘበው ከጅምሩ ጀምሮ የእኛ መሻትና ፍላጎት ግጭት የሚባል በአገር ውስጥም በአካባቢው አገራትም እንዳይኖር ማድረግ ነው:: ለምሳሌ ከኤርትራ ጋር የነበረውን ግጭት በሰላም እንፍታ ብለን ኤርትራ ድረስ የሄድንበት ዋነኛው ዓላማ በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል ሰላም ቢኖር የሁለቱም አገራት ህዝቦች ይጠቀማሉ ከሚል መነሻ ነው:: ይህ በቀጥታ ኢትዮጵያን የሚመለከት ጉዳይ ነው:: ነገር ግን ሶማሊያና ኬንያ ሲጋጩ ግጭት ተገቢ አይደለም፤ አንድ መሆን አለባችሁ ብለን የሶማሊያን መሪ ናይሮቢ ወስደን መሪዎቹን በማገናኘት ችግሩን ለመፍታት የሞከርንበት ምክንያት ቀጥታ ባይመለከተንም ግጭት ስለሚጎዳን ነው::

የደቡብ ሱዳን ምክትል ፕሬዚዳንቱ ከአገር ወጥተው ደቡብ አፍሪካ በነበሩበት ጊዜ ወደአገር እንዲመለሱና ድርድር እንዲጀምር ጥረት ያደረግነው የደቡብ ሱዳን ሰላም ለእኛ ስለሚጠቅመን ነው:: ሱዳን ከመፈንቅለ መንግስቱ በኋላ የገጠማት ችግር ሽግግሩ ሰላማዊ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና የተጫወተችው ኢትዮጵያ ናት:: በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአካባቢውም ሰላም እንዲኖር እንፈልጋለን:: የቀጣናው ሰላም ላይም ተሳትፎ አለን:: አሁን መግለፅ ማለት ባልፈልግም ከቀጣናችንም ባሻገር ባሉ በርካታ የሰላም ድርድሮች ውስጥም ተሳትፈናል::

ሰላም በጣም ወሳኝ ነው፤ ሰላም ያስፈልጋል:: ለሰላም የሚከፈል መስዋዕትነት ካለ ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለብን:: ለሰላም የሚሰጥ ማንኛውም ነገር ካለ ማድረግ ተገቢ ነው:: ሰላም ሁሌም የሚደናቀፈው በግጭት ነው:: ሰላም የሚወዱ ሰዎች ግጭት እንዳይፈጠር ይጥራሉ፤ ግጭት ሲፈጠር ደግሞ እንዲያጥር ይሰራሉ:: መልሰው ሰላም እንዲሰፍን ይታትራሉ::

እኛን በሰላም መፈለግ ጉዳይ ጥያቄ መጠየቅ የሚከብድ ይመስለኛል:: ምክንያም በሰላም ጉዳይ ከቤተክርስቲያን እስከ አለምአቀፍ ደረጃ እውቅና አግኝተናል:: ሰላም ፈላጊ መሆናችንን አለም ያውቀዋል:: የዛሬ ሁለት አመት መጪው መስከረም ዘመን መለወጫ ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ የትግራይ ህዝብ የጥይት ድምጽ ይበቃዋል፤ እንኳን ውጊያ የጥይት ድምጽ አያስፈልገውም ብዬ ሁለት ወር ሳይሞላው ነው ወደ ውጊያ የገባነው::

እኛ ከማንም ጋር ውጊያ አንፈልግም:: ትናንትም አንፈልግም፤ ዛሬም አንፈልግም፤ ነገም አንፈልግም:: እኛ የምንሳተፍበትም ብቻ ሳይሆን የማንሳተፍበትም አንፈልግም፤ የዩክሬንና የራሽያ ውጊያም አንፈልግም:: እኛ ውጊያ ሳይሆን ሰላም ነው የምንፈልገው:: ሰላም ትርፋማ ያደርጋል:: ሕወሓት ይህን ውጊያ ከመጀመሩ በፊት ስፖንሰር እያደረገ በየቦታው የሚፈጠረው መፈናቀል፣ በየቦታው ያለው ግጭት በገንዘብ ደጋፊውና አሰልጣኙ ማን እንደነበር ይታወቃል:: ልክ ግጭቱን ከፈጠሩ በኋላ በሚዲያዎቻቸው በርካታ የመጠራጠር ስሜት እንዲፈጠር ይሰሩ ነበር::

መከላከያ እየገነቡ፤ መከላከያን ከውስጥ እያፈረሱ ነበር፤ በየቦታው በሚፈጠረውን ግጭት በመከላከል ስንባዝን በመዘጋጀት ጊዜውን ለመጠቀም ሞክረዋል:: አሁን ሸኔ የሚባል ከሪፎርም በፊት አራት ሺ፣ አምስት ሺ ሀይል የሌለው፤ በየወሩ አንድ ሺ፣ ሁለት ሺ እየተማረከ እየተገደለ የሚፈለፈለው ከየት ነው? ምንጩ ከየት ነው? ትንሽ ከመንደር ንግግር ወጣ ብሎ ማየት ያስፈልጋል:: እናም የግጭቱ ዋንኛ መንስኤ ሕወሓት የፖለቲካ ሽንፈቱን እየዋለ እያደር መቀበል በመቸገሩ ነው ። እኛ መጀመ

እንደምታውቁት እስክሪፕቶ እና ሀሳብ ብቻ ነው ያለን:: ጦሩም ታንኩም ብሩም በእነርሱ እጅ ነበር::

ካሸነፍን በኋላ ያንን ሽንፈት መቀበል ስላልቻለ፤ ሽንፈቴን በጉልበት ላሳካው እችላለሁ:: አንድም እያበጣበጥኳቸው ካልሆነ መጥቼ ነው ያሉት:: ይሄን መንግስት በአጭር ጊዜ እናፈርሰዋለን ብለው ሲናገሩ ነበር:: መንግስት እጥላለሁ፤ አገር አፈርሳለሁ፤ ህዝብ አናክሳለሁ፤ ይህ እንዲሳካ ሲኦልም እገባለሁ አሉ:: ተው አያዋጣም እያልን ነበር:: እየተዋጋን እንኳን ሁለት ሶስት ቀን ይሄ አያዋጣምና እጃችሁ ስጡ፤ ይቅር እያልን ነበር::

መጀመሪያ ለምን ተዋጋችሁ የሚል ሰው ካለ፤ እኛ ተከላከልን እንጂ አልተዋጋንም:: ታንካችንን ጀነራላችንን፣ ወታደራችን በተኛበት በገዛ ቤተሰቡ ታፍኖ በሺ የሚቆጠር ሰው እንዲሁም ንብረት ስለተያዘብን ልንከላከል ነው የተንቀሳቀስነው፤ ያንን የተያዘብንን ሰውና ሀብታችንን አስመለስን:: እንዳንወጣ ደግሞ ህዝቡ ተቸገርኩ አለ:: ከዚያ በፊት ታስታውሱ ከሆነ መውጣት እናስብ ነበር:: ሌላ የምንሰጋባቸው አካባቢዎች ስለነበሩ:: አትወጡም የተባልነው በሕወሓት ነው:: ሰው እያስተኙ አትወጡም አሉን:: በሌላ በኩል እንዳንወጣ ደግሞ ውሀ፣ መብራት፣ መንገድ እንዲሁም የጤና ችግር አለ ስንባል ህዝባችን ነው በሚሊዮን በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ መድበን ስንሰራ ነበር:: እኛ ልማቱን ስንሰራ እነርሱ ዝግጅት ያደርጉ ነበር::

የዓለም ሚዲያ ደግሞ ዘመቻ ጎን ለጎን ይከፍትብናል፤ ስለዚህም የእኛ መኖር ካልተመቻቸው ሲፈልጉን እንገናኛለን በሚል እሳቤ ለመውጣት ስንሞክር ደግሞ ጊዜው አሁን ነው ብለው በሰልፍ የምታውቁትን አይነት ጦርነት አካሄዱ:: ያኔም ተከላክለን ወደክልል ከመለስናቸው በኋላ ከዚህ በኋላ አንቀጥልም፤ ብንቀጥል ረሀብ፣ ስደት እንዲሁም መፈናቀል ይመጣና ተጨማሪ ጣጣ ነው ብለን ተውነው:: በሂደት ውስጥ እኛ የተከተልነው መንገድ ኢትዮጵያ አንድም ቀን ቢሆን ሰላም እንድታገኝ ነው::

ይሄ ብቻ አይደለም፤ ሪፎርም ከመጣ በኋላ ኤርትራ ያሉ ግንቦት 7፣ ኦነግ፣ ኢህአፓና ሌሎች ስማቸው ብዙ የሆኑ ፓርቲዎችን ኑ ግቡ በጋራ አገር እናልማ አላልንም እንዴ? በምርጫ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የኢትዮጵያ ህዝብ ተሰልፎ ከመረጠን በኋላ ግዴለም ብቻችንማ አንመራም፤ በፌዴራልም በክልልም የሚፎካከሩ ፓርቲዎች ምርጫ ከተወዳደሩ ይግቡ ብለን ፓርቲዎች የካቢኔ አባላት ሆነዋል:: ሶስት የካቢኔ አባላት የሚፎካከሩ ፓርቲዎች ናቸው:: በዓለም ላይ አሸንፎ መቀመጫ የሚጋራ አንድም ፓርቲ አታገኙም:: ከተሸነፈ ይጋራል:: ካልተሸነፈ ግን አይጋራም:: ይቅር፤ ባህል ይቀየር፤ አብረን እንስራ ነው አላማው::

ይህ በመረታታትና መጠናከር አለበት:: አንዳንዶቹ ግጭት በገጠመን ወቅት እዚህ ፓርላማ ያሉ አባላት ጭምር ከብልፅግና አባል ባልተለየ ሁኔታ ኢትዮጵያን ሊከላከሉ ተሰልፈዋል:: ስለዚህ ፓርቲ የሚለው ጉዳይ ሁልጊዜ የማይሰራ አንዳንዴ በትብብር ልንሰራ የምንችልባቸው ጉዳዮች መኖራቸውን የሚያመላክት ነው። ለዚህም ስልጣን ብንጋራ ችግር የለውም:: አብረን አገር ብናቀና፤ ብናለማ ችግር የለውም:: ምንድነው የነበረው ችግር ያላችሁኝ እደሆን ጽንፈኝነትና ጥላቻ ነው:: ብሄር መጥላት፣ ሰው መጥላት ነው:: ጥላቻ መርዝ ነው::

ይሄውላችሁ ባለፉት ሀምሳ አመታት ዩናትድ አረብ ኢምሬትስ በተለምዶ ዱባይ፣ አቡዳቢ የሚባለው አገር

ሼህ ዛይድ ጀምረውት አሁን ሼህ መሃመድ የሚመሩት አገር በሃምሳ ዓመት ውስጥ ዱባይን ከአፈር ወደ ወርቅነት ቀየሯት:: ከድንኳን ታይቶ ወደማይጠገቡ ህንጻዎች ቀየሩ:: በልቶ መጥገብ ሳይሆን እንደኛ አይነቱን መቶ ሚሊዮን ቁጥር ያለውን ህዝብም የሚያበላ ሃብት ፈጠሩ፤ ይህ የሆነው በ50 ዓመት ውስጥ ነው:: ከምንም ተነስተው እጅግ አስደማሚ ውብ በዓለም ተመራጭ አገር ፈጠሩ:: የሚያደምጥ፣ የሚከተል፣ የሚያግዝ፣ ልማት የማያደናቅፍ ህዝብና የሚሰሩ አመራሮች ተባብረው አገራቸውን ቀየሩ::

ይሄን ቁጥር እኛ ጋር አምጡት ሕወሓት ሲቀነስ ሲደመር 48፣ 47፣ 49 ዓመት ታግሏል:: ቢያንስ ትግራይን ከ81 ጀምሮ እስካሁን እያስተዳደረ ነው:: 30 ምናምን ዓመት ነው:: ባለፉት 50 ዓመታት ወይም 48 ዓመታት የሕወሓት ትግል የትግራይ ህዝብ ምን አተረፈ? ካላችሁ ጥላቻ፣ ጦርነት እና ልመና ነው:: የዛሬ 50 ዓመትም ችግር አሁንም ችግር፤ የዛሬ 50 ዓመት መሰረተ ልማት የለም፤ አሁንም የለም:: የዛሬ 50 ዓመትም ስደት አለ፤ አሁንም ስደት አለ:: አንዳንዶች በ50 ዓመት የሌለ አገር ያደርጋሉ:: እነዚህ በቁጥርም በስፋትም ከትግራይ የሚያንሱ ናቸው::

አንዳንዶች ደግሞ እነሱ ለ50 ዓመት ኮብራ ይቀያይራሉ፤ ሰው እዛው ነው:: በሕወሓት አጠቃላይ ትግል አንድ ሺ፣ ሁለት ሺ፣ አምስት ሺ፣ አስር ሺ የዛ አካባቢ ሰዎች ኮብራ ነድተው ሊሆን ይችላል፤ የትግራይ ህዝብ ግን ምንም አላገኘም:: ይህን እንኳን ቆሞ ለማሰብና የኛ መፈጠር ምንድን ነው? ሕወሓት ከናካቴው ባይፈጠር የትግራይ ህዝብ ምን ያጣ ነበር? ብሎ እንኳን ለማሰብ ዝግጁ አይደለም:: አንዳንዶች አሁን ፓርቲ ስንሆን በእኛ መፈጠር በህዝባችን ላይ ምን የተሻለ ነገር እንጨምራለን የሚለውን አብረን ካላየን በስተቀረ መፈጠርና ዕድሜ መቁጠር ብቻ ዋጋ የለውም::

ጦርነቱ የእኛ አይደለም፤ እየለመንን ነው አትችሉም አይችሉም ተብለን የገባንበት። ብዙዎች ልካችንን ስለማያውቁ በልካቸው እያሰቡ የሞኩራት ጉዳይ ነው፤ ያኔም ዛሬም ያለው:: የእኛ መሻት በውጊያ የተገኘውን ድል በሰላም መድገም ነው:: በውጊያ አትፈርስም ብለን አገር አስቀጥለናል:: ኢትዮጵያ በልማት ጎዳና ላይ ነው ያለችው ጥያቄ የለውም:: ብዙ ፈተናዎች መቋቋም የሚችል ተቋም እየገነባች ነው ጥያቄ የለውም፤ አይታችሁታል::

ለልጆቻችን ቁርሾ አንተው፤ ጥላቻ አንተው:: እኛ ዋጥ አድርገን ስሜታችንን ወደሰላም እንሂድ:: የምንፈልገው

# ወቅታዊ

ይህንን ነው:: ከሕወሓትም ከማንም ሰው ሰላም ፈላጊ ከሆነ ሰው ሁሉ ጋር ሰላም ነው የምንፈልገው:: ለምን ከተባለ ከእያንዳንዱ የሰላም ቀን ትርፍ ስለምናገኝ ነው:: ጥይት ይተኮሳል፤ ዶላር ነው፤ ሰው ይሞታል፤ ወጣት ነው:: ሽማግሌ አይደለም የሚሞተው፤ ወጣት ነው፤ ሊሰራ የሚችል ሰው ነው የሚሞተው:: በዛም ሞተ በዚህም ሞተ ያው ነው:: ማስቀረት የሚቻል ከሆነ ለሰላም መቆም ችግር የለውም::

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ናይጄሪያ ተገናኙ፤ ሶማሊያ ተገናኙ፤ አውስትራሊያ ተገናኙ፤ ሶሪያ ተገናኙ፤ የሚባል ተረት ግን ተረት ነው:: አጋጣሚ ናይጄሪያ በነበርኩበት ጊዜ እኔ ከናይጄሪያ መንግስት ጋር በነበረን ንግግር በጣም በርካታ ጉዳይ ነበረን:: እንዳጋጣሚ ሆኖ ለአንዲት ሰከንድ ሕወሓት የሚል ቃል አልተነሳም፤ እነሱም ትኩረታቸው አልነበረም:: እንደውም አልፎ አልፎ እንደምንጠየቀው የሰሜን ጉዳይ ምን ሆነ አላሉንም፤ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ነው ጊዜ ያባከነው:: ግን ናይጄሪያ፣ ሶሪያ ሶማሊያ እየተባለ ይነገራል፤ እሱ ስህተት ነው::

ክቡር ዶክተር ጫኔ ላነሱት ጉዳይ ፓርላማው ብቻም ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብም ንግግር ሰላም የሚፈልግ ቢሆንም የማውቀው መብት አለው:: እና ብልጽግና ተሰብስቦ ከእንግዲህ በኋላ ያለውን ጉዞችንን እንዴት ነው የምንፈታው ብሎ አሁን ወጥተው የሚያሙትም ጭምር ባሉበት ስብሰባ ላይ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አቋቁሟል:: ይህ ኮሚቴ ክቡር አቶ ደመቀ መኮንን የሚመሩት ኮሚቴ ነው:: ሰላምን በሚመለከት ኢትዮጵያ ምን ምን ትፈልጋለች? ዝም ብሎ ድርድር አይካሄድም ብዙ ስራ አለ:: ምን ሲሳካ ነው የምንነጋገረው እንዴት ነው የምንነጋገረው የሚለውን ጉዳይ የሚያጠና ኮሚቴ ተቋቁሞ፤ ኮሚቴው ሲያጠና ቆይቷል::

እስካሁን ለስራ አስፈጻሚ ሪፖርት አላቀረበም፤ ምናልባት በሚቀጥሉት አስር አስራ አምስት ቀናት እንጠብቃለን:: ኮሚቴው ሪፖርት ይዞ ሲቀርብ አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት ሲሚሉልኝ ንግግር ማድረግ እችላለሁ፤ በዚህ በኩል ይሄ ይሄ እንዲሟላ እፈልጋለሁ፤ እኔ ደግሞ ይሄን አደርጋለሁ፤ ለሰላም ስል ይሄን ዋጋ እከፍላለሁ የሚል ሃሳብ ሲመጣ ለህዝባችን በግልጽ እናውጃለን:: የሚደራደረውም ኮሚቴ ይሄው ኮሚቴ ነው፤ እኔ ናይጄሪያ ሄጄ ሶማሊያ ሄጄ የምገናኝበት ምንም ምክንያት የለም:: አጥንቶ አውቆ የሚሰራ ኮሚቴ ተመድቧል::

ብዙ ጊዜ እኛ ስለ ስንዴ ስንናገር ሰው አያምንም፤ ሰው የሚያምነው ዶክተር ሲናገሩ አኪና ዲሲና ሲናገሩ ነው:: ኢትዮጵያዊ እንደዚህ ነው፤ ምን እናደርጋለን:: በትዊተር ሲነገር ነው እንጂ የሚታመነው እኛ ስንል አይታመንም:: የ‹‹ኢንትሪክ፣ የኮንስፓይረንሲ›› ፖለቲካ ልምምድ ስላለን ሁሉም በዛ ይታያል:: እኛ ውጊያ አልደበቅንም፤ ውጊያ ተነስቷል፤ አገር ተደፍሯል፤ በቃ እንዋጋለን ብለን ለህዝባችን ነግረን ውጊያ የገባን ሰዎች ነን:: ታድያ አሁን ሰላም ለማምጣት ምን አስደበቀን:: ሰላም የሚደበቅ ነገር አይደለም:: ምክንያቱም ውጊያውንም አልደበቅንም:: እናም ዝም ብሎ መሰቃየት አያስፈልግም:: ጊዜው ሲደርስ እና ንግግር ሲጀመር እንናገራለን::

አሉባልታው፣ ስሞታው፣ ሽኩቻው ብዙ ነው:: ያ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን አማራ ሳያውቅ የተባለው ስህተት ነው:: ሕወሓት የአማራ ጠላት ሳይሆን የኢትዮጵያ ጠላት ነው:: የተዋጋውም ኢትዮጵያ ነው፤ የሞተውም ኢትዮጵያ ነው:: ይሄ ነገር ሰንጥቆ ለራስ መውሰድ ትክክል አይደለም:: አማራ የሚደራደር ከሆነ፤ አማራ ብቻ እዛ ይዋጋ:: እዛ እየሞተ ያለው ኢትዮጵያዊ ነው፤ የሚደራደረውም ኢትዮጵያዊ ነው:: ጠላቱም የኢትዮጵያ ነው፤ ሕወሓት በአማራ ብቻ የሚቆም አይደለም:: አማራን ቆርጥሞ፣ ኦሮሞን ቆርጥሞ የሚቆም አይደለም:: ከጨረሰን ወደ ሌላ ጎረቤት አገር ይቀጥላል:: ለብቻ የተሰራ ስራ የለም፤ በጋራ እንሰራዋለን::

አጋጣሚ ሆኖ ኮሚቴውን የሚመሩት አቶ ደመቀ ናቸው:: ሌላ አማራ ፈልገን ካላመጣን በስተቀረ የአማራን ጥቅምና ሁኔታ ይገነዘባሉ:: አማራ ተወላጅ የሆኑም የአፋር ተወላጆችም ሶማሌዎችም በኮሚቴው ውስጥ ስላሉበት በጋራ እየሰሩ ነው:: እኛ የምናስበው የኢትዮጵያን ችግር፣ የኢትዮጵያ እዳ፣ የኢትዮጵያ ፍዳ ነው፤ ኢትዮጵያዊያን በጋራ እንቋቋመዋለን ብለን ነው የምናስበው:: እና ነገሩን ዝም ብሎ ወደታች ማውረድ ጥሩ አይደለም:: በነገራችን ላይ ስለፖለቲካ ስንናገር እዛ ሰራዊቱ ጋር የሚያመጣውን

**የኢትዮጵያ መንግስትም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት ግን አንድም ጥይት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይተኮስ ነው:: ለጥይት የሚወጣው ዶላር ለመድሃኒት፣ ለግንባታ እንዲውል ማድረግ ነው:: ይህ የእኛም የህዝባችንም ፍላጎት ነው:: ማነው ጦርነትን ያለ ልክ የሚያስጨኸው? መዋጋት የማይችለው ነው**

ችግር ማሰብም ጥሩ ነው:: እየሞተ ያለውን፣ በጸሃይ እየተቃጠለ ያለውን ሰው ምንም አያገባህም ካልነው አደገኛ ነው:: በኋላ ችግር ያስከትላልና በዛ አይን ማየት ጠቃሚ ይሆናል::

የኢትዮጵያ መንግስትም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት ግን አንድም ጥይት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይተኮስ ነው:: ለጥይት የሚወጣው ዶላር ለመድሃኒት፣ ለግንባታ እንዲውል ማድረግ ነው:: ይህ የእኛም የህዝባችንም ፍላጎት ነው:: ማነው ጦርነትን ያለ ልክ የሚያስጨኸው? መዋጋት የማይችለው ነው:: ስንዋጋ የለም ስንመለስ ተዋጉ ይሉናል:: በየአገሩ ተቀምጦ ውጊያ ሰፈር ሳይደርስ ውጊያ ውጊያ የሚል አለ፤ ውጊያ እኛ አንወድም:: በጣም ነው የምንጠላው:: እኔ በ14ዓመቴ ነው ክላሽ የተሸከምኩትና አውቀዋለሁ፤ ስለዚህ አልፈልገውም:: ማየት አልፈልግም፤ ብዙ ሲበላ አይቻለሁ፤ ውጊያ ጓደኛ የሚበላ፣ ወንድም የሚበላ አደገኛ በሽታ ነው::

ውጊያ ሳይሆን የምፈልገው ልማት ነው:: ማነው ውጊያን የሚወደው ? ውጊያን የማያውቅ ብቻ ነው:: ሰላም እንፈልጋለን ማለታችን የተደበቀ ድርድር እናደርጋለን ማለታችን አይደለም:: የተደበቀ ድርድርም ፍሬ የለውም:: አሁን ተደራድረን ለምሳሌ መብራት ይገባላችኋል ብሎ መንግስት ቢወስን ሰሞኑን እንደሚወራው፤ መብራት ሲገባ አይታይም እንዴ? መብራት እኔ አላስገባ፤ መደበቅ እኮ አይቻልም:: ደብቆ ድርድር፣ ደብቆ ምናምን የሚባል ነገር ብዙ ቦታ የለውም:: ግን ለሰላም እስከሆነ ድረስ እናንተ በርቱ አይዟቹ ሞክሩ አቅማችሁ እስከቻለ ድረስ ሰላም አምጡ በርቱ ነው ማለት ያለባችሁ:: የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም አቅጣጫ መሆን ያለበት ወደ ሰላም ሂዱ፤ ኢኮኖሚ የለንም፤ ብዙ ደሃ አለን፤ የዋጋ ግሽበት አለ፤ የሚል ምክር ቢሆን ይበልጥ ጠቃሚ ይመስለኛል::

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የጸጥታ ተቋማት ዝግጅታቸው ምን ይመስላል የሚለው ተነስቷል፤ የኛ የጸጥታ ተቋም ለሕወሓት አይደለም የሚዘጋጀው:: የእኛ የጸጥታ ተቋም ሕወሓት የሚልከውም የሚያስበውም የሚመኘውም የኢትዮጵያን ህልውና እገዳደራለሁ ካለ ኢትዮጵያ የተባለች ድንቅና ታሪካዊ አገር አጽንቶ ለማስቀጠል ነው የሚዘጋጀው:: የሰፈር ዝግጅት ብቻ አናደርግም:: ይህማ ሞኛ ሞኝ ሃሳብ ነው፤ ጦር አዘጋጅተን ከሕወሓት ጋር በሰላም ቢያልቅ እናፈርሰዋለን ማለት ነው? ሕወሓትን የላከው አካል ሌላ ተላላኪ ይፈልጋል:: እና ዝግጅቱ ኢትዮጵያን ለማስቀጠል ነው::

እንዳያችሁት ደግሞ ጅማሮው ጥሩ ነው፤ ብዙ ስራ ይጠበቅብናል:: ምንም ጥያቄ የለውም፤ ገና ነው:: ቢያንስ ቢያንስ ግን አሁን ያለው ጦር ሕወሓት ካለበት ሁለት ሶስት እጥፍ በቁጥርም በቴክኖሎጂም በአቅምም ይሻላል:: ይሄ ጥርጣሬ የለውም፤ ይሄ በቂ ነው አይደለም ከተባለ በየቀኑ የሚወለድ እውቀትና ብቃት ስላለ አብረን ማደግ አለብን፤ መማር አለብን:: ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ናት፣ ሃብታም አገር ናት፤ ታላቅ አገር ናት፤ ስመጥር አገር ናት :: ልጆቿ ስላልገባቸው ቢያረክሷትም በአፍሪካ ቁንጮ የሆነች አገር ናት፤ መቀጠል አለባት:: እሷን የሚያስቀጥል ተቋም ይገነባል:: ተቋም ሲባል ግን ዶክተር እንዳነሱት የፊዚካል (አካላዊ) ውጊያን የሚከላከል ብቻ አይደለም:: የቨርቹዋል ውጊያው ከፊዚካል ውጊያው እየበለጠ ነው::

ለምሳሌ ዘንድሮ በሳይበር ጥቃት በዓለም አቀፍ ደረጃ የደረሰው ጉዳት ከምንገምተው በላይ ነው:: 16 ቢሊዮን ዶላር በቀን በሳይበር ውጊያ / ዎርፌር/ ጥቃት ጉዳት ይደርስበታል:: በዓለም ላይ በአንድ ሰዓት ውስጥ 685 ሚሊዮን ዶላር ጥቃት ይደርሳል:: በዓለም ላይ በአንድ ደቂቃ 11 ሚሊዮን እንዲሁም በአንድ ሰኮንድ 190 ሺ ዶላር የሚያክል ጉዳት ይደርሳል:: ይህ ቀላል ነገር አይደለም:: እኛ ከተዋጋንበት ውጊያ ሀብት በብዙ እጥፍ ይበልጣል:: ኢትዮጵያ ላይ ባለፉት 9 ወራት ብቻ 5 ሺ 860 ገደማ የቨርቹዋል ጥቃት ተካሂዷል:: ስድስት ሺ ጥቃት ደርሶብናል ማለት ይቻላል:: በሚሊዮን ብር ያጣንበት አለ፤ በቢሊዮን ያዳንንበት አለ:: እርሳቸው እንዳነሱት፤ በዋናነት ፋይናንሻል ሴክተር፣ አይ.ሲ.ቲ፣ ኢንፍራስትራክቸር እና ሬኢንፎርስመንት ኤጀንሲስ፣ መንግስት ተቋማት እና ፕሮጀክቶቻችን በብዙ መንገድ ይሞከራሉ::

ፕሮፋይሊንግ ላይ የሚሰራ ስራ አለ:: ሳይበር ኤክስፕሎይት ለማድረግ የሚሰራ ስራ አለ፤ ሳይበር ወርፌር አለ:: ለምሳሌ ኮሮና መጣ፤ እኛ ዘንድ እንኳን ብዙ ችግር የለውም፤ አፍሪካ ግን በየሜዳው ሬሳ ይታያል፤ በሚሊየኖች ይሞታሉ ተባለ:: እኛ ደጋጎች ነን፤ ከዚህ ሲሆን አንሰማም፤ ከውጭ ሲሆን እንሰማለን:: ሁሉም ሙያተኛ እንዲባል አፍሪካ በየመንገዱ ይሞታል እያለ ሪፖርት ጽሁፍ ያወጣ ነበር:: ሞትን እንዴ? ፈጣሪ እኮ ደግ ነው፤ አልሞትንም:: አሁን ደግሞ ችግር አለ አለም ላይ አለ:: ችግሩን ወደ አፍሪካ ሲያመጡት አፍሪካ በረሀብ ምክንያት ይሰደዳል እያሉ ነው::

እነሱ የማይራቡ የማይቸገሩ ነው የሚመስላቸው:: ግን አይደለም:: እንደዚህ አይነት አጀንዳ ኤክስፖርት አድርገው ሞኛ ሞኞች እያጫወቱ ኑሯቸውን ለመግፋት የመጣር ፍላጎት እዚህም እዚያም አለ:: ተሰብስበው ኮንፍረንስ ምናምን ብለው ተቀምጠው ሳያፍሩ አፍሪካ በረሀብ ትሰደዳለች ይላሉ:: አፍሪካ ኤክስፖርት ብታደርግስ? እንደዚህ አይነት ጨዋታዎች አሁን ለምሳሌ ድርድር እንደሚባለው ድርድር በጣም ይገርመኛል፤ ድርድር የሚጭበረበርበት መንገድ፤ ለሰላም መነጋገር የከፋ ይመስል ሆን ብሎ፣ ቁጭ ብሎ የሚሰራ ሰው አለ:: ለምን? በውስጣችን መጠራጠር በውስጣችን መባላት እንዲፈጠር የሚደረግ ሙከራ ነው:: እና ሰላምን በሚመለከት በቨርቹዋልም በፊዚካልም የሚደረግ ማንኛውም ጥቃት አቅም በፈቀደ መጠን ለመከላከል እና ኢትዮጵያን እንደ አገር ለማስቀጠል ይሰራል እየተሰራም ነው:: ይሄ እንደተጠበቀ ሆኖ በሰላም የሚገኝ ማንኛውም ድል ካለ ደግሞ ቢበዛ ሰላም ለማምጣት እንሰራለን::

ሪፖርቱ ለስራ አስፈጻሚ ሲቀርብ ወዲያው ለህዝባችን እናሳውቃለን:: በእነዚ በእነዚህ ነጥቦች ለመነጋገር ዝግጁ ነን ብለን:: ለመነጋገር የምንፈልግበት ምክንያት እኮ በጣም ብዙ ነው:: አለም በሙሉ ነው የሚያናግረን፤ እናንተን የሚያክል አገር እንዴት ይህን ችግር አይፈታም እያለ ያናግረናል:: አይ ግዴለም እኛ እንዋጋለን አይባልም:: የምንኖረው ከአለም ጋር ነውና:: በዚህ በኩል እየለመንክ፤ በዚህ በኩል እየፎከርክ እንዴት ይሆናል:: የግል ክብር ብቻ ሳይሆን የአገር ጥቅም ይጎዳል:: ይሄን ታሳቢ ያደረገ አካሄድ መሄድ ጥሩ ነው::

ሰላም ከመጣ አንደኛው ተጠቃሚ የትግራይ ህዝብ ነው:: መፈናቀል ብላለች እህቴ፤ አንደኛው የሚጠቀመው የትግራይ ህዝብ ነው:: ከፍተኛ ችግር ላይ ስለሆነ፤ ይሄ ፓርላማም ለእዚያ ህዝብ መቆርቆር አለበት:: ከሆን አይቀር ድንበር ላይ ብቻ ሳይሆን፤ ትግራይ ላይ ስደት፣ ረሃብ፣ ችግር እየበዛ ነው:: ሰዎቹ ግድ የላቸውም:: ሰዎቹ ጄነሬተራቸው ነዳጅ ካገኘ እነሱ የኤሌክትሪክ ሃይል ጉዳይ አያስጨንቃቸውም:: እነሱ ውሃ ካገኙ የሌላው ሕዝብ ማጣት ጉዳያቸው አይደለም፤ መሃል ላይ ህዝቡ ይጎዳል ብሎ ማሰብ ከሁላችን የሚጠበቅ ነው:: በዚህ አግባብ ማየት አለብን:: በሰላሙ ትግራይ ከተጠቀመ በኋላ አፋርም አማራም፣ ኦሮሚያም፣ ደቡብም ሁሉም ይጠቀማል::

ሰላም ከመጣ ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን ጎረቤትም ይጠቀማል:: በዚህ ጦርነት እኮ ቀጠናው ላይ በብዙ የሚነግድ ሰው አለ:: የሚያቀባብል አለ፤ ለዚያ ሁሉ መፍትሄ ይሆናል:: እንግዲህ እኛ ሰላም ፈለግን ማለት፤ እኛ ለሰላም ተጋን ማለት በዚያው ልክ ግብረ መልስ እናገኛለን ማለት ላይሆን ይችላል:: እኛ ግን ሁልጊዜ የምናውጀው ሰላምን ነው:: የምንለምነው ለሰላም ነው:: ሰላምን አልፈልግም ኢትዮጵያን አፈርሳለሁ ብሎ ከመጣ ‹‹እኔን ካፈረስከኝ በኋላ ነው፤ አትችልም::›› ብለን እንከላከላለን::

ይሄን ያደረግነው እና የምናደርገውም ጉዳይ ነው:: ስለዚህ ሰላምን ጥያቄ ውስጥ ማስገባት ተገቢ አይደለም:: በዚህ አይነት ማየት ጥሩ ነው:: አሉባልታውን ወሬውን እንተወው:: እርሱ ከመከፋፈል ውጪ ጥቅም የለውም:: ሲደርስ እና ሲያስፈልግ በግልጽ የምናየው እና የምንሰማው ይሆናል::

ከህግ ማስከበር ጋር ተያይዞ ለተነሳው ጥያቄ በመጀመሪያ የህግ ማስከበሩ ስራ የተጀመረው የብልጽግና አባላት ሆናችሁ ጉባኤ የተሳተፋችሁ ሰዎች ታስታውሱታላችሁ:: ጉባኤው ላይ አንዱ አጀንዳ ህዝባችን እናድምጥ፤ የህዝባችን ስሜት እንረዳ ብለን ነው፤ ጉባኤውን በጨረሰን ማግስት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ አካሄድን:: ስብሰባው ላይ በመጀመሪያ የተወያየንበት ጉዳይ ህዝባችን ጋር ሄደን እንወያይ፤ ህዝባችንን እናነጋግር ተባባልን::

ከዚህ ጉባኤ ህዝቡ ብዙ ነገር ይጠብቃል፤ ምን እንደሚለን እንስማ አልን:: በአገር ደረጃ ሁሉም ሰው ተሰማርቶ ውይይት ተካሄደ:: ብዙ ጉዳይ ተነስቷል፤ ከነዚህ ውስጥ ሶስት አንኳር ጉዳዮችን ልጥቀስ:: አንደኛው ሰላም ሰላም ሰላም የሚል ከሰላም ጋር የሚያያዝ ጉዳይ በሁሉ አካባቢ ተነስቷል:: ሁለተኛ የዋጋ ግሽበት፤ ኑሮ ተቸገርን፤ እኛ መርጠናችኋል እንድትሰሩልን እንፈልጋለን፤ መርጠናችኋል ግን ባካችሁ መፍትሄ አምጡ የሚል ከፍተኛ ጥያቄ ነበር::

ሶስተኛው ስለመልካም አስተዳደር ነው:: በኑሮ ውድነት ላይ ሌቦች አስቸገሩን፤ የማይሰሩ ሰዎች አስቸገሩን፤ ይሄን ነገር መንግስት አንድ ይበለን የሚል ጥያቄ ነበር:: ብዙ ጉዳይ ነበር:: ነገር ግን ዋና ዋናው ሶስቱ ጉዳዮች እነዚህ ነበሩ:: ይሄንን ማዕከላዊ ኮሚቴው ከተመለሰ እና ከተወያየን በኋላ በአገር ደረጃ ጥናት እንዲጠና አደረግን:: ጥናቱን በጋራ ስናይ ኦሮሚያ፤ አማራ፤ ቤኒሻንጉል ሶስቱ ላይ በጣም ሰፋ ያለ ከሰላም ጋር የሚያያዝ ችግር አለ:: አዲስ አበባ ላይ ደግሞ ቀማኞች፤ በሞተር ሳይክል እየሄዱ ቦርሳ እና ሞባይል የሚቀሙ እንዲሁም የጠላት ወኪል የሆኑ ሰዎች በስፋት አሉ::

በሌላ በኩል ሶማሌ ላይ ኮንትሮባንድ እና አልሸባብ አለ:: መንግስት ትኩረቱ ሰሜን ስለሆነ የኮንትሮባንድ ትስስሩ (ኔትወርክ) እንዲሁም አልሸባብ እያስፋፉ ነው:: እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት እናድርግ አልን:: ሌሎቹ ደግሞ ሥራቸውን ይሥሩ የሚል ስምምነት አደረግን:: ይሄ በጥቅሉ አንድ ወር ተኩል፤ ሁለት ወር ሊሆን ይችላል::በዚህ ሁለት ወር ተኩል ኦሮሚያ ክልል መሠረታዊ ዘመቻ ተካሄደ:: ኦሮሚያ ክልል ከ1ሺ በላይ የሸኔ አባላት ተገድለዋል:: በብዙ ሺ ተማርከዋል::

አንዱ በጣም መሠረታዊ የሚባል ውጤታማ ስራ የተሰራው ኦሮሚያ ነው:: ሁለተኛው አማራ ክልል ነው:: አዲስ አበባ እና ቤኒሻንጉል ላይም ሰፊ ስራ ተሰርቷል:: አልሻባብ እና ኮንትሮባንድን በሚመለከትም ተሰርቷል:: በድምሩ የገመገምነው በባለፈው ከህዝብ ውይይት በኋላ ሰላምን የማረጋገጥ፣ ህግ የማስከበር ስራችን ውጤት እያመጣ ነው:: ብለን ገምግመን ህዝቡን ደግሞ እናወያየው አልን:: ህዝቡን ደግሞ አወያይተን በቅርቡ ከነበረው ሪፖርት ከጫፍ ጫፍ የሰማሁት ህዝቡ ደስተኛ ነው የሚል ነው:: አማራ ክልል ብቻ ሳይሆን በሰላም ማስከበሩ ምእራብ ጎጃም በጣም ደስተኛ ነው:: ይህን ከተቻለ አቶ ክርስቲያን ሄደው ቢያወያዩ ጥሩ ነው:: ሰሞኑን ጠፍተዋል የሚሉ ሀሜቶች ሰምቼ ነው፤ ቢያወያዩ እውነቱን ነው ደስታውን ይሰሙታል::

ህዝቡ ለምን ደስተኛ ሆነ? ያላችሁኝ እንደሆነ፤ አማራ ክልል እናቶች መተኛት አይችሉም ነበር:: ማታ ማታ ጥይት

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ



ይንጣጣ ነበር። በየከተማው ልክ እየተንጣጣ ሲያድር የምናመርት ይመስላል። በዶላር የማይመጣ ይመስል። ጠላት ጎኑ ተቀምጦ ተከብቤያለሁ እያለ ነገር ግን ዝም ብሎ ሲተኩስ ያድራል። ሰው ይጨነቃል፤ የወጣ ልጅ ካለ ይጨነቃል፤ ይሄን ደግሞ እናንተ በደንብ ታወቁታላችሁ። ሥርዓት ወደ ማስያዝ ሳንገባ ከተቻለ በሰላማዊ መንገድ ትጥቅ ይፈታ ሞክሩ አልን።

ክቡር አቶ ክርስቲያን እኔ ባለኝ መረጃ ከአማራ ክልል ፕሬዚዳንት ጋር እርስዎ ራስዎ በሰላም አስገባለሁ ብለው ውይይት ለማድረግ መሞከርዎን አውቃለሁ። አሁን ሳይሆን ቀደም ብሎ ባለው ሁኔታ ተነግሮኝ፤ በሰላም ከተቻለ ሳንያያዝ ይሞክሩ ብዬ እርስዎ እንኳ እንደሞከሩ አውቃለሁ። በሰላም የሚመጣ ነገር ካለ ደስ ይለናል። እኛ ውጊያ ምን ያደርግልናል? የሚወጣው ገንዘብ እኮ ነው። ከህይወት ብቻ ሳይሆን ከትንሿ ነገር ጀምሮ ኪሳራ ነው፤ አስፈላጊ አይደለም።

ግሸበት ላይ የጓሮ አትክልት ብለን ከቤተመንግስት ጓሮ የጀመርነው፤ ቅድም እንዳነሳሁት ድጎማ ያደረግነው ለዛ ነው። መልካም አስተዳደር ላይ ከ5ሺ በላይ የብልጽግና አባላት በሁሉም ክልል አስረናል፤ አባርረናል፤ ከደረጃ ዝቅ አድርገናል። በዚህች ሁለት ወር ውስጥ ይህን ሰርተናል። ተቃዋሚ ጋር ብቻ ሳይሆን በውስጣችን ያሉ ሌቦችንም ለማጥራት ሙከራ አድርገናል። በቂ ነው ወይ? ከተባለ አይደለም ገና ብዙ ስራ ይጠበቅብናል። እርስዎ እንዳሉት በሰላም ከሞከርን በኋላ አልሳካ ሲል፤ ብቸኛ ሀይል የመጠቀም ስልጣን ያለው መንግስት ነው። ለእዚያ ደግሞ አቅም አለው። አቅም እንደሌለው ሆኖ የታየበት ዋና ምክንያት ዴሞክራሲውን ብንለማመድ የሚል ፍላጎት ስላለ ነው። ያም ሆኖ የፌደራል ሥርዓት ስሪታችንንም በደንብ መገንዘብ ጥሩ ነው።

በአማራ ክልል የተካሄደው እያንዳንዱ ሕግ ማስከበር መቶ በመቶ የተካሔደው በአማራ ልዩ ሀይል ነው። አንድም የፌደራል ጦር የለበትም። አንድም የሚመራው ፕሬዚዳንት ነው፤ የሚሳተፈው የአማራ ልዩ ሀይል ነው። እኛ ያደረግነው በሴኩሪቲ ካውንስል ጥናቱ ሲቀርብ ጉዳዩን ካየን በኋላ፤ ክልሎች ይምሩት ብለናል። የሴኩሪቲ ካውንስል አባላት ግን በየክልሉ ቴክኒካል ድጋፍ ይስጡ ብለን የመደብናቸው ሰዎች አሉ። መረጃ እና ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል። በዋነኝነት እነሱን የሚመራው ግን ፕሬዚዳንቱ ነው።

አማራም፣ ደቡብም፣ ኦሮሚያም ሁሉም ቦታ ከተሳካም ከተበላሸም የሚመራው ያው ፕሬዚዳንቱ ነው። አንዳንዴ ፌዴራል ሰው ታፍኗል ሲባል፤ ክልሎች ህጋዊ የማሰር ስልጣን ያላቸው፤ ህግ አስፈጻሚም፤ የህግ ተርጓሚ አባላት በየክልሉ እንዳሉ ሰው አይገነዘብም። በየክልሉ ህግ አውጪ፤ ህግ ተርጓሚ፤ ህግ አስፈጻሚ አለ። የማሰር የመጠየቅ መብት ያለው አለ። በዚህ ምክንያት አማራ ክልል የተደረገው ህግ ማስከበር (ኦፕሬሽን) የአማራ ክልል ምክር ቤት ሪፖርት ሲቀርብ ተወካዮች ህዝብ አነጋግረው ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው። እኔ ባልመራሁት ዘመቻ በዝርዝር ይሄ ነው፤ ያ ነው ማለት አልችልም።

ዝርዝር እቅድ ሰምቻለሁ፤ ሁኔታውን አውቃለሁ። ነገር ግን ልክ የፌደራል መንግስት እንደሚመራው አይነት ተደርጎ የቀረበው ስህተት ነው። የአማራውን ዘመቻ አማራ ይመራዋል፤ የኦሮሚያውን ኦሮሚያ ይመራዋል፤ የቤኒሻንጉልን ቤኒሻንጉል፣ የሶማሌውን ሶማሌ ይመራዋል። ሁሉም ጋር ግን ቴክኒካል ድጋፍ ይደረጋል። እናም አንደኛ ኦፕሬሽኑ ከውስጥ መሆኑን ማወቅ ጠቃሚ ነው። ሁለተኛ በህዝብ ጥያቄ የተጀመረ መሆኑን ማወቅ ጥሩ ነው።

በተጨማሪ ከተጀመረም በኋላ ህዝብ ደስተኛ መሆኑንና ሰላም እያገኘ መሆኑን ማወቅ ጥሩ ነው። ይሄ እንደተጠበቀ ሆኖ በስንዴ ማሳ ስንዴ ብቻ ሳይሆን እንክርዳድ፤ በብልጽግና እሳቤ ውስጥ አበልጻጊ ብቻ ሳይሆን ሌቦች እንዳሉት ሁሉ በሚያኮራ ስም እና ሁላችንም ልንመካበት በሚገባ ስም ሌሎች መጠቀም ፈልገዋል።

ፋኖ ለአማራም ለኢትዮጵያም ኩራት ነው፤ ምንም ጥያቄ የለውም። በጀግንነት ተዋግቷል፤ ወደፊትም በጀግንነት ይዋጋል። እሱ የአብይን ውዳሴ፣ ሙገሳ ጠብቆ የሚዋጋ ሳይሆን አገሩን ወዶ የሚዋጋ ነው። ከተነካችበት ወደፊትም አይቆምም። አድርጓል፤ ያደርጋል፤ እያደረገም ነው። ይሄ ጥያቄ የለውም መወደስ አለበት፣ መመስገን አለበት፤ መከበር አለበት። ይሄንን ስም ግን መጠቀሚያ ማድረግ ጥሩ አይደለም።

በከተማ ተኩስ ብቻ ሳይሆን፤ መዝረፍ፣ ሴቶች መድፈር፣ ሕጻን መጥለፍ፣ ነጋዴ መዝረፍ፣ ግብር መሰብሰብ፣ ሃሰተኛ (ፎርጅድ) ብር ማምረት፤ ይሄ የፋኖ ሥራ ሊሆን አይችልም። ፋኖ ሃሰተኛ (ፎርጅድ) ብር አይሰራም። ሴት አይደፍርም፣ ሕጻን አይጠልፍም። ሲባጎ ለጥፎ ግብር አይሰበስብም። አማራ ክልል የነበረው ይሄ ነው፤ የአማራ ክልል ተወካዮች ታውቃላችሁ። እማታውቁ ከሆነ ሕዝባችሁን ሂዱና ጠይቁ።

በነገራችን ላይ የተከበሩ አቶ ክርስቲያን፤ በአማራ ክልል ሕግ ማስከበር ከተያዙ ሰዎች በጣም የሚገርማችሁ 3 ሺህ 500 ሰው የተያዘው የከዳ ሠራዊት ነው። ከዚህ ውስጥ ከሁለት ሺህ በላይ የአማራ ልዩ ኃይል ነው። ከአማራ ልዩ ኃይል ታጥቆ ሠልጥኖ የከዳ፤ የከዳ ብሎ ፋኖ ከየት የመጣ ነው? አማራማ ባለ በሌለ አቅሙ አሰልጥኖ አስታጥቆ ጠብቀኝ አለው። ጠብቀኝ ካለው ቦታ ጠፍቶ፣ የሰፈር አለቃ ሆኖ፣ ክላሽ እየተኮሰ ሕዝብ የሚያምስ ሰው ሲያዝ ለምን ሕግ ተከበረ? ማለት ጥሩ አይደለም።

ምክንያቱም እርስዎ እንዳሉት አርሶ አደር የሚያርሰው ሰላም ካገኘ ነው። አገር የሚለማው ሰላም ካገኘ ነው። መባል ያለበት ችግር የለውም ጠላት ይረብሻል፤ በገዛ ልጆቻችን ግን መታመስ የለብንም ማለት ይገባል። ከድቶ በሰፈር አለቃነት ሰው ማስቸገር ጥሩ አይደለም። ለጊዜው ከፖለቲካ አንፃር እናንተም ደግፉችሁት ይሆናል፤ ግን ድንገት በሚቀጥለው ምርጫ ብታሸንፉና ክልሉን ብትመሩ ይሄን ዓይነት ልምምድ ጥሩ አይደለም። ሁሉም ነገር ሕግ የተከተለ መሆን አለበት።

በነገራችን ላይ በአማርኛ ሚዲያ ሕወሓት አንዲት እናት አምስት ልጇቿን ሰጠች፣ ሦስት ልጇቿን ሰጠች እያለ ይናገራል። በአማርኛ የሚናገረው ለማነው? ለእኛ እኮ ነው። ለእሷማ የሚያወራት በትግርኛ ነው። እየነገረን ያለው ለእኛ ነው። በአማርኛ አምስት ልጆች ሰጠች እያለ፤ እኛ አምስት አያስፈልግም ብለን አንዳንድ የወሰድነው እንኳን ምሽጉን ጥሎ ሰፈር ከገባ ማን ይጠብቅሃል? የገባው በግዴታ አይደለም ወዶ ነው። ወዶ ገብቶ ክላሽ ሰርቆ ሸጦ ባጃጅ የሚገዛ፣ ክላሽ ሰርቆ ሸጦ ሰፈር ሄዶ የሚዘርፍና የሚሸፍት ሰው መፍጠር ትክክል አይደለም።

የተሠራውን ሥራ በጥቅሉ ብቻ ሳይሆን በውጤት ደግሞ እንመልከተው፤ 3 ሺህ 500 የከዳ ሠራዊት፣ ብዙ ኩንታል ሀሽሽ ተያዟል፤ ፋኖ ሀሺሽ ምን ያደርግለታል? በኦሮሚያም በአማራም ብዙ ኩንታል ሀሺሽ ተይዟል። ከፍተኛ ቁጥር ያለው የውጭ ምንዛሬ፣ ሀሰተኛ (ፎርጂድ) ገንዘብ፣ የሰበሰብነው ይሄን ነው። ቦምብ፣ የሚቀጣጠል ፈንጂ፣ ስናይፐር ይዘናል።

በነገራችን ላይ የተከበረው ምክር ቤት እንዲገነዘበው የምፈልገው፣ ከዚህ ውጊያ በኋላ የገዛነው ለየት ያለ ክላሽ አለ። ኢትዮጵያ ውስጥ ድሮ አልነበረም፤ ከዚህ ግጭት በኋላ ያስገባነው መከላከለያ ብቻ ያለው ክላሽ አለ። በቀለሙ ብቻ የሚለይ ክላሽ ነው። ይህንን ክላሽ አገር እንከላከል፣ አገር አትፈርስም ብለው የቆሰሉ ኦሮሞዎችን፣ አማራዎችን፣ ወላይታዎችን ገድሎ መሳሪያ የወሰደ ሁሉ ፋኖ ነኝ ብሏል። ሊከላከለው የሄደውን ወንድሙን ገድሎ፤ መከላከያ ያንን ክላሽ ሲያይ ያመዋል። ያ ክላሽ ማንም ጋ የለም፤ ክልል የለም፤ ፖሊስ ጋር የለም። ሳያፍር አንጠልጥሎ ይሄዳል፤ ይሄ ትክክል አይደለም፤ ይጎዳናል።

ነፃነትና ብልጽግና ሥርዓት ሲኖር ነው። ሥርዓት ያስፈልጋል፤ ሁሉ ነገር በስርዓት መሆን አለበት። የጀገነ አንድም የአገር መከላከያ ሚኒስቴር አባል ይሆናል። የአማራ ልዩ ሃይል ይሆናል፤ ሚሊሻ ይሆናል፤ አልያም «ስትፈልጉኝ ጥሩኝ» ብሎ ቤቱ ይቀመጣል፤ ያርሳል። አሥርና ሃያ ሰላሳ ሆኖ እንደመከላከያ መሆን እና ሃይል መጠቀም ለአማራም ጥሩ አይደለም።

ለምክር ቤት ለመናገር አይመቸኝም፤ ግን አማራ ገጠመኝ የሚለው ጦር ሕወሓት ከሆነ፣ ሕወሓት እኮ አንድ ቋንቋ የሚያወራ፤ የሚደማመጥ፣ ችግር እንኳን ቢኖር ደብቆ የሚያወራ እንጂ በየሚዲያው የሚሰዳደብ አይደለም። አማራን ጠንካራ የሚያደርገው፤ አንድ ግንኙነት ሲኖር እንጂ አስር ቦታ ከተከፋፈለ እዚያ ሚሊሻ፣ እዚያ ልዩ ሃይል፣ እዚያ ሌላ ሲሆን መከላከልም አይችልም፣ ለአማራም ለኢትዮጵያም አይበጅም።

አንድ መሆን መሰብሰብ ያስፈልጋል። ይሄ መሳሪያ የያዘ ኃይል፣ ወጣት ኃይል፣ ብር የለመደ ሃይል፣ መኪና የሚቀማ ሃይል አርሶ አደር በሬ ሸጦ ሲመለስ የሚቀማ ሃይል እሳት ነው። በአማራ ባህል ውስጥ እሳት ዝም ብሎ አይለቀቅም። እናቶች ዝም ብለው እሳት አይለቁም። እንጀራ የሚጋግሩ ከሆነ እሳቱ እንዳይረጭ ሰብስብ የሚያደርገው በእበት የሚሰራ አንከርት የሚባል አለ። እሳት ከተረጨ ቤት ያቃጥላል። ወጥ የሚሰሩ ከሆነ ሰብስብ አድርጎ እሳቱን የሚይዝ ጋቻ የሚባል ነገር አለ። ይሄ እሳት ሰብሰብ ተደርጎ ካልተያዘ ወደፊትም ልንዋጋ አንችልም። ወደኋላም አስቸጋሪ ይሆናል። በዚያ መነጽር ማየት ጥሩ ነው።

የመብት ተሟጋቾች እንደዚህ ብለዋል ለተባለው፤ እነዚህ ተሟጋቾች የሚሟገቱት ለሰው ከሆነ ለሚጠለፈው፣ ለሚዘረፈው እና ለሚደፈረው ሕዝብ አይናገሩም እንዴ? በኢትዮጵያ ውስጥ ታዋቂ ያልሆኑ ሰዎች በሕይወት የመኖር መብት፤ ታዋቂ ከሆኑ ሰዎች ከመናገር መብት ጋር እንዴት አቻ ሆኖ ይታያል? ሰዎች በሕይወት ለመኖር እየተቸገሩ፣ እንደተባለውም እየተፈናቀሉ፣ እየተቸገሩ ኢትዮጵያዊ ሆነው በአገራቸው ውስጥ እንደሁለተኛ ዜጋ ሆነው እየኖሩ፣ እርሱን ለማስከበር የሚሰራ ጥረት እንዴት ከመናገር መብት ጋር እኩል ይታያል? ከመናገር ሰው ማኖር አይበልጥም? ይሄን ማየት ጥሩ ነው።

ይሄ ማለት ግን ይሔን የሚያክል ሕግ የማስከበር ሥራ ሲሰራ በስህተት የተያዘ ሰው የለም፤ ጥፋት አይጠፋም፤ የእኛ መንግስት እንከን አልባ ነው ማለት አይደለም። መገምገም አለበት። በስህተት የተያዘ ሰው ካለ፣ የተጎዳ ሰው ካለ፤ አላግባብ ሃይል የተጠቀመ ካለ መጠየቅ አለበት። ምክንያቱም አንደኛውን ጥፋት ለማከም ሌላ ጥፋት ማጥፋት ትክክል አይደለም።

ይሄን ደግሞ የተከበረው ምክር ቤት፤ በዋነኛነት የክልል ምክር ቤት ሥራ ቢሆንም የተከበረው ምክር ቤት ያለውን ነገር ኮሚቴ አቋቁሞ ማጥናት መጠየቅ ይችላል። ችግር ካለ ማረም አለበት። የአማራ ክልል ባለኝ ሪፖርት በሺህ የሚቆጠር ሰው አጣርቶ ፈቷል። የቀረም ካለ ተጣርቶ መለቀቅ አለበት። የተጎዳም ካለ ካሳ መከፈል አለበት። እኛ የምንፈልገው ሰላማዊ ክልል እንድንሆን ነው እንጂ ዜጎች እንዲበደሉ አይደለም። ግን ሦስት ሺህ 500 የከዳ ሰራዊት የት እንደገባ አይታወቅም? ለሚለው የከዳ ሰራዊት የሚጠየቅበት አለው። እና ይሄን ማየት ጥሩ ነው። እርስዎም ከሌሎች የፓርላማ አባላት ጋር ሄደው አይተው ጥሩ ጎኑን ማጠናከር፣ ችግር ካለ ደግሞ የሚታረምበትን መንገድ መፍጠር አስፈላጊ ነው።

«መንግሥት እያሸበረ ነው» የሚለው የሶሻል ሚዲያ ንግግር ጥሩ አይደለም። ቢያምኑም ባያምኑም አማራ ክልል ባሉ ከተሞች የጥይት ድምጽ ስለቀነሰ፤ እናቶች ተኝተው እያደሩ ያሉት አሁን ነው። ጎንደር መተኛት እኮ አይቻልም። ቅማንት ነው ምናምን እየተባለ የሚያድረው ሲተኮስ ነው። ሰዎች ለመውጣት ለመግባት ይፈራሉ። ባህርዳር ከተማ ውስጥ ተመሳሳይ ነው። ይሄን ደግሞ በደንብ የምትገነዘቡት ይመስለኛል።

ሕግ ይከበር፣ ሰላም እናስጠብቅ፤ ስህተት ካለ ግን ያንን እየቀነስን ትክክለኛውን መስመር የምንከተልበትን፤ እኛ በሕግ የምንታረምበትን መንገድ መከተል ጠቃሚ ይሆናል። ያ ካልሆነ ጥሩ አይሆንም። በሁሉም ክልሎች የሕግ ማስከበር ዘመቻው ተጠናክሮ ይቀጥላል። መፍትሔው ሕግ ማክበር ነው። እንትና ነኝ፣ አርሶ አደር ነኝ፣ ባለባንዲራ ነኝ፣ ባለከዘራ ነኝ ማለት አይሰራም። ሕግ ያላከበረ ይጠየቃል። እኛ የምንሰቃየው በስንቱ ነው? ዋስትናው ህግ ማክበር ብቻ ነው። ከዚህ በመለስ ሀሳብ መግለጽ፣ መነጋገር ችግር የለውም።

እዚያው ላይ ማህበራዊ ሚዲያን በሚመለከት፤ እንግዲህ በመጪው አምስት አሥርት ዓመታት የዓለም የኑሮ ሥርዓት ይቀየራል። የገንዘብ ሥርዓት፣ የጤና ሥርዓት፣ የትምህርት ሥርዓት፣ የፖለቲካ ሥርዓት፣ ብዙ ነገር ይቀየራል። ማህበራዊ ሚያው ብዙ ነገር እየነካካ ነው። አሁን እኛ ጋ ልምምዶች ናቸው። ብዙ ዕድሎችም ፈተናዎችንም ይዞ ይመጣል። ፈተናውን እንዴት አድርገን እንቋቋመዋለን፣ ዕድሉን ደግሞ እንዴት እንጠቀመዋለን? የሚለውን ማሰብ ያስፈልጋል። የቴክኖሎጂ ባለቤቶች ዋና ሥራቸው ዜጎች በእነርሱ ፍላጎት (አፕሊኬሽን) ላይ ተጥደው እንዲውሉ ማድረግ ነው። አሊጎሪዝሞች የሚጻፉት በዚሁ ስሜት ነው። ለምሳሌ እዚሁ ፓርላማ ያላችሁ ሰዎች እዚያ ጫፍ ያሉት ሰውዬና እዚያ ጫፍ ያሉት ሴትዮ ሁለታችሁም ወጥታችሁ ዩ ትዩብ ብትከፍቱ ሁለታችሁ ገጽ ላይ አንድ ዓይነት አይመጣም።

እርስዎ የሚፈልጉትን፣ እርሳቸውም የሚፈልጉትን ዩትዩብ ያውቃል፤ ያጠናችኋል። የሚሰጣችሁ የምትፈልጉንት ተቃራኒ ሃይል ነው። ዩትዩብ ላይ በአጀንዳ ሴቲንግ የሚሰሩ በርካታ የውሸት ዜናዎች የብዙ ሰው ጭንቅላት ያምሳሉ። ሲሰራ ውሎ እስኪ ዜና ልስማ ብሎ የውሸት ዜና ሰምቶ ሲታመም የሚያድርና ነገ ሥራ የሚበላሽበት በየአገሩ ስንት ሰው አለ?

እነዚህ አልጎሪዝሞች አላማቸው በውሸት፣ በጥላቻ፣ በስድብ ብዙ ተከታይ ያፈራሉ። ለምን? ብዙ ተከታይ ያለው ሰው ብዙ ብር ያገኛሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ በዩ ትዩብ የሚከፈል ገንዘብ፤ ታክስ የሚከፍል የለም። ዩ ትዩቡን ላይክ ሼር እያደረግን የምናባዛው እኛ ነን። የእሱ አካውንት ያለው ግን የሆነ ቦታ ነው።

ይሄን የመገናኛ ብዙሃን ባለስልጣኑም፤ የመረጃ እና ደህንነቱም ማጥናት አለበት። ማንኛውም ዜጋ ከሚያገኘው ገቢ ታክስ መክፈል አለበት። የሚያገኘው በዶላር እኮ ነው። በዚህ ምክንያት ሥራው ማጋባት፣ ማፋታት ማጣላት ነው። ሰው በባህሪው ተቃራኒ ሃይል ስለሚስበው፤ ሰው እንዲያይ ሁል ጊዜ መርዶ ያቀርባሉ።

ሌላው ችግር አክቲቪስት፣ ጋዜጠኛ እና ፖለቲከኛ ተቀላቅሏል። አንድ ሰው ጠዋት አክቲቪስት ነው፤ ከሰዓት ፖለቲከኛ ነው፤ ከዚያ ደግሞ ጋዜጠኛ ይሆናል። ሲያባላ አክቲቪስት ነው፤ ሲጠየቅ ደግሞ ጋዜጠኛ ነው። ይሄ ትክክል አይደለም፤ ወገኖቼ ይሄ አገር በቋፍ ነው፤ መጠናከር አለበት፤ ዝም ብሎ ማንም መከላከያን የሚያፈርስ ሥራ ሲሰራ አትደግፉ።

እነዚህን እናንተ የምትናገሩላቸው አክቲቪስቶች በኢሜል የአማራ ጀኔራል አትዋጋ፤ የኦሮሞ ጀኔራል አትዋጋ እያሉ መከላከያን የሚያፈርሱ ናቸው። መከላከያ ከፈረሰ በማንኛውም ቅፅበት አገር ትፈርሳለች። ተቋም የሚያፈርሱ ሰዎችን ጋዜጠኛ አክቲቪስት እያልን ስም አንስጣቸው። የመናገር እና ሃሳብን የመግለፅን መብትን እየነካችሁ እያፈናችሁ ትላላችሁ? ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ዐቢይ የተሰደበ መሪ አለ? በስድብ እስክስታ እየተወረደ ነው። በቀን ሶስት ሰዓት እና አራት ሰዓት እየተኛሁ፤ በለፋሁለት ህዝብ እንድዋረድ የሚለፈልፍ አለ።

**( ይቀጥላል)**

# ስፖርት





# አረንጓዴው ጎርፍ በኦስሎ

ቦጋለ አበበ

የ2022 የዳይመንድ ሊግ ውድድሮች መነሻቸውን በኳታር መዲና ዶሃ አድርገው በእንግሊዝ በርሚንግሃም፣ በአሜሪካ ዩጂን፣ በሞሮኮ ራባት፣ በጣሊያን ሮም ከተካሄዱ በኋላ ከትናንት በስቲያ ምሽት ስድስተኛዋ የውድድሩ መዳረሻ ከተማ በሆነችው የኖርዌይ መዲና አስሎ በተለያዩ ርቀቶች ፉክክሮችን አስተናግዷል።

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በተሳተፉበት በዚህ የኦስሎ ዳይመንድ ሊግ የአምስት ሺ ሜትር ውድድር በሁለቱም ጾታ ከአንድ እስከ ሶስት ባለው ደረጃ በማጠናቀቅ በርቀቱ ነግሰዋል።

ባለፉት አመታት በመካከለኛ ርቀቶች በተለይም በአንድ ሺ አምስት መቶ ሜትር ውድድር አስደናቂ ብቃት በማሳየት ትልቅ ተስፋ የተጣለባት ወጣቷ አትሌት ዳዊት ስዩም ልዩ ተሰጥኦ ባሳየችበት ርቀት በውጤታማነቷ ገፍታ በአለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናና ኦሊምፒክን በመሳሰሉ መድረኮች ጎልታ መታየት አልቻለችም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህች ድንቅ አትሌት በአዲስ ርቀት ውጤታማ ሆና ብቅ ብላለች። በአምስት ሺ ሜትር ልምድ ባይኖራትም ውጤታማ እየሆነች የምትገኘው አትሌት ዳዊት በኦስሎው ዳይመንድ ሊግ በርቀቱ ብዙ ልምድ ያካበቱና ቁንጮ የሆኑ ኢትዮጵያውያን አትሌቶችን ጭምር በማሸነፍ አስደናቂ ውጤት አስመዝግባለች።

በርቀቱ በአለም ላይ ትልቅ ስምና ዝና ያላቸው በርካታ ኢትዮጵያውያንና የሌሎች አገራት አትሌቶች በተሳተፉበት የኦስሎ ዳይመንድ ሊግ ውድድር አንድ ሺ ሜትሩን እጅግ በጠንካራ ፉክክር በ2:53:83 ማገባደድ የቻሉት ከዋክብት አትሌቶች ሁለት ሺ ሜትሩንም ፈጣን በሆነ 5:52:33 ሸፍነዋል። በበርካታ ከዋክብት አትሌቶች እስከ መጨረሻው ዙር በአስደናቂ ፉክክር የታጀበውን ውድድር ወጣቷ




አስደናቂ ፉክክር በታየበት የኦስሎ ዳይመንድ ሊግ 5ሺ ሜትር ውድድር አትሌት ዳዊት ስዩም አሸናፊ ሆናለች፣

አትሌት ዳዊት ለማጠናቀቅ አንድ ዙር ሲቀራት አፈትልካ በመውጣት ድሉን ጨብጣለች። በርቀቱ ከአለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና እስከ ኦሊምፒክ መድረኮች መንገስ የቻሉ እንደ ለተሰንበት ግደይ፣ ጉዳፍ ጸጋይና አልማዝ አያና የመሳሰሉ ድንቅ ድንቅ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ውድድሩ አንድ ዙር እስኪቀረው ያሳዩት ጠንካራ ፉክክር በመጨረሻም ለዳዊት አስደናቂ የአጨራረስ ብቃት እጅ ሰጥቷል።

በሪዮ ኦሊምፒክ በ10ና 5ሺ ሜትር የወርቅና የብር ሜዳሊያ ካጠለቀች በኋላ በወሊድና በጉዳት ምክንያት ለረጅም ጊዜ ከውድድር ርቃ የተመለሰችው አልማዝ አያና በኦስሎው ምሽት ጠንካራ ተፎካካሪ መሆኗን ዳግም ብታሳይም ከእሷ በኋላ በርቀቱ የነገሱ ኢትዮጵያውያንን መቋቋም አልቻለችም። መጨረሻው ዙር ላይ ከሜዳሊያ ፉክክሩ የወጣችው አልማዝን ወደ ኋላ ትተው የአሸናፊነት ክሩን ለመበጠስ እልህ አስጨራሽ ፉክክር ያደረጉት የቶኪዮ ኦሊምፒክ የ10ና 5ሺ ሜትር የነሐስ ሜዳሊያ አሸናፊዎቹ ጉዳፍና ለተሰንበት አዲሷን የርቀቱ ኮከብ ማቆም አልተቻላቸውም። በዚህም ዳዊት 14:25:84 በሆነ ሰአት ጣፋጭ ድል ልታስመዘግብ ችላለች። ዳዊትን ተከትላ ጉዳፍ 14:26:69 በሆነ ሰአት ሁለተኛ ሆና ስታጠናቅቅ የ10ና 5ሺ ሜትር የአለም ክብረወሰን በእጇ የሚገኘው ለተሰንበት 14:26:92 በሆነ ሰአት ሶስተኛ ደረጃን ይዛ ፈጽማለች።

በዚህ ውድድር የታየው አስደናቂ ፉክክር የአለም ክብረወሰን እንዲሻሻል በቂ ባይሆንም በርቀቱ ታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ ሰባት አትሌቶች ከ14:35 በታች ማጠናቀቅ የቻሉበት ሆኗል። በተመሳሳይ ስምንት ያህል አትሌቶችም ከ14:40 በታች በማጠናቀቅ የኦስሎን ዳይመንድ ሊግ የማይረሳ አድርገውታል።

የኦስሎው የዳይመንድ ሊግ ምሽት በተመሳሳይ ርቀት በወንዶች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በግል ውድድር ከአንድ እስከ ሶስት በማጠናቀቅ የአረንጓዴውን ጎርፍ ታሪክ ደግመዋል። በሴቶቹ ውድድር በ1500 ሜትር የምትታወቀው አትሌት የ5ሺ ሜትር ቁንጮዎቹን ስታሸንፍ በወንዶቹ ተመሳሳይ ውድድር በተቃራኒው በ5ሺ ሜትር የሚታወቀው አትሌት በ1500 ሜትር ገናና ስም ያለውን አትሌት የረታበት ውጤት ተመዝግቧል።

ከውድድሩ መጀመሪያ አንስቶ የመጠባበቅና የመፈራራት ድባብ የተስተዋለበት ቀዝቀዝ ያለ ፉክክር መጨረሻ ላይ የቻለ እንዲያሸንፍ አትሌቶቹ ፍላጎት እንደነበራቸው ያስታውቅ ነበር። የሁለት ጊዜ የአለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ቻምፒዮና የ1500 ሜትር አሸናፊው ሳሙኤል ተፈራ ፉክክሩን እየመራ 3ሺ ሜትሩን በ7:54:39 አገባዷል። ከዚህ በኋላ ወደ ኋላ በመመለስ አጨራረስ ላይ ጉልበት ቆጥቦ ለማፈትለክ የሞከረው ሳሙኤል እቅዱ በሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ጥላሁን ሀይሌ ከሽፏል። በአምስት ሺ ሜትር ባለፉት አመታት ተስፋ ተጥሎባቸው ከነበሩ አትሌቶች አንዱ የነበረው ጥላሁን በበርካታ ውድድሮች ከአሸናፊነት ርቆ ቢቆይም ኦስሎ ላይ በ13:03:51 ወደ አሸናፊነት የተመለሰበትን ድል አስመዝግቧል። ፉክክሩን በጥሩ መንገድ ሲመራ ቆይቶ አጨራረስ ላይ እቅዱ የከሸፈበት ሳሙኤል ተፈራ 13:04:35 በሆነ ሰአት የሁለተኛነቱን ደረጃ አላጣውም። እሱን ተከትሎም ስኬታማው የ3ሺ ሜትር መሰናክል ስኬታማው አትሌት ጌትነት ዋለ 13:04:48 በሆነ ሰአት ሶስተኛ ደረጃን ይዞ በማጠናቀቅ በርቀቱ የኢትዮጵያውያን የበላይነት ጎልቶ እንዲታይ አድርጓል።



## አማራ ክልል

ንብረትነቱ የአቶ ሳጅን አለሽኝ አብጤ የሰሌዳ ቁጥር - ኮድ 01-23686 አማ የሞተር ቁጥር -93477 የሻንሲ ቁጥር - 42025 የተፈቀደለት የጭነት ልክ (መጠን) 3 ሰው የተሽከርካሪ ዓይነት - ባጃጅ የሆነ ተሽከርካሪ ሊብሬ የጠፋባቸው መሆኑን ለፖሊስ ያመለከቱ ስለሆነ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ሪፖርት ካልተደረገ ለአመልካች ምትክ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአብክመ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ባለሥልጣን የምሥራቅ ጎጃም ዞን ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ተጠሪ ጽ/ቤት የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ቡድን**

## ኦሮሚያ ክልል

ንብረትነቱ ስም ከፈለኝ ነጋሽ ለማ የተመዘገበ ተሽከርካሪ ሠሌዳ ቁጥር 1-63147-ኦሮ የሻንሲ ቁጥር EAYACARWAJG009710 የሞተር ቁጥር AK4KJ4574312 ሲሆን ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ታርጋ ጠፋብን ብለው በ 29/09/2014 ዓ.ም አመልክቷል፡፡ ታርጋውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር የሞጆ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

ንብረትነቱ የጨፌ ኦሮሚያ ጽ/ቤት የሰሌዳ ቁጥር 4-04546 ኦሮ የሆነ፣ የሻንሲ ቁጥር AHTER22G506061351፣ የሞተር ቁጥር 2KD-5809108፣ የሊብሬ ቁጥር 0174715 የሆነ የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፍቶብናል በማለት በ30/09/2014 ዓ.ም አሳውቀውናል፡፡ ስለዚህ ይህንን ሰሌዳ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ተይዟል የሚል አካል ቢኖር ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ለመ/ቤታችን ሪፖርት የማያደርጉ ከሆነ ለባለንብረቱ ሌላ ምትክ ሰሌዳ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር የሰበታ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 1- A05645 ኦሮ የሆነ ሰሌዳ ጠፍቶብኛል ብለው አቶ ንጉሴ ቶላ በ11/08/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ሰሌዳውን በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ ካላቀረበ መ/ቤቱ ለባለንብረቱ ሌላ ተለዋጭ ሰሌዳ የሚሰጥ መሆኑን ያስታውቃል፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የምዕራብ አርሲ ዞን ትራንስፖርት ባለሥልጣን ሻሸመኔ**

የባለንብረቱ ስም አበራ አምሳሉ የተሽከርካሪ ዓይነት ት/ሣይክል የሰሌዳ ቁጥር 1-28890 ኦሮ የሻንሲ ቁጥር MD6M14PFXF4A4069 ሞዴል ትቭስ የሞተር ቁጥር OK4AF4187675 የሊብሬ ቁጥር 0340787 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሠሌዳ ቁጥር 1-28890 ኦሮ ጠፋብን ብለው በ22/09/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ የሰሌዳ ቁጥር 1-28890 ኦሮ ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ምትክ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የዱከም ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ሽጋዉ ባህሩ አባተ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-5016 የተሽከርካሪው አይነት ሞተር ብስክሌት የሻንሲ ቁጥር MD634KE4XF2C03916 ሞዴል RTR160 የሞተር ቁጥር 0E4CF2740860 የሊብሬ ቁጥር 386344 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 30/9/2014ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአዲስ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሉሲ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B12449 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር TSMLYE21S00737577 ሞዴል LYE21S የሞተር ቁጥር M16A-2317282 የሊብሬ ቁጥር 283085 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 30/9/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዮሐንስ አለማየሁ ታሪኩ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A24308 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር MROHR29G002020033 ሞዴል KUN25L-CRMSHW የሞተር ቁጥር 2KD-7434408 የሊብሬ ቁጥር 406122 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 30/9/2014 አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካት ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አስራት መሐመድ ይመር የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-28658 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር VFKTX34CW42EX6064 ሞዴል NO MODEL SEMI TRIALER የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0189760 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ1/10/2014ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሳሙኤል ፋንቱ ገብሬ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-6140 የተሽከርካሪው አይነት ሞተር ብስክሌት የሻንሲ ቁጥር MD2A21BZ8GWM07906 ሞዴል boxer የሞተር ቁጥር PFZWGM45512 የሊብሬ ቁጥር 442618/405097 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ2/10/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ጃምቦ ኮንስትራክሽን P.L.C የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-26053 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር CWB450H-03771 ሞዴል UD-CWB450H የሞተር ቁጥር PF6-121078T ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 2/10/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆን እንገልፃለን ፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የአዲስ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

በከሳሽ ወ/ሮ እታፈራው መርሻ እና ተከሳሽ አቶ ማርቆስ አለዊ ሽዋ መካከል ስላለው የቤተሰብ ክስ ጉዳይ ተከሳሽ አቶ ማርቆስ አለዊ ሽዋ በ23/10/2014ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ 4፡30 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 3ኛ ቤተሰብ ችሎት መልስ ይዘው እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**